# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

## የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኰሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በድራሼ ብሔረሰብ


በ

ዳንኤል ደጀኔ



ታህሳስ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በድራሼ ብሔረሰብ


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

በኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር የኤም. ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት


በ

ዳንኤል ደጀኔ

አማካሪ

አቶ ዘሪሁን አስፋው


ታህሳስ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

## የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኰሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

## ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በድራሼ ብሔረሰብ

**በ**

**ዳንኤል ደጀኔ**


**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | | |
|---|---|---|
| **አማካሪ** | **ፊርማ** | **ቀን** |
| **አቶ ዘሪሁን አስፋው** | ------------------------ | -------------------------------- |
| **የውስጥ ፈታኝ** | | |
| **ዶ/ር ዓለሙ ካሣዬ** | ------------------------ | -------------------------------- |
| **የውጭ ፈታኝ** | | |
| **ዶ/ር ሙሉጌታ ነጋሣ** | ------------------------ | -------------------------------- |

## የኢትዮጵያ ካርታ




## የደቡብ ብሔራዊ ክልል ካርታ




የደራሼ ወረዳ

ምንጭ፡ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ዓመታዊ መጽሔት፣ሀዋሳ 2016 G.C

# ሙዳዬ ቃላት

ዲራይታት …………………..የድራሼ ብሔረሰብ ቋንቋ

ቃላላ /ጨቃ/……………….ባህላዊ መጠጥ

ፓውራ ……………………ባህላዊ የእርሻ መሳሪያ

ሀውዳ ………………………የእጅ ጥበብ ሠራተኞች

ዋሎት /ማኪያ/ …………..የቀብር አስፈፃሚዎች

ኤታንታ …………………..አምራች ኃይሎች

ዳማ ………………………የድራሼ ብሔረሰብ መሪ /ንጉስ/

ፓልዳ …………………….የጎሳ አለቃ

ሼላ ……………………….የአንድ ንዑስ ጎሳ መሪ

ሻና ………………………..የመንደር መሪ

ኦስማረ …………………….የቤተሰብ መሪ

አራፋይታ ………………...የዳማው ችሎት ስብስብ

ሆርቤ ……………………የችሎት አስፈፃሚ

ፒያ ………………………የዳማው ችሎት አፈ-ጉባኤ

ሞራ ……………………..የችሎት አደባባይ

አፋ-ላማ …………………..ከብቶች እያጠፉ የሚከፈል ክፍያ

ኤርጋዳማ …………………እጅ መስጠት /ራስን ማስገዛት/

ዳሃላ ………………………የውርስ ጋብቻ

ሎሀላ ……………………..የጠለፋ ጋብቻ

ራቦት ……………………..የመተጫጨት ጋብቻ

ሀልቶት …………………..የጎሳና አምልኮአዊ መሪዎች የጋራ መጠሪያ

አባ- ቲምባ ………………..የመንደር ጡርንባ ነፊና አስተባባሪ

አራርሳ /ሆሮታ/ …………..የባህላዊ ግጭት መፍቻ ስርዓት መጠሪያ

# ምስጋና

ከዚህ ጥናት ርዕስ መረጣ ጀምሮ ድጋፍዎ ሳይለየኝ “ፍጠን እንጂ” የሚል አባታዊ ማበረታቻ ባይከተለኝ ጥናቴ እዚህ አይደርስም፡፡ መምህሬ ዘሪሁን አስፋው ዕድሜ፣ ጤናና ሠላም አይለዩዎት፡፡

ለጥናቱ መሳካት ያገዛችሁኝ ወንድሞቼ መኳንንት መሐመድና ዳንኤል በቀለ በእውነት አመሰግናለሁ፡፡

ስለ ትዕግስትሽ እና ስለ ድጋፍሽ ባለቤቴ ትዝታ በቀለ ምስጋና ይገባሻል፡፡ የተሞነጫጨረ ጽሁፌን በእርጋታ አንብበሽ ለተየብሽልኝ ዘርፌ እንዲሁም መረጃዎችን ሁሉ ለሰነዳችሁልኝ ለአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የሥራ ባልደረቦቹ እግዚአብሔር ውለታችሁን ይክፈል፡፡

# አበርክቶ

በተለያዩ ተፅዕኖዎች ውስጥ አልፈው የቀደመ ባህላቸውን ጠብቀው ለመቆየት ዋጋ ለከፈሉ የባህል ስርዓቱ መሪዎችና ሽማግሌዎች ለፅናታቸው ብርታት ይሆንልኝ ዘንድ ይህን ጥናቴን አበርክቻለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ውስጥ በሚገኘው በሰገን አካባቢ ህዝቦች ዞን በድራሼ ልዩ ወረዳ ላይ ያተኮረ ሲሆን የጥናቱ ዋና አላማም የድራሼ ብሔረሰብን ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት መግለጽና መተንተን ነው፡፡ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት ለጥናቱ በተመረጠው ቦታ በአካል በመገኘት በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት ነው፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች የተገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በብሔረሰቡ አባላት እና አጎራባች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ምክንያቶች፣ ግጭቶቹ የሚፈቱባቸው ባህላዊ ተቋማትና ሥርዓቶች እንዲሁም የባህላዊ ሥርዓቱ እሴቶች ተለይተው ተተንትነዋል፡፡

በጥናቱ ሃያ ሶስት የመረጃ አቀባዮች የተሳተፉ ሲሆን ከእነዚህ ሃያ ሶስቱ ዘጠኙ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ በተሰበሰቡት መረጃዎች ገላጭ የምርምር ስልትን በመጠቀም የይዘት ትንተና ተካሂዷል፡፡

በጥናቱም እንደተገኘው በድራሼ ብሔረሰብ ተዘውትረው የሚፈጠሩ ግጭቶች የጎሳ ግጭት፣ ከአጎራባች ብሔረሰቦች (ከአሌ፣ ኮንሶ፣ ዘይሴ) ብሔረሰቦች ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶች፤ የነፍስ ግድያ ግጭት ናቸው፡፡ የእነዚህ ግጭቶች መነሻ ምክንያት ደግሞ ድንበር መግፋት፣ በሰው ንብረት ላይ ሰደድ እሳት መልቀቅ፣ መካካድ መሆናቸው በጥናቱ ታውቋል፡፡

ብሔረሰቡ እነዚህን ግጭቶች የሚፈታበት አራርሳ (ሆሮታ) ተብሎ የሚጠራ የግጭት መፍቻ ሥርዓት ያለው ሲሆን የግጭት መፈቻ ተቋማቱ ደግሞ የቤተሰብ መሪ (ኦስማረ)፣ ሻና፣ ሼላ፣ ፓልዳ እና በንጉሱ (በዳማው) የአራፋይታ ችሎት መሆናቸው ጥናቱ የተመለከተ ሲሆን ግጭቶቹም የሚፈቱት በሽምግልና፣ በዳኝነትና በእርቅ ሥርዓት መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

# ማዉጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ሙዳዬ ቃላት……………………………………………………………………………..i

ምስጋና…………………………………………………………………………….....iii

አጠቃሎ……………………………………………………………………………………iv

አበርክቶ…………………………………………………………………………………...v

ማውጫ……………………………………………………………………………………...vi

1. መግቢያ…………………………………………………………………………1

1.1. ጥናቱ አደረጃጀት………………………………………………..………...........1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ……………………………………………………2

1.3. የጥናቱ ዓላማ……..…………………………………………..……………….2

1.4. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች ……………………………………………..….3

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ……………………………………………..…………..3

1.6. የጥናቱ ወሰን ……………………………..…………………..……….....3

1.7. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ...…………………………………………..…………….4

1.8. የመረጃ ትንተና ዘዴ………………………………………………………..….5

1.9. መረጃ ሰጪዎች አመራረጥ ………………………………..……………….6

1.10. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች……..…...…..6

1.11. የመስክ ተሞክሮ……………………..…………...................................7

2. የድራሼ ብሔረሰብ ዳራ …………………….…………………………………......10

2.1. መልክአ ምድራዊ ገጽታ……………………………………..………………..10

2.2. የብሔረሰቡ አመጣጥ አፈ ታሪክ ……………………..………………...12

2.3. ከታሪክ መዛግብት አንፃር…………………………………………………..13

2.4. የብሔረሰቡ ቋንቋ /ዲራይታት/ ……………………………………………....14

2.5. እምነት/ሀይማኖት/ …… 15
2.6. የብሔረሰቡ መተዳደሪያ …… 16
2.7. ጋብቻ …… 17
2.8. የብሐረሰቡ ማህበራዊ አደረጃጀት …… 19
2.9. የድራሼ ብሔረሰብ ባህላዊ እሴት …… 21

3. ክለሳ ድርሳናን …… 23

3.1. የግጭት ምንነት …… 23

3.2. የግጭት መንስኤዎች …… 25

3.3. የግጭት አይነቶች …… 25

3.4. የግጭት መፍቻ ዘዴች …… 27

3.5. የተዛማጅ ጥናቶች ክለሳ (ቅኝት) …… 27

3.5.1. በድራሼ ብሔረሰብ ላይ የተደረጉ ጥናቶች …… 28

3.5.2. በባህላዊ የግጭት አፈታት ላይ የተደረጉ ጥናቶች …… 29

3.6. የባህላዊ አስተዳደርና የግጭት ፍትህ ስርዓት መዋቅሮች …… 31

3.6.1. የባላዊ አስተዳደር መዋቅር ገጽታ …… 31

3.6.2. የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ መዋቅር ገጽታ …… 37

3.6.3. ባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ የመዋቅሩ መሪዎች ሚና እና የሚዳኟቸው ጉዳዮች …… 40

3.6.4. የባህላዊ ግጭት መፍቻ ሰርዓት …… 46

3.6.4.1. ማስታረቅ፣ ማስማማት፣ መዳኘት መቅጣት

የባህላዊ ግጭት መፍቻ ስርዓት አራርሳ /ሆሮታ/ ……..……46

3.6.4.2. በግጭት አፈታት ሥርዓቱ የሚታለፉ ሂደቶች……………....48

3.6.4.3. የባህላዊ ፍትህ ሥርዓት ውሳኔዎች ……..………………….49

4. ግጭት እሳቤ፣ የግጭት አይነቶች፣ ምክንያቶችና የአፈታት ሥርዓታቸው…………......51

4.1. የግጭት ዓይነቶችና አነሳሽ ምክንያታቸው…………..……………..……........51

4.2. ዋና ዋና የግጭት ዓይነቶችና አፈታት ስርዓታቸው…………..……..…..….58

4.2.1. የነፍስ ማጥፋት ግድያ ግጭት አፈታት ሥርዓት…………..………...58

4.2.2. የጠለፋ ግጭት አፈታት……………………………………………….63

4.2.3. የጎሳ ግጭት አፈታት……………..…………………………........66

4.2.4. ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶች

የአፈታት ሥርዓት…………………………………………………...68

5. በባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቱ ላይ የተደረገ ትንተና……………………………77

5.1. የባህላዊ ሥርዓቱ ፋይዳ …………………………………………………...77

5.2. የባህላዊ ሥርዓቱ እሴቶች ……………………………………………….80

5.3. የባህላዊ ግጭት መፍቻና የመደበኛ ፍትህ ሥርዓት ተዛምዶ……………….81

5.4. የተቋማቱ ውሳኔ ተቀባይነት………………………………………..……..82

5.5. ለሁለቱ ተቋማት ማህበረሰቡ ያለው አመለካከት ………..………………..83

5.6. የባህላዊ ሥርዓቱ ጥንካሬና ክፍተት ……………………………...………84

5.6.1. የባህላዊ ሥርዓቱ ጥንካሬዎች ……………………………..………84

5.6.2. የባህላዊ ሥርዓቱ ክፍተቶች ……………………………………………......85

5.7. በባህላዊ ሥርዓቱ የሴቶችና የህጻናት ተሳትፎ ……………………………………....86

6. ማጠቃለያ…………………………………………………………………..………..…87

ይሁንታ……………………………………………………………………..................89

የተጠቀሱ ምንጮች…………………………..………………………………..……………..91

አባሪዎች………………………………………..……..…………………………......95

# 1. መግቢያ

የድራሼ ብሔረሰብ ባህላዊ ግጭት አፈታት ዘመናዊ የዳኝነት ስርዓት ተፅዕኖ ያሳረፈበት ቢሆንም ብሔረሰቡ አሁን ድረስ ከዘመናዊ ዳኝነት ይልቅ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ ግጭቶችን በባህላዊ የፍትህ ስርዓት ሲፈታ ይታያል፡፡ ይህ ስርዓት በባህላዊ የአስተዳደርና የፍትህ መዋቅር የተቃኘ ሲሆን የራሱ ደንቦች አሉት፡፡ የማህበረሰቡም አባላት በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ይቀበላሉ፡፡

ይህ ጥናት የድራሼ ብሔረሰብ ግጭቶች ሲፈጠሩ የሚፈታበትን ባህላዊ ዘዴዎች፣ስርዓቶችንና ደንቦችን ማጥናት በብሔረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ የተለያዩ የግጭት ዓይነቶችን መተንተንና እነዚህን ግጭቶች በባህላዊ መንገድ የሚፈቱ አካላት ለማህበረሰቡ የአብሮነት ህይወት የሚጫወቱትን ሚና ማጥናት ነው፡፡ በዚህ የባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓት ውስጥ ያሉ እውቀቶችን ለዘመናዊ ህግና የዳኝነት ስርዓት በመጠቆም ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማሳየትና ብሔረሰቡን ማስተዋወቅ የጥናቱ የትኩረት ነጥቦች ናቸው፡፡

## 1.1. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ በስድስት ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ ቀዳሚው ምዕራፍ የጥናቱን አጠቃላይ ገጽታ የሚያስተዋውቀው መግቢያ፣ ጥናቱን ለማጥናት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች፣ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን አላማና ይህንን አላማ የማሳከባቸው ስልቶችን የያዘ ነው፡፡የዚህ ተከታይ ምዕራፍ ለጥናቱ የተመረጠው አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ፣ የብሔረሰቡን ታሪክ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አደረጃጀት የሚመለከት ነው፡፡

የጥናቱ ሶስተኛ ምዕራፍ ስለግጭት መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳብ በተለያዩ ምሁራን የተሰነዘሩ ሀሳቦች በንፅፅር የሚታዩበት፣በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ከዚህ ቀደም የተጠኑ ጥናቶች ጥንካሬና ቀርነታቸው ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ዝምድናና ልዩነት እንዲሁም የድራሼን ብሔረሰብ ጥንታዊ ባህላዊ የአስተዳደርና የፍትህ መዋቅር ቅርፅ የሚተነትን ነው፡፡

የዚሁ ተከታይ የጥናቱ ምዕራፍ በድራሼ ብሔረሰብ ተዘውትረው የሚከሰቱ ግጭቶች፣የሚፈቱበት ስርዓት እንዲሁም ግጭቶቹም ሲፈቱ የሚያልፉበት ሂደት በዝርዝር ይተነተናል፡፡ የባህላዊ ግጭት ስርዓቱ ፋይዳዎች እሴቶችና በባህላዊ የዳኝነት ስርዓቱና

በመደበኛው ፍርድ ቤት የፍትህ ስርዓት መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት፤የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ ድክመትና ጥንካሬዎች በጥናቱ አምስተኛ ምዕራፍ በንፅፅር ይቀርባል፡፡ በምዕራፍ ስድስት  የጥናቱ ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ለማቅረብ ስነሳ ሁለት ርዕሰ ጉዳዮችን አሰብኩ፡፡ አንደኛው የባህል ጥናት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የልጆች ስነ-ጽሁፍ ነበር፡፡ ይህን ፍላጎቴን ይገፎ የረዥም ጊዜ የቀለም አባቴን መምህር ዘሪሁን  አስፋውን አማከርኩ፡፡ በባህል ጥናቱ ላይ ትኩረት እንዳደርግ ጠቆሙኝ፡፡ በዚህም የድራሼ ብሔረሰብ ቀዳሚ ምርጫዬ ሆነ፡፡

በብሔረሰቡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳኝ አንዱ ምክንያት ከፊሉን የቀለም ትምህርት ዘመኔን በአካባቢው በተከታተልኩበት ጊዜ የብሔረሰቡን ባህል፣ ወግና ልማድ በቅርበት ለማወቅ መቻሌ ነው፡፡ እዚያ በቆየሁባቸው አመታት በአካባቢው ተደጋጋሚ የሆኑ ደም አፋሳሽ ግጭቶች በተለያዩ ምክንያቶች ይከሰቱ ነበር፡፡ በዚያን ወቅት በ«ከተማ» አካባቢ ፍርሃትና ስጋት ይነግስ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ትልቅ የተባለና ደም ያፋሰሰ ግጭት  በሀገር ሽማግሌዎች በባህላዊ መንገድ ችግሩ ተፈቶ እርቀ ሰላም ወርዶ ሁሉም ወደ ተለመደው የዕለት ተዕለት ህይወቱ ይመለሳል፡፡

ይህ ሁኔታ በወቅቱ ባይገባኝም በመጀመሪያ ዲግሪና በሁለተኛ ዲግሪ በወስድኳቸው የፎክሎር ኮርሶች የባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓት ራሱን ችሎ ሊጠና እንደሚችል ተገነዘብኩ፡፡ በዚህም የድራሼ ብሔረሰብ የግጭት አፈታት ስርዓትን ባጠናና ብሔረሰቡ ለዘመናት ችግሩን ሲፈታበት የኖረውን ባህላዊ የዳኝነት ስርዓትን ሰንዶ ማኖር የባህላዊ ስርዓቱን ጠቃሚ እሴቶች ለዚህ ትውልድና ለዘመናዊው የፍትህ ስርዓት ማስተላለፍ ይቻላል የሚል እምነት በውስጤ ተፈጠረ፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ደግሞ የተጠና ጥናት ውስን መሆኑ የበለጠ ይህን ጥናት እንዳጠና አነሳስቶኛል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የድራሼ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትን መመርመር፣ መግለጽና መተንተን ነው፡፡ ይህን አቢይ ዓላማ በመያዝ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- የድራሼ ብሔረሰብ የግጭት መንስኤዎችን መለየት፣ የግጭት አፈታት ሂደቶችን፣ መዋቅሮችንና የእርቅ ማጽኛ ሥርዓቶችን መዘርዘርና መተንተን
- ግጭቶች በሚፈቱበት ሂደት ውስጥ ያሉ ባህላዊ እውቀቶችን በመተንተንና በመተርጎም ለዘመናዊ ህግና የዳኝነት ስርዓት ጠቃሚነቱን ማሳየት፣

## 1.4. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት በድራሼ ብሔረሰብ የግጭት ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ምን ይመስላል? የሚሉ ዓበይት ጥያቄዎችን በመያዝ የሚከተሉትን ዝርዝር የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

- በድራሼ ብሔረሰብ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚፈጠሩ ግጭቶች ምንምን ናቸው? የግጭቶቹ ምክንያቶች ምንድናቸው ?
- በድራሼ ብሔረሰብ ግጭት ከተፈጠረበት እስከሚፈታበት ድረስ ያሉ ሂደቶችና ስርዓቶች ምን ይመስላሉ?
- በግጭት አፈታት ስርዓቱ ውስጥ ያሉ የማህበረሰቡ እውቀቶች ምንድናቸው?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ፡-

- በብሔረሰቡ የሚፈጠሩ ተደጋጋሚ ግጭቶችን መነሻና የተፈቱበትን ሂደት ያሳያል፣
- በባህላዊ ፍትህ ስርዓት ውስጥ ያሉ እውቀቶችን ለትውልድ ለማሸጋገር ይጠቅማል፣
- በአካባቢው የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለማብረድ የሚሰሩ የመንግስት መዋቅሮችም ሆኑ ማህበራት ከባህላዊ እውቀት በመነሳት ችግሩን እንዲፈቱ ይረዳል፣
- በብሔረሰቡ ላይ በዚህ ዘርፍ ሰፊ ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ አጥኚዎች እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል::

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

በድራሼ ልዩ ወረዳ ኩሱሜ፣ ሞስዬ፣ ማሾሌና ድራሼ የተባሉ አራት ብሔረሰቦች ይኖራሉ፡፡ ይህ ጥናት በድራሼ ብሔረሰብ ላይ ያተኮረ ሲሆን የብሔረሰቡን የግጭት መንስኤዎች እና ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱን ብቻ ይመለከታል፡፡ በወረዳው የድራሼ ብሔረሰብ

በአስራ አንድ ቀበሌዎች ውስጥ የሚኖር ሲሆን ጥናቱ የሚያተኩረው በስድስት ቀበሌዎች ብቻ ነው፡፡ የተመረጡት ቀበሌዎችም  ዋላይቴ፣ ቀያማ፣ ያይቤ፣ ላይኛው አርጉባ፣ ሽሌሌና ጋርዳ ናቸው፡፡ እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡት ለጥናቱ ከሌሎች ብሔረሰቦች አጎራባች ሆነው በተደጋጋሚ ግጭት የሚፈጠርባቸው ቀበሌዎች ስለሆኑና የብሔረሰቡ አባላት በብዛት የሚኖሩባቸው በመሆናቸው ነው፡፡

## 1.7. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

በፎክሎር ጥናት ሁለት ዓይነት የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም ጥናት ማካሄድ እንደሚቻል (Goldstein 1964፣  ፈ.ቃደ 1991) ይገልጻሉ፡፡ እነዚህም የመረጃ ምንጮች ቀዳማይና ካልአይ የመረጃ ምንጮች ሲሆኑ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ከመስክ የሚገኙ መረጃዎች ናቸው፡፡ ካልአይ የመረጃ ምንጭ ደግሞ ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ ጽሑፋዊ ሰነዶች፣ ጥናታዊ ጽሑፎች፣ ታሪካዊ መዛግብቶች ወዘተ የሚያካትት ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ሰብሰብያለሁ፡፡ እነዚህም ዘዴዎች ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት ናቸው፡፡

### 1.7.1.ምልከታ

ምልከታ በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ በመገኘት መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ ይህ ዘዴ በመስክ ላይ ሁኔታዎችን በተፈጥሯዊ ግኝታቸው በማየት፣ በመስማት ወይም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ መሆኑን (Goldstine 1964:77) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም እኔም በተጠኚው ብሔረሰብ ውስጥ በመገኘት ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱን በተፈጥሯዊ መቼት በመመልከት መረጃዎችን ሰብሰብያለሁ፡፡ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በምልከታ ወቅት በቪዲዮ ካሜራ፣ በዲጅታል ድምጽ መቅረጫና በፎቶ ካሜራ በመቅረጽ ነው፡፡ በምልከታም ያገኘዋቸውን መረጃዎች በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት ካገኘዋቸው ጋር በማቀናጀት ተጠቅሚያለሁ፡፡

### 1.7.2 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ መረጃ አቀባዮች ስለተጠየቁት ጉዳይ ሁኔታ፣ድርጊት፣ አመለካከት ገለፃ በማድረግ መረጃ እንደሚሰጡ (Goldstein 1964:77) ይገልጻሉ፡፡ ይህንን ሃሳብ በማጠናከር

ቃለ መጠይቅ ሰዎች ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ የሚያውቋቸውን የተለያዩ ጉዳዮች ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ መሆኑን (ፈቃደ፣1971) ያስረዳሉ፡፡

በዚህ ፅንስ ሀሳብ መሰረት በድራሼ ብሔረሰብ ውስጥ ሰለሚከሰቱ ግጭቶች ዓይነት፣ የግጭት መንስኤዎች፣ ግጭቶች የሚፈቱባቸው ሂደቶችና ተቋማት ወዘተ ውስን፣ ከፊል ውስንና ክፍት  ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ችያለሁ፡፡ ይህም ዘዴ በዚህ ጥናት ውስጥ በሌሎች የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ለመመልከትና ለማግኘት ያልቻልኳቸውን መረጃዎች ለማግኘት አስችሎኛል፡፡

በቃለ መጠይቁም የተሳተፉ የባህላዊ ግጭት አፈታት ሰርዓቱ መሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ በብሔረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ግለሰቦችና ከግጭት አፈታት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተቋማት መሪዎች ናቸው፡፡

### 1.7.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት

የተተኳሪ ቡድን ውይይት ከመስክ መረጃ ለመሰብሰብ ተመራጭ ዘዴ እንደሆነና የቡድን አባላቱም ቁጥር ከ7-12 ሊደርስ እንደሚችል (Mike and Cook:2007) ይገልፃሉ፡፡ ሂደቱም በተመራማሪውና ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል በሚደረግ ምልልስ የሚከናወን ነው፡፡ የተተኳሪ ቡድን ውይይትን በዚህ ጥናት በምልከታና በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ያልተመለሱና እርግጠኛ ያልሆንኩባቸውን ጉዳዮች ለማጥራት ተጠቅሜበታለሁ፡፡ ውይይቱ በሁለት መልክ የተዘጋጀ ሲሆን አንደኛው በባህላዊ የግጭት አፈታቱ በየእርከኑ የመሪነት ሚና ካላቸው 12 ሰዎች ጋር መስከረም 5/2008 ዓ.ም በሆልቴ ቀበሌ የተደረገ ሲሆን ሁለተኛው በግጭት አፈታት ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ካላቸው ሰባት የሀገር ሽግሌዎች ጋር በጊዶሌ ከተማ መስከረም 8/2008 ዓ.ም የተደረገ ነው፡፡

## 1.8. የመረጃ ትንተና ዘዴ

ጥናቱ በድራሼ ብሔረሰብ ባህላዊ ግጭት አፈታት ስርአት ሂደት ላይ የሚያተኩርና የግጭት አፈታት ተቋማቱን እንዲሁም ሂደታቸውን የሚመለከት በመሆኑ ገላጭ ዘዴን ተጠቅምያለሁ፡፡ ይህ ዘዴ ነባራዊ ሁነቶች ያላቸውን ባህርይ በመለየት ለመግለጽ የሚያስችል ዘዴ መሆኑን (Koul, 2006:432) ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት በብሔረሰቡ የሚፈጠሩ ግጭቶች ዓይነትና የአፈታት ሂደታቸውን ለመግለጽ የተሻለ ዘዴ

በመሆኑ ተመራጭ ሆኗል፡፡ በተጨማሪ የይዘት ትንተና ዘዴን ተጠቅሚያለሁ፡፡ ይህ ዘዴ በገለፃ የቀረቡ መረጃዎች የቀረቡበትን አውዳዊ ትርጓሜ ለማየት የሚጠቅም ዘዴ መሆኑን (Miller and Brewer 2003:43) ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም በጥናቱ በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ውስጥ ያሉ የእርቅ ሂደቶችን (ሥርዓቶችን)፣ ዕውቀቶችን ለማሳየት የይዘት ትንተና ዘዴን መርጫለሁ፡፡

## 1.9. የመረጃ ሰጪዎች አመራረጥ

የድራሼ ብሔረሰብን ታሪክ፣ እምነት፣ ባህል፣ በጥልቀት ያውቃሉ የተባሉ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የጎሳ መሪዎች የሃይማኖት አባቶች፣ የቤት እመቤቶች፣ የመንግስት የስራ ሃላፊዎች፣ ነጋዴዎችና ገበሬዎች በድምሩ 23 ሰዎች በመረጃ ሰጪነት በጥናቱ ተሳትፈዋል ከነዚህ ውስጥ ዘጠኙ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡

እነዚህም የመረጃ አቀባዮች የተለዩት የብሔረሰቡን የባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት የሚመሩ፣ የሽምግልና ልምድ፣ ስለ ብሔረሰቡ ባህልና ታሪክ እውቀት ያላቸው በመሆናቸውና በማህበረሰቡ ዘንድ ባላቸው ተቀባይነት ነው፡፡ በተጨማሪም ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶችን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በመፍታት ሂደት ውስጥ ባላቸው ተሳትፎ ነው፡፡ የመረጃ አቀባዮችም እድሜ ከ38-89 ዓመት ሲሆን ጾታም ወንድ 19 ሴት 4 ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡

## 1.10. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

በዚህ ጥናት ሂደት ውስጥ የተለያዩ ችግሮች ገጥመውኛል፡፡ እነዚህም ችግሮች ለጥናቱ የተመረጡ የጎሳ መሪዎች፣ የአገር ሽማግሌዎችና ሌሎች የመረጃ ሰጪዎች በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ምክንያት በውይይቱ ወቅት ያለመገኘት፣ ለጥናቱ የተመረጡ ቀበሌዎች ለትራንስፖርት ምቹ አለመሆንና ወቅቱ ክረምት መሆኑ፣ የብሔረሰቡን ባህላዊ የእርቅ ስርዓት ከተፈጥሯዊ መቼቱ ቀርሶ ለማስቀረት ወደ ስፍራው በተደጋጋሚ መጓዝ ነበረብኝ ይህ ደግሞ ከፍተኛ ወጭን ጠይቋል፡፡በተጨማሪም የጥናቱ ቦታ ከአዲስ አበባ አራት ቀን መፍጀቱና በስፍራው ለበርካታ ጊዜያት መቆየቴ የፋይናንስ አቅሜን ፈትኖታል፡፡

## የተወሰዱ መፍትሔዎች

የመረጃ ሰጪዎቹ በወቅቱ ባይገኙም ተለዋጭ ቀጠሮ በመያዝ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ ምንም እንኳ ቀበሌዎቹ ለትራንስፖርት አመቺ ባይሆኑም ከአንድ ሰዓት እስከ ሁለት ሰዓት በእግር በመጓዝ መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ጥናቱን በረጋ መንፈስ ለመስራት የጊዜ እጥረት አንዱ ችግር ቢሆንም በቢሮ ቆይታዬ ከስራ ሰዓት ውጪ ያሉ ጊዜዎችን መጠቀም እንደ አንድ መፍትሔ ወስጄ ነበር፡፡ ይህ ግን በቂ አልሆነም፡፡ በመሆኑም ለተወሰነ ጊዜ ካለሁበት ስራ መራቅና ከዘወትር የመንፈስ ጉትጎታ ለማረፍ ወሰንኩ፡፡ ይህም ጥናቴን በተረጋጋ መንፈስ እንድሰራ አድርጎኛል፡፡ በዚህም ለጥናታዊ ምርመራ ስራ ጊዜና የተራጋጋ መንፈስ እንደሚያስፈልግ ተረድቻለሁ፡፡ የገንዘብ አቅም ችግሬን ለመፍታት ለጥናቱ የመደብኩትን ገንዘብ በአግባቡ በቁጠባ ተጠቅሜያለሁ፡፡

## 1.11. የመስክ ተሞክሮ

ወደ ድራሼ ወረዳ መረጃ ለመሰብሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ የሄድኩት ሐምሌ 14/2007 ዓ.ም ነበር፡፡ ከሁለት ቀናት ጉዞ በኋላ ወደ ወረዳው ዋና ከተማ ጊደሌ ደረስኩ፡፡ጊደሌ[1] ከተማ በደረስኩ ማግስት በቀጥታ ወደ ወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት በማምራት የወረዳውን ዋና አስተዳደሪ አገኘሁ፡፡ይህንን ያደረኩበት ዋናው ምክንያት በአካባቢው በድንበርና በሌሎች ጉዳዮች ግጭቶች በተደጋጋሚ ስለሚከሰቱና ከወረዳው እውቅና ውጪ ወደ ህብረተሰቡ ዘልቆ ጉዳዩን ለማጥናት መሞከር የተሳሳተ ትርጉም ያሰጣል በሚል ነው፡፡

---

[1] ጊዶሌ የሚለው ቃል ``Giddii Oolle`` ከሚለው የኦሮሚኛ ቃል የተወሰደና ይህም "ህይለኛ ህዝቦች ነን" የሚል ትርጓሜ እንዲይዝ አድርገው በጣሊያን ጦርነት ጊዜ አርበኞች መጠሪያውን እንደሰየሙና በጊዜ ሂደት ``Giddii Oolle`` የሚለው ወደ ``Gidole`` በመለወጥ ለአከባቢው መጠሪያነት ማገልገል መጀመሩን (ፍሬው ተስፋዬ 2012) ይገልጻል፡፡

በዚህም መሠረት ለወረዳው ኃላፊ የመጣሁበትን ዓላማ በዝርዝር አስረዳሁ፡፡በብሔረሰቡ ባህላዊ ግጭት አፈታት ሰርዓት ላይ ለማጥናት መነሳቴን አድንቀው የወረዳው ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ጽ/ቤት ማንኛውንም መረጃ በመስጠት እንዲተባበሩኝ እንደሚያደርጉና ጥናቱ ሲጠናቀቅ አንድ ኮፒ እንዲደርሳቸው አሳስበውኝ በምስጋና ተሰነባበትን፡፡

ከዚህ ቀን በኋላ ባሉ ሁለት ተከታታይ ቀናት የድራሼ ብሔረሰብ ተወላጅ የሆኑና በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይ የሚገኙ ወጣቶችን፣ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎችን በማግኘትና በመተዋወቅ መደበኛ ባልሆነ መንገድ መረጃዎችን መሰብሰብ ጀመርኩ፡፡ በዚህ ሂደት አቶ ይልማ ከተማን እንዲሁም አቶ መለሰ ማሞን አገኘሁ፡፡ እነዚህ ሁለት ግለሰቦች መረጃ እንዴት እንደማገኝ? እነማን ሊሰጡኝ እንደሚችሉ በመለየት እንደሚያግዙኝና ለጥናቱ ወደ መረጥኳቸው ቀበሌዎች አብረውኝ እንደሚጓዙ ቃል ገቡልኝ፡፡ በገቡልኝ ቃል መሠረት መረጃ የሚሰጡኝን ግለሰቦች በጋራ ለየን፡፡ ቀበሌዎቹ በተለያየ ርቀት ላይ የሚገኙ በመሆኑ እንዴትና፣ በምንና መቼ? እንደምንቀሳቀስ ቀጠሮ በመያዝ ከሁለት ቀን ቆይታ በኋላ አቶ ባዩ ዘውዱ የተባሉ ግለሰብን በመጨመር ለጥናቱ ወደ ለየናቸው ቀበሌዎች ተጓዝን፡፡በደረስንባቸው ቦታዎች ሁሉ ለሚገኙ ሽማግሌዎችና ነዋሪዎች ስለመጣሁበት ዓላማና ማንነቴን በማስረዳት አስተዋወቁኝ፡፡

አብዛኛዎቹ ትብብር እንደሚያደርጉልኝ በደስታ በመግለጽ የትኛውንም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኝነታቸውን አሳዩኝ፡፡ መረጃዎች መሰብሰቤን ቀጠልኩ፡፡ ከዚህ በኋላ እነዚህ ግለሰቦች በየገጠሩ ቀበሌዎች ስዘዋወር አብረውኝ በመሆን መረጃ በማፈላለግም ሆነ በመስጠት በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ በተጨማሪ የድራሼና የአሌ ብሔረሰብ ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት እንደሚያደርጉ ይህም ለጥናቱ ጠቃሚ መሆኑን በመጠቆም የእርቅ ሥርዓቱን ከተፈጥሯዊ መቼቱ መመልከትና መቅረጽ እንድችል አግዘውኛል፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያ ዙር የመስክ ቆይታዬ እነዚህንና ሌሎች መረጃዎችን በመሰብሰብ መስከረም 27/2008 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ፡፡

ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ጥናት ቦታው ለመሄድ የወሰንኩት በቀደመው ጉዞዬ ያገኘኋቸውን መረጃዎች ስተነትን አንዳንድ ያልተመለሱ ጥያቄዎችና ክፍተቶች መኖራቸውን በማስተዋሌ ነው፡፡በመሆኑም ሚያዝያ 2/2008 ዓ.ም ወደ ድራሼ ወረዳ ተጓዝኩ፡፡ እንደተለመደው ከሁለት ቀናት በኋላ ጊዶሌ ከተማ ደረስኩ፡፡ ከመጀመሪያው ጉዞዬ በተሻለ

ሁኔታ ወደ መረጃ አቀባዮቼ መቅረብ ችያለሁ፡፡ በመሆኑም በጽሑፍ ያሰፈርኳቸውን የቦታ ስሞች፣ ትርጓሜዎች፣ ስያሜዎችና አንዳንድ ብዥታ የፈጠሩብኝ ጉዳዮች አቶ ካቶ ኩሾን፣ አቶ ብሩ ሰማሎን እና የሀገር ሽማግሌዎችን በድጋሚ ቃለመጠይቅ በማድረግ ግድፈቶችን ለማስተካከል ችያለሁ ፡፡

በዚህ ወቅት በላይኛው አርጉባ በሰው እርሻ ከብቶች ገብተው ሰብል በማጥፋታቸው የሽምግልና ሥርዓት መኖሩን መረጃ በማግኘቴ ሚያዝያ 8/2008 ዓ.ም በሥፍራው በመገኘት ተከታትያለሁ፡፡ ይህም ቀደም ብዬ የሰበሰብኩትን መረጃ የበለጠ አጠናክሮልኛል፡፡ በዚህ ጉዞዬ ቀደም ሲል ትኩረት ያልሰጠኋቸውን ምስሎች በፎቶ ካሜራዬ በመቅረጽ ለመረጃ ትንተናዬ ተጠቅሜበታለሁ፡፡ በተጨማሪ በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ያሉ ጽሑፋዊ መረጃዎችን ቀደም ባለው ጉዞዩ በተለያዩ ምክንያቶች ማግኘት አልቻልኩም ነበር፡፡በዚህ ወቅት ስለ ድራሼ ወረዳና ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ስለተፈጠሩ ግጭቶች ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ችያለሁ፡፡እነዚህን መረጃዎች በማሰባሰብ ሚያዝያ 22/2008 ዓ.ም የመስክ ቆይታዬን አጠናቅቄ ተመልሻለሁ፡፡

## 2. የድራሼ ብሔረሰብ ዳራ

በዚህ ክፍል የድራሼ ብሔረሰብ አጠቃላይ ማህበረ-ባህላዊ ገጽታ ይቀርባል፡፡ በዋነኝነትም ብሔረሰቡ የሚኖርበት መልክአ ምድር፣ የማህበረሰቡ ባህላዊ ዳራ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ እንዲሁም የብሔረሰቡ ባህላዊ እሴቶች በየፈርጃቸው ይቀርባሉ፡፡

### 2.1. መልክአ ምድራዊ ገጽታ

የድራሼ ወረዳ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በሰገን[2] አካባቢ ህዝቦች ዞን ከሚገኙ አራት ወረዳዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የወረዳው ዋና ከተማ ‹‹ጊዶሌ›› ተብላ የምትጠራ ስትሆን ከተማዋ የተመሰረተችው ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1936-1941 ባለው ዘመን እንደሆነ (ሐንሳሞ፣1993) ያስረዳሉ፡፡ የድራሼ ወረዳ[3] ከክልሉ ዋና ከተማ ሀዋሳ 330 ኪ.ሜ፣ ከአዲስ አበባ ደግሞ 598 ኪ.ሜ፤ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡የድራሼ ወረዳን በደቡብ የኮንሶና የአሌ፣ በምስራቅ የአማሮ ወረዳ፣ በሰሜን የጋሞጎፋ ዞን/አርባምንጭ ዙሪያ/፣ በምዕራብ የአሌ(ዶበሴ) ወረዳዎች ያዋስኑታል፡፡

ይህ ወረዳ ከባህር ወለል በላይ ከ1.235 እስከ 2.561 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ የማዕከላዊ እስታትስትክስ ኤጀንሲ መረጃ እንደሚገልጸው አጠቃላይ የድራሼ ህዝብ ቁጥር 71,181 ሲሆን ከዚህም ውስጥ 49% ሴቶችና 51% ወንዶች እንደሆኑ ያሳያል፡፡ ከዚህ አጠቃላይ የህዝብ ቁጥር 91% በገጠር የሚኖሩ ሲሆን 9% ደግሞ ከተማ የሚኖሩ መሆናቸውን ይጠቁማል፡፡ የድራሼ ወረዳ ሶስት ዓይነት የአየር ፀባይ ያለው ሲሆን ከአጠቃለይ የአካባቢው የቆዳ ስፋት ቆላ 40 % ወይና ደጋ 35%፣ ደጋ 25% ይሸፍናሉ፡፡(ማ.እ.ኤ፣ 2007)

---

[2]የሰገን አካባቢ ህዝቦች ድራሼን ኮንሶን፣ አማሮንና የቡርጂ ልዩ ወረዳዎችን አንድ ላይ በማጣመር በአንድ የዞን አስተዳደር ውስጥ በማዋቀር እንደ አዲስ የተመሰረተ ዞን ነው፡፡ የሰገን አካባቢ ህዝቦች የሚለው ስያሜ በአካባቢው ከሚገኘው ሰገን ተብሎ ከሚጠራው ወንዝ የተወሰደ ነው፡፡

[3]ወረዳ ራሱን የቻለ ፓለቲካዊና አስተዳደራዊ የመንግስት አወቃቀር ሲሆን ተጠሪነቱ በቀጥታ ለዞኑ አስተዳደር እንደሆነ SNNPRS የክልሉ ህገ- መንግስት 2001 ያስረዳል፡፡

እንደ አየር ፀባዩ ሁሉ አካባቢው በከፍተኛ ተራራ፣ ረባዳማና ሜዳማ በሆኑ የመልክአ ምድር ገጽታዎች የተከበበ ነው፡፡ በተለይ ተራራማው ክፍሉ ‹‹ጋርዱላ›› በመባል የሚታወቅ ሲሆን የአፄ ምኒሊክ ሰራዊት ለመጀመሪያ ጊዜ የጦር ምሽግ የሰራበት በኋላም አካባቢውን ለመግዛት ‹‹ጋርዱላ አውራጃ›› በመባል እንደ ማዕከላዊ መቀመጫ ያገለገለ ቦታ ነው (ሐንሳሞ ሐመላ፣ 1993)፡፡

## ስዕል 1 የድራሼ ወረዳ ካርታ




ምንጭ፡- የወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት

## 2.2. የብሔረሰቡ አመጣጥ አፈ ታሪክ

የድራሼ ብሔረሰብ[4] ታሪክ ከአካባቢው ከሚኖሩ ህዝቦች ታሪክ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ በተለይ በስተምስራቅ ከሚያዋስነው ከኮንሶ ህዝብ ጋር በቋንቋ፣ በባህልና በአኗኗር ዘዴ አንድም ሁለትም ናቸው የሚያሰኝ ነው፡፡ የብሔረሰቡን ጥንተ አመጣጥ አፈ ታሪክ አቶ ታደሰ ተሸባሌ እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ፡-

> «ካላ» እና «ቲቲፓ» የተሰኙ ወንድማማቾች ነበሩ፡፡ እነዚህ ወንድማማቾች እጅግ የሚፎካከሩና ሁሌም በባላንጣነት ይኖሩ ነበር፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይህ የባላንጣነት መንፈስ እየፀና ሲመጣ እስከ መቼ እንዲህ ሆነን እንኖራለን በሚል አንድ ስምምነት ላይ ይደርሳሉ፡፡ ይኸውም ወደ አንድ ከፍታ ቦታ በመሄድ የሀገሩን ስም በመጥራት ምድሪቱ ቀድማ መልስ የሰጠችው በዚህም እንዲቆይ፤መልስ ያልሰጠችው ደግሞ ወደ ሌላ ምድር እንዲሄድ ተስማሙ፡፡ በስምምነታቸውም መሠረት ሁለቱም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የምድሪቱን ስም ጠሩ፡፡ ምድሪቱም ለ «ካላ» ቀድማ መልስ ሰጠች፡፡ «ቲቲፓ»ም መልስ ስላላገኘ ስምምነታቸውን በማክበር አካባቢውን ለቆ ወደ ደጋማው ሥፍራ ተሰደደ፡፡ «ካላም» በዚያው ቀረ፡፡ ቲቲፓ ይኸው ዛሬ ለድራሼ ህዝብ እዚህ ማረፍ ምክንያት ሆነ (ቃለ መጠይቅ፣ ታደሰ ተሸባሌ፣ ጊዶሌ፣ መስከረም 3/2008)፡፡

ይህንን በብሔረሰቡ የሚነገረውን አፈ ታሪክ በሌላ መልኩ በቡድን ውይይት ወቅት የነበሩ የብሔረሰቡ ተወላጆች እንዲህ ሲሉ ገልጸውልኛል፡-

> ሁለት ወንደማማቾች ማለትም ካላና ቲቲባ ለኑሮአቸው አመቺ ቦታ ሲፈልጉ ከቦረና ተነስተው ኮንሶ እንደደረሱና ኮንሶ ውስጥም የቤተሰቦቻቸው ቁጥር በመጨመሩና አካባቢውን ከሁለት አንዱ እንዲለቅና ሌላው የግሉ ማድረግ እንዳለበት ስለተማመኑ ለዚህም ማን መሄድ እንዳለበት የመሬት ምስክርነት እንደፈለጉ ይነገራል፡፡

---

[4] የድራሼ ብሔረሰብ ስያሜ ለድራሼ ብሔረሰብና ለሚኖርበት አካባቢ መጠሪያ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን "ድራሼ" እና "ጊዶሌ" ለአካባቢ መጠሪያነት አንዱ ሌላዉን በመተካት እንደሚያገለግሉ የማዕከላዊ እስታቲስቲክስ መረጃ ኤጀንሲ 2007 ይገልጻል፡፡

> በዚህም መሰረት መሬት የመሰከረችለት ማለትም ህዝብ በተሰበሰበበት መሬትን "አንቺ መሬት" ብለው ሲጠሯት " አቤት ካለች" አቤት ያለችው ሰው የመሬቱ ባለቤት እንደሚሆንና ሌላውም ለእርሱ አስረክቦ መሄድ እንዳለበት ተወሰነ በዚሁ መሰረት ሁለቱ ወንድማማቾች ለውድድር ቀረቡ፡፡ ነገር ግን ከእነርሱ አንደኛው "ካላ" የተባለው ድርጊቱ ከሚካሄድበት ቦታ አንዲት ሴት ጉድጓድ ቆፍሮ በውስጡ ደብቋት ሲጠራት አቤት እንድትል መክሮ ስላስቀመጣት ወንድምየው ቲቲባ ሲጣራ ዝም ብላ ካላ በጠራ ጊዜ ግን "አቤት" በማለቷ ካላ አሸናፊ ሆኖ የኮንሶን ምድር ከነ ቤተሰቡ ይዞ ሲቀር ቲቲባ ዛሬ ድራሼ ተብሎ ወደሚጠራው ምድር ተሰደደ፡፡ ቲቲባ ከኮንሶ ለቆ በመጀመሪያ ቱሮ ወደተባለ ቆላማ ክፍል ሲያመራ አየሩ ለኑሮ አመቺ ሆኖ ስላላገኘው ወደ ደጋው ክፍል ወጥቶ ማሾሌ ላይ ሰፈረ፡፡ እዚያም ሆኖ ሲመለከት ከፍተኛ ቦታ በሩቁ ስላየ ወደዚያው በመገስገስ "ጥሊሎ" ወይም "ጋርዱላ" ከተባለ ቦታ ደርሶ ኑሮውን መሰረተ፡፡ ይህ ቦታ አሁን ድራሼ ተብሎ የሚጠራው ስፍራ ነው ( የቡድን ውይይት፣ ያይቤ መስከረም 5/1/2008)፡፡

ከሁለቱ አፈ ታሪኮች እንደምንረዳው የድራሼና የኮንሶ ህዝቦች ከአንድ ሐረግ የሚመዘዙ ቤተሰቦች መሆናቸውን ዛሬም ድረስ የሁለቱን ህዝቦች ቋንቋ ባህልና የአኗኗር ዘዬ አጥብቆ ለመረመረ የሚያሳምን ይመስላል፡፡

## 2.3 ከታሪክ መዛግብት አንፃር

የድራሼ ብሔረሰብን ከየት መጣነት? ጥናት ያደረጉ ምሁራን የተለያዩ መላ ምቶችን ይሰነዝራሉ፡፡ አብዛኛዎቹ ምሁራን በዙሪያው ከሚኖሩ ብሔረሰቦች ወይም ጎሳዎች ጋር በማዛመድ መላምቶችን ሰጥተዋል፡፡

ጄህረሰን የተባሉ ፀሐፊ "ጋርዱላዎች" ወይም ድራሼዎች የባንቱ ዝርያ እንዳላቸው መግለጻቸውን (ሐንሳሞ፣ 1993) ያስረዳሉ፡፡ Black (1973) ደግሞ "Gidole (D'rashe) came originally from Konso" በማለት ይገልጻሉ፡፡

በሌላ መልኩ የኮንሶ ባህልና ቋንቋ ላይ ጥናት ያደረጉ Hallpike (1972) "ድራሼን ጨምሮ በዙሪያው የሚገኙ ህዝቦች ባህልና ቋንቋቸው ከኦሮሞ ባህልና ቋንቋ ጋር የሚዛመድና በእጅጉ የሚመሳሰል በመሆኑ ከአንድ ዝርያ የመጡ ናቸው ይላሉ፡፡"

ሐንሳሞ ሐመላ ደግሞ የድራሼ ብሔረሰብ ከዛሬው ኬንያና ሱማሌ ጋር ከሚዋሰነው ቦረና በኩል "ሳባር" ወይም "ሳፔር" ከተባለ ቦታ በመምጣት በሊበን በኩል አልፈው ዛሬ ድራሼ ከሚገኝበት ሥፍራ እንደደረሱ ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም በጊዜ ሂደት ከተለያዩ ቦታ ከ16ኛው ምዕተ ዓመት በፊት የፈለሱ ጎሳዎች ድብልቅ መሆናቸው ያስረዳሉ (1993፣39-42)፡፡

ሐንሳሞ ይህን መላምት ሲገልጹ በብሔረሰቡ የሚነገሩ አፈ ታሪኮችንና በየዘመኑ የድራሼ ብሔረሰብ መሪዎች ነበሩ የሚሏቸውን የጎሳ መሪዎች ታሪክ በመግለጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ድምዳሜው ቃላዊ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው ከኦሮሞ ቦረና እንዲሁም ኮንሶ መጣ የሚለውን የሚቃረን አይደለም፡፡ ይህንንም ሀሳብ አብዱልፈታ አብዲላህ «የኮንሶ ህዝብ ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ ከጎረቤት ብሔረሰቦች ጋር የተሳሰረና የተቆራኘ ነው፡፡ <u>በተለይም ከቦረና ኦሮሞ፣ ከአሌና ከደራሼ ብሔረሰቦች ጋር የታሪክ፣ የባህል፣ የቋንቋና የአኗኗር ግንኙነቶችና አንድነቶች እንዳሉት ይነገራል</u>» (2006፣ 28) በማለት ይገልጹታል፡፡ሰረዙ የእኔ ነው ፡፡

ከላይ ስለ ድራሼ ህዝብ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የተገለጹ ሀሳቦች የኮንሶ፣ የቦረናና የድራሼ ህዝቦች የባህል፣ የቋንቋና የታሪክ ተመሳስሎ እንዳላቸው ከመግለጽ ውጪ የድራሼ ህዝብ ከየት መጣነት ሳይንሳዊም ሆነ ታሪካዊ መረጃዎችን በማቅረብ የሚገልጹ አይደሉም በመሆኑም የድራሼ ህዝብ ታሪክና ትውፊት ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ መስክ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.4 የብሔረሰቡ ቋንቋ /ዲራይታት/

የድራሼ ብሔረሰብ ቋንቋ ‹‹ዲራይታት›› ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ ቋንቋ የብሔረሰቡ አፍ መፍቻ ቋንቋ ነው፡፡ የብሔረሰቡ አባላት ከዚህ ቋንቋ በተጨማሪ ኦሮምኛ፣ ዶርዝኛ፣ ኮንሶኛና አማርኛን ይናገራሉ፡፡

የድራሼ ቋንቋ ‹‹ዲራይታት›› በስነ-ልሳን ጥናቶች ትንታኔ ከጥንቱ ቆላማው ምስራቃዊ ኩሽቲክ ቋንቋዎች ጋር እንደሚዛመድ (Bender 1969)፣ (Black 1973)፣ (Hayward,1980)፣ (Wondwosen፤2006) ይገልፃሉ፡፡ ‹‹የድራሼ ቋንቋ ምድብ፣ ኩስሜ፣ ሞስዬ ወይም ቡሳ እንደሆነና በባህል ረገድ ድራሼዎች ኦሞቲክ ቋንቋ ይናገሩ ከነበሩት ጥንታዊ ሕዝቦች ጋር የጠበቀ ዝምድና እንዳላቸው (ሐንሳሞ፣1993፣21) ያሰረዳሉ፡፡ ቋንቋው ከመግባቢያነት አልፎ የትምህርትና የጽሁፍ ቋንቋ አልሆነም፡፡

## 2.5 እምነት (ኃይማኖት)

በድራሼ አካባቢ የፕሮቴስታንት፣ ኦርቶዶክስና የሙስሊም እምነት ተከታዮች ይገኛሉ፡፡(ማ.እ.ኤ፣ 2007) እነዚህ እምነቶች በተለያዩ የታሪክ ሂደቶችና ክስተቶች ወደ አካባቢው እንደገቡ ቃላዊ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ እነዚህ እምነቶች ወደ አካባቢው ከመግባታቸው በፊት የብሔረሰቡ አባላት በባህላዊ እምነት (ቃልቻ) ያምኑ እንደነበረ ይነገራል፡፡ ይህንን ባህላዊ እምነት የሚከተሉ የብሔረሰቡ አባላት አሉ (አቶ ይልማ ከተማ፣ መስከረም 4/2008)፡፡

ወደ አካባቢው ከገቡ ከሶስት እምነቶች ቀዳሚው የኦርቶዶክስ እምነት እንደሆነ ሐንሳሞ እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ፡-

> ፊታውራሪ ወልዴ ካስመጧቸው አዳዲስ ክስተቶች አንደኛው የቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት ወደ ‹‹ጋርዱላ››ከተማ ማስገባታቸው ነበር፡፡ ከርሳቸው በፊት የነበሩ ማናቸውም ገገሮች ያላደረጉት ነበር፡፡ በመሆኑም ክርስትና ወደዚህ አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ የገባው በፊታውራሪ ወልዴ ነበር ማለት ነው (1993፣ 124)፡፡

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የኦርቶዶክስ ኃይማኖት ወደ አካባቢው የገባው ከሀገሪቱ የታሪክ ሂደት ወይም ለውጥ ጋር ተዛምዶ መሆኑን ነው፡፡ የአፄ ምኒሊክ የአስተዳደር መዋቅር በአካባቢው መስፈኑ እምነቱም ወደ ድራሼ አካባቢ እንዲገባ ምክንያት ሆኗል፡፡ በድራሼ ወረዳ ዋና ከተማ ጊዶሌ በስተ-ደቡብ በተለምዶ ገብርኤል ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የገብርኤል ቤተ-ክርስቲያንም ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ሁለት ቤተክርስቲያናት በተጨማሪ በወረዳው ከተማ ‹‹ጊዶሌ›› አንድ መስጊድ አለ፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮችም በቁጥራቸው እጅግ አነስተኛ መሆናቸው ይነገራል፡፡ እነዚህ

ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑትም የእስልምና እምነት ተከታዮች የአካባቢው ተወላጆች ሳይሆኑ ከወሎ፣ ከጎጃምና ከሌሎች አካባቢዎች ፈልሰው የመጡ ነዋሪዎች ሲሆኑ የአካባቢው ሰዎች ‹‹አማሮች›› ብሎ ይጠራቸዋል (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ታደሰ ተሸባሌ፣ 3/2008)፡፡

በድራሼ አካባቢ 50.03% የፕሮቴስታንት እምነት፣ 34.27% የኦራቶዶክስ እምነት ተከታይ 12.84% ባህላዊ እምነትን እንደሚከተሉ (የማዕከላዊ እስታቲስቲክስ መረጃ ኤጀንሲ 2007) ይገልጻል፡፡ በአሁን ጊዜ በድራሼ ገጠራማ ቦታዎች ሁሉ የፕሮቴስታንት እምነት የአምልኮ ቦታዎች ተስፋፍተውል (ቃለ መጠይቅ፣ አቶይልማ ከተማ መስከረም 2/2008)፡፡

## 2.6 የብሔረሰቡ መተዳደሪያ

የድራሼ ብሔረሰብ ዋንኛ መተዳደሪያው እርሻ[5] ነው፡፡ የእርሻ ስራውን የሚያከናውነው ‹‹ፓውራ›› በተሰኘ ባለሁለት አፍ የዕጅ መሳሪያ ነው፡፡ በበሬ ማረስ አልፎ አልፎ የሚታይ እንጂ በቀዳሚ የእርሻ መሳሪያነት የሚጠቀስ አይደለም፡፡ ይህን መሳሪያ በመጠቀም በቆሎ፣ ማሽላ፣ ጤፍ፣ ስንዴ የመሳሰሉት የእህል ዘሮችን ያመርታል፡፡ ብሔረሰቡ አብዛኛውን የእርሻ ስራ የሚያከናውነው በቡድን ነው፡፡ ይህን የእርሻ ስራ ከመጀመሩ በፊት ከብት በማርባት ይተዳደር እንደነበረ ይነገራል፡፡ አሁንም ከእርሻው ስራ ጎን ለጎን ከብት ማርባትና ማደለብን እንደ አንድ የገቢ ምንጭ ይጠቀሙበታል፡፡ የእርሻ ስራውንም ሆነ የከብት እርባታው 85 በመቶ የሚከናወነው በቆላማው የአካባቢ ስፍራ ነው፡፡

የድራሼ ብሔረሰብ  ሶስት ሀገር በቀል /Indigenous/ የእርሻ ጥበብ አለው፡፡ የአፈርና ውሃ ጥበቃ፣ የእህል ዘርን ለረጅም ጊዜ ማቆየትና የእርሻ ስራውን የሚያከናውንበት ባህላዊ የቀን /ወቅቶች/ መቁጠሪያ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በተለይም የአካባቢውን የአፈር መሸርሸር ለመግታት የእርከን ስራ በመስራትና አፈራርቆ በመዝራት ‹‹ታሪጋ›› እና ‹‹ፓታይ›› በተባለ ባህላዊ የአፈር ጥበቃ ዘዴ ምርቱን ያመርታል፡፡ ያመረተው ምርት እንዳይበላሽ ‹‹ፓውላ›› የተሰኘ የእህል ጥልቅ ጉዳጓድ በመቆፈር እንደነተራ ምርቱን እዚህ ጉድጓድ ውስጥ በመክተት ለረጅም ጊዜ ያቆየዋል፡፡ ምርቱ ከአመታት በኋላ እንኳ ቢወጣ አይበላሽም (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ መሰለ ማሞ፣መስከረም 7/2008)፡፡

---

[5]የእርሻ ስራውን ብሔረሰቡ የሚያከናውነው በቆላማው የአካባቢው ስፍራዎች ሲሆን ዋነኛ መኖሪያው ደጋማው የአካባቢው ቦታ ነው፡፡ በመሆኑም ወደ ቆላማው የእርሻ ቦታ ለመሔድ ከአንድ እስከ ሁለት ሰዓት በእግር መጓዝ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንንም የእግር ጉዞ በቡድን የሚያደርግ መሆኑን በመስክ ቆይታዬ መመልከት ችያለሁ፡፡

የድራሼ ብሔረሰብ የእርሻ ስራውን የሚያከናውነው በራሱ የቀንና የወራት መቁጠሪያ ዘዴ ነው፡፡ በተለይም ዝናብ[6] የሚጥልባቸው ወቅቶችን በሚገባ በመለየት እርሻውን ያከናውናል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማህበረሰቡ በቆላማውና በደጋማው አካባቢ የጫት ተክል በመትከል የግብርና ስራውን ገንዘብ ተኮር በማድረግ ወደ ንግዱ ዘርፍ የመግባት አዝማሚያ ይታይበታል፡፡ ይህ የጫት ምርት በስፋት እየተመረተ ወደ አርባ ምንጭ፣ ሀዋሳ እና አልፎ አልፎ ወደ አዲስ አበባ ይላካል፡፡

## 2.7 ጋብቻ

የድራሼ ብሔረሰብ በዘጠኝ ጎሳዎች የተከፈለ ሲሆን የጋብቻ ባህሉም በጎሳዎቹ ዝምድና ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እነዚህ ጎሳዎች ጥብቅ የደምና የሥጋ ዝምድና እንዳላቸው ያምናሉ፡፡ በአካባቢው የሚኖሩ የማሹሌ፣ ሞስዬ፣ ዶባሌ/አሌ/፣ ኩሱሜ፣ ኮንሶ እና ድራሼ በጎሳ ደረጃ ከ‹‹አርጋማይት››ጎሳ የሚመደቡ ናቸው፡፡ የአንድ ቤተሰብ(ወገን) አባላት ናቸው ተብሎ ስለሚታመን በነዚህ መካካል ጋብቻ አይፈፀምም፡፡ በብሔረሰቡ የእያንዳንዱ ጎሳ ዝምድና (የዘር ቆጠራ) የሚደረገው በወንዱ በኩል ስለሆነ ጋብቻ የሚፈፀመው ከሌላ ጎሳ ከምትወለድ ወይም ከሚወለዱ ሴትና ወንድ ጋር ብቻ ይሆናል፡፡

በብሔረሰቡ እንዲህ አይነቱ የጋብቻ ትስስር ፋይዳው ላቅ ያለ መሆኑን አቶ ብሩ ሰማሎ እንዲህ ሲሉ ይገልፃሉ፡-

> ማንኛውም ሁኔታ በሁለት ጎሳዎች መካከል የሚፈጠር ግጭት ወይም አለመግባባት መንስሄ ከአንዱ ጎሳ አባል ወይንም አባሎች ውጪ ስለማይሆን ማህበረሰቡ በሁለት በደምና በሥጋ በተዋሀዱ ቤተሰቦች መካከል እንደተፈጠረ ግጭት ስለሚወሰድ ችግሩን ለማብረድና መፍትሄ ለማምጣት ይሯሯጣል እንጂ አያባብስም፡፡ ምክንያቱም በግጭት ውስጥ ወይ ወንድም አሊያም የእኅት ልጅ ይገኛል (ቃለ መጠይቅ ፣ መስከረም4፣ 2008)፡፡

---

[6] ዝናብ የሚዘንበው ‹‹ ሞሐ›› እና ‹‹ምስናታ›› የተባሉ ከዋክብት በሚያደርጉት ወስባዊ ተራክቦ ዝናብ እንደሚዘንብ ብሔረሰቡ እንደሚያምን (ፍሬው፣ 2011) ይገልፃል፡፡ ዝናብ በአካባቢው ካልዘነበ ሴቷ ኮከብ ወሲባዊ ተራክቦ ለማድረግ ፈቃደኛ እንዳልሆነችና እንደተቆጣች ይታመናል፡፡

በድራሼ ብሔረሰብ ባህል ሶስት የጋብቻ አይነቶች አሉ፡፡እነዚህም የውርስ ጋብቻ (ዳሃላ) ፣ የጠለፋ ጋብቻ (ሎህላ)፣ የመተጫጨት ጋብቻ (ራቦት) እንደሚባሉ (ሀንሳሞ 1993) ይገልጻሉ፡፡

__ዳሃላ (የውርስ ጋብቻ )፡-__ የሚፈፀመው ታላቅ ወንድም ሲሞት ታናሽየው የወንድሙን ሚስት በውርስ ያገባታል፡፡ ይህ የውርስ ጋብቻ የሚፈፀመው የወንድሙን ሀብትና ንብረት ወደ ሌላ ወገን እንዳይሄድና የሟች ልጆች በሌላ ወገን እንዳይበደሉ ከሚል እምነት የመነጨ ነው፡፡ በባህሉ ታላቅ የታናሽን ሚስት በውርስ ጋብቻ አያገባም፡፡

__ሎህላ (የጠለፋ ጋብቻ) ፡-__ ይህ የጋብቻ አይነት በብሔረሰቡ በእጅጉ የተለመደ ነው፡፡ እንደ አንድ ባህል የሚታይ ነው፡፡ ይህ የጋብቻ ባህል የብሔረሰቡን አስተዳደርና መንፈሳዊ መሪ ለሚባሉት ለዳማ፣ ለፖልዳና፣ ለሼላ የተፈቀደ አይደለም፡፡ ክብራቸውን ያዋርዳል ተብሎ ስለሚታሰብ በመተጫጨት የጋብቻ አይነት እንዲያገቡ ይደረጋል፡፡ በዚህ የጋብቻ ሂደት ልጅቱ ከተጠለፈች በኋላ ከጠላፊው ወገን አንዱ ቤተሰብ ጋር እንድትቀመጥ ተደርጎ የልጅቱ ፈቃደኝነት ይጠየቅና ጉዳዩ በሽምግልና እንዲያልቅ ይደረጋል፡፡

__ራቦት (የመተጫጨት ጋብቻ)፡-__ይህ የጋብቻ አይነት እንደ ማንኛውም የአካባቢ ልጅ ልጅቱን ከወደዳት በገበያ፣ በእርሻ ቦታና በልዩ ልዩ ማህበራዊ የግንኙነት ቦታዎች ልጅቱን በማፈላለግ ስሜቱን ይገልፅላታል፡፡

የልጅቱን ፈቃደኝነት አይቶ በብሔረሰቡ አጠራር ራቦት ተብሎ የሚጠራውን የአንገት፣ የእግር የጆሮ ጌጣጌጦች[7] ስጦታ ይሰጣታል፡፡ ፍቅራቸውም ሲጠና በቤተሰብ ፈቃድ ጎጆ ወደ መመስረት ያመራሉ፡፡

በድራሼ ብሔረሰብ የጋብቻ ባህል ውስጥ ዘር ከማስቀጠልና የህይወት አጋርን ከማግኘት ያለፈ ትርጉም እንዳው ይታመናል፡፡ በተለይ የ‹‹ዳማ››፣ «የሼላ»፣ የ«ፓልዳ» የጋብቻ ትስስር ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትርጓሜን ይይዛል፡፡

[7]ጌጣጌጦቹ የሴቷ ባል ወይም ቤተሰብ ያለውን ሀብት ማሳያ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ በጋቢቻው እለት የሚሰጣት የእጅም ይሁን የአንገት ጌጣጌጦች የአግቢውንና ቤተሰቡን የሀብት መጠን የሚያሳይ በመሆኑ የልጅቷ ዘመድ አዝማድ “ብረት መዝጊያ አማች” አመጣሽልን የሚል ክብርና ሙገሳ ይሰጧታል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው በድራሼ ብሔረሰብ ከተመሳሳይ ጎሣ አባል ጋር ጋብቻ መፈጸም አይቻልም፡፡ በመሆኑም ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር መሪዎች ከሌላ ብሔረሰብ በማህበራዊ መሠረት አቻ ከሆኗቸው የጎሳ መሪዎች ጋር ሊጋቡ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ በአካባቢው የሚፈጠሩ ግጭቶችን ወይም አለመግባባቶችን ሠላማዊና ቤተሰባዊ በሆነ መንገድ ለመፍታትና የመሪነት ስልጣናቸውን በፅኑ መሰረት ላይ ለመጣልና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ያስችላቸዋል፡፡

ሌላው በጋብቻ ሂደት ውስጥ በብሔረሰቡ ከማህበራዊ መሠረት በመነሳት ጋብቻን የሚከለክል ባህል አለ፡፡ በዋነኝነት በብሔረሰቡ የጥበበ ዕድ ሰራተኞች (ሸክላ ሰሪ፣ ብረት አቅላጮች) እና ሌሎች በጥበበ ዕድ ሥራ ላይ የተሰማሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ከሌሎች ጎሳዎች ጋር መጋባት አይችሉም፡፡ እነዚህ ሐውዳ በመባል የሚጠሩ ሰዎች የተናቁ፣ የተጠሉና የሞተ ከብት ስጋ የሚበሉ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህም ምክንያት ከሌሎች ጋር አብሮ የመብላት፣ የመጠጣትና የመገበያየት ዕድል የላቸውም፡፡ ለቅሶ እንኳ ቢደርሱ ከሰው ሁሉ ራቅ ብለው ይቀመጣሉ፡፡ የትኛውም መጠጥ ቤት በራሳቸው ዕቃ እንጂ ሌላው ሰው በሚጠጣበት የመጠጥ ዕቃ አይሰጣቸውም፡፡ በተመሳሳይ ‹‹ዋሎት›› (ማኪያ) የሚባሉት የቀብር ስነ-ስርዓት አስከባሪዎች እንደ ‹‹ሐውዳ›› ሁሉ የተገለሉና ከፈለጉት የጎሳ አባል ጋር ጋብቻ እንዲያደርጉ ባህሉ አይፈቅድም (ቃለ መጠይቅ፣ ታደሰ ተሽባሌ፣ መስከረም 3/2008)፡፡

## 2.8 የብሔረሰቡ ማህበራዊ አደረጃጀት

የአንድን ማህበረሰብ ማህበራዊ አደረጃጀት በሚገባ ማጤን ማህበረሰቡ የሚከተላቸው አስተዳደራዊና ማህበራዊ የፍትህ መዋቅሮችን ለመረዳት መንገድ ይከፍታል፡፡ በዚህም መሰረት የድራሼ ብሔረሰብ በዘጠኝ ጎሳዎች እንደሚከፈል ቀደም ሲል ተጠቅሷል፡፡ በእነዚህ ዘጠኝ ጎሳዎች ውስጥ የሚገኙ የብሔረሰቡ አባላት ከማህበራዊ መሰረታቸው አንፃር በአራት ይከፈላሉ፡፡ እነዚህም፡- **ሀልቶት፣ ሐውዳ፣ ዋሎት/ማኪያ/ እና ኤታንት** በመባል ይጠራሉ፡፡

የብሔረሰቡ አባላት በእነዚህ ማህበራዊ አደረጃጀቶች መሰረትነት አጠቃላይ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ማህበራዊ አደረጃጀቶች

በብሔረሰቡ ውስጥ ለሚደረጉ ማናቸውም ክንውኖች መሰረት ናቸው (ቃለ መጠይቅ፣ ታደሰ ተሸባሌ፣ ጊዶሌ፣ መስከረም 3/2008)፡፡

**ሀ)** <u>**ሀልቶት፡-**</u> በዚህ የማህበራዊ አደረጃጀት የሚታቀፉ ከዘጠኙ ጎሳዎች ታላላቅ የሚባሉና በፖለቲካዊም ሆነ በእምነት መሪነት ውስጥ ያሉ ሲሆኑ በዚህም አደረጃጀት ውስጥ ዳማው /ንጉሱ/፣ ፓልዳ/የጎሳ መሪ/ ሼላ እና ሻና ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በእነዚህ ማዕቀፍ ውስጥ የዳማው ቤተሰቦችና የሌሎች የእምነት መሪ ወገኖችና ዘሮች በዚህ ውስጥ ይካተታሉ፡፡

ይህ ማህበራዊ አደረጃጀት በመንደር ተከፋፍሎ የምናገኘው አይደለም፡፡ በመሆኑም ለማህበራዊ አደረጃጀቱ የጎሳው ጥንተ ታሪክ፣ ስልጣንና የዘር ሐረግ ለማህበራዊ ማንነቱ ምድብ መሠረት ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

**ለ)** <u>**ሀውዳ፡-**</u> ይህ የብሔረሰቡ ክፍል በእጅ ጥበብ ሥራ የተሰማሩትን የሚመለከት ነው፡፡ የሽመና ሰራተኞች፣ ብረት አቅላጮች (ማጭድ፣ ቢላዋ፣ ማረሻ)፣ የቆዳ ስራ የሚሰሩ፣ ሸክላና የሸክላ ውጤቶችን የሚያመርቱ ባለሙያዎች በዚህ ክፍል የታቀፉ ናቸው፡፡

በብሔረሰቡ ‹‹ሐውዳ›› የሚባሉት በማህበራዊ ሆነ አስተዳደራዊ መዋቅሮች ላይ የማይሳተፉ፣ ዝቅ ተደርገው የሚታዩና የተገለሉ ናቸው ፡፡ በልዩ ልዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች እንደ ሠርግ፣ ለቅሶ፣ ዕድር በመሳሰሉ ክንውኖች ለብቻቸው እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡ ምግብም ሆነ መጠጥ ሲሰጣቸው በራሳቸው ዕቃ እንጂ ሌሎች በሚጠቀሙባቸው ቁሳቁስ መጠቀም አይፈቀድላቸውም፡፡ የዚህ ምክንያቱ የሞተ ከብት ወይም እንስሳ የሚበሉ በመሆኑ የረከሱ ናቸው ስለሚባል ነው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ካቶ ኩሾ፣ መስከረም 6/2008)፡፡

**ሐ)** <u>**ዋሎት /ማኪያ/፡-**</u> በድራሼ ብሔረሰብ ባህል እያንዳንዱ ጎሳ የቀብር ሥርዓት እና አፈፃፀም አለው፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ ይህንን ሥርዓት የሚያከናውኑት ዋሎት (ማኪያ) በመባል ይጠራሉ፡፡ እነዚህም አንድ ሰው ከመሞቱ በፊትና በኋላ ያሉ ሥርዓት አምልኮኦችን የሚጠብቁና የሚፈጽሙ ናቸው፡፡ በድራሼ ብሔረሰብ ባህል መሰረት አንድ ዳማ ወይም ፓልዳ ቢሞት ሬሳው እስኪቀበር ድረስ ለሁለትና ለሶስት ወራት የመቆየት ልምድ እንዳለ ይገለፃል፡፡ ይህንን ተግባር የሚፈጽሙት ዋሎት (ማኪያ) በመባል የሚታወቁት ናቸው፡፡

*መ)* ***ኤታንት፡-*** የዘጠኙንም ጎሳዎች አምራች ኃይል የሚመለከት ነው፡፡ ኤታንት የተከበረ ሥራ የሚሰራ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዋነኛነትም ከብት በማርባት እርሻ በማረስ ሌሎች የግብርና ስራዎችን የሚያከናውኑ የብሔረሰቡ አባላት ከዚህ ወገን የሚመደቡ ናቸው፡፡ ለዚህም ብሔረሰቡ ‹‹አምራች ኃይል›› ብሎ ይጠራቸዋል፡፡ ኤታንቶች ጥበበኞችና የድራሼ ብሔረሰብ መሰረት ተደርገው ይታያሉ፡፡

## 2.9 የድራሼ ብሔረሰብ ባህላዊ እሴት

የድራሼ ብሔረሰብ ትውልዱን የሚቀርጽበት ወግና ባህሉን የሚጠብቅበት ባህላዊ የማስተማሪያ ጥበቦች አሉት፡፡ እነዚህ ባህላዊ የስነ-ምግባርና የሞራል ማስተማሪያ ጥበቦች ከብሔረሰቡ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅርና ከረጅም የሕይወት ልምድ ፍልስፍና የሚቀዱ ናቸው፡፡

እነዚህ ባህላዊ የማስተማሪያ እሴቶች ያልተጻፉ ነገር ግን በሁሉም የብሔረሰቡ አባላት በእለት ተእለት ግንኙነት ውስጥ የሚተገበሩ ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገሩ የመጡ ናቸው፡፡

**ዳውራ (የተከለከሉና የተነወሩ ምግባራት)**

በድራሼ ብሔረሰብ ሐሰት መናገር፣ የሰውን ንብረት መውሰድ፣ ማመንዘር፣ ሰው መግደል እጅግ የተከለከለና የተወገዘ ተግባር ነው፡፡ እነዚህን መፈፀም ከቤተሰብ እስከ ከፍተኛ የባህላዊ አስተዳደር መዋቅር ድረስ የሚያደርስና የሚያስቀጣ ተግባር መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ይህንን መፈጸም በመገሰጽ ብቻ የሚታለፍ ሳይሆን ‹‹ዳውራ›› በተባለ የአስተምሮት ባህል ትውልድን አጥብቆ ያንፃል፡፡ እነዚህ ውግዝ ተግባራት ከቤተሰብ ጀምሮ አንድን ህፃን ከልጅነቱ ማስተማር የማህበረሰቡ ግዴታ ተደርጎ ይወሰዳል (ቃለ መጠይቅ፣ ብሩ ሰማሎ፣ መስከረም 4፣2008)፡፡

አንድ ህፃን የሰውን ንብረት መውሰድ የራስን እንደሚያሳጣ፣ ማመንዝር መሐን (ዘር አልባ) እንደሚያደርግ፣ ሐሰት መናገር ክፉ መናፍስትን በራስ እንደመጥራት እንደሚቆጠር ሲነገረው ያድጋል፡፡ በዚህም ብሔረሰቡ መልካም እሴቶችን ጠብቆ፤ ክፉ ምግባራትን ከትውልድ አርቆ ማንነቱን እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ ዛሬም ድረስ በአንዳንድ የድራሼ አካባቢዎች መንገድ ላይ በድንገት የተገኙ ዕቃዎችን ንብረቱ በተገኘበት ስፍራ ዛፍ ላይ

ሰቅሎ ማስቀመጥ የተለመደ ነው፡፡ ይህ ከብሔረሰቡ የ‹‹ዳውራ›› የማስተማር ባህል የመነጨ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

## ሰርካ (የማክበርና የመታዘዝ) እሴት

ይህ የ‹‹ሰርካ›› የማክበር እሴት ‹‹እናትና አባትን አክብር፣ ለታላላቆችህ ታዘዝ›› ከሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል የመጣ ይመስላል፡፡ በድራሼ ብሔረሰብ በዕድሜ ታላቅ የሆነ የትኛውም የብሔረሰቡ አባል ትልቅ ክብር ይሰጠዋል፡፡ በዕድሜ ታናናሾች በየትኛው የዕድሜ ደረጃ ቢሆኑ በማህበራዊ ግንኙነት በሐዘን፣ በደስታ ጊዜ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ሳይገናኙ ከቆዩ የአባትና የእናትን፣ የታላቅን ጉልበት ዝቅ ብሎ በመሳም ፍቅርና አክብሮታቸውን ይገልጻሉ፡፡ የዕድሜ ባለፀጋውም የጉልበት ሳሚውን አገጭ በእጁ ከፍ በማድረግ ለዕድሜ ታናሹ አክብሮቱን በማሳየት እደግልኝ ብሎ ግንባሩን በመሳም ይመርቃል፡፡

## ከኩ /ወግና ልማድን የመጠበቅ/ እሴት

ከኩ ህፃናትና ወጣቶች የብሔረሰቡን ልማዶች፣ ወጎችና ሥርዓቶች እንዲከተሉና እንዲያውቁ የሚያደርግ የማስተማሪያ እሴት ነው፡፡ በዚህ እሴት ብሔረሰቡ ታሪኩን፣ ቋንቋውን፣ ባህሉን በአጠቃላይ የማንነቱን መሰረት ለአዲሱ ትውልድ ያሳውቅበታል፡፡ ህፃናትና ወጣቶችም በዚህ የማስተማሪያ እሴት ተቀርፀው ስለሚያድጉ የብሔረሰቡን ማንነትና ሥርዓት ጠብቀው እነሱም በተራቸው ለቀጣዩ ትውልድ ያስተላልፋሉ፡፡ በመሆኑም ብሔረሰቡ ወግና ልማዱን ጠብቆ ማንነቱን ይዞ ዘመንን እንዲሻገር ያደረገው ይህ የ‹‹ከኩ›› የወግና ልማድ እሴት ነው፡፡

እነዚህ የድራሼ ብሔረሰብ የመልካም ምግባር ባህላዊ እሴት ከብሔረሰቡ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህሎች ጋር በጥብቅ ተቆራኝተው በትውልዱ ውስጥ ሁሉ የሚሰርፁ በመሆኑ ተቀባይነታቸውና ተፈፃሚነታቸው በእጅጉ ላቅ ያለ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብሩ ስማሎ፣ መስከረም 4/ 2008ዓ.ም)፡፡

# 3. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ የጥናቱ ክፍል ስለ ግጭት ምንነት የተሰጡ ብያኔዎች፣ መንስኤዎች፣ የግጭት ዓይነቶችና ደረጃዎች ይቀርባሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በድራሼ ብሔረሰብ ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንዲሁም በግጭት አፈታት ላይ የተደረጉ ተዛማጅ ጥናቶች ይከለሳሉ፡፡

## 3.1 የግጭት ምንነት

ስለ ግጭት በመስኩ ጥናት ያደረጉ እንደተነሱበት የጥናት ዓላማና እንደሚያጠኑት ርዕሰ ጉዳይ የተለያዩ ብያኔዎች ሰጥተዋል፡፡ የስነ-አዕምሮ ምሁራን ከሰው ልጅ ስነ-ልቦናዊ ተፈጥሮ ጋር አዛምደው ሲበይኑ የፖለቲካ ሳይንስ ተንታኞች ደግሞ ከሰው ልጅ እና ከሀገራት ፖለቲካዊ ግንኙነት በመነሳት ይበይኑታል፡፡ በአንፃሩ ኢኮኖሚስቶች ከሀብትና ከጥቅም ግንኙነት አዛምደው ሲበይኑት፤ የስነ-መለኮት ተመራማሪዎች ደግሞ ከመናፍስት (ከክፉ መንፈስ) ጋር አዛምደው ይገልጹታል፡፡

ስለ ግጭት ጥናት ካደረጉት መካከል Zartman ግጭት በሰው ልጆች የአብሮነት ሕይወት ውስጥ የማይቀርና በተለይ በእርስ በእርስ ግንኙነት ምክንያት በሚፈጠር የምርጫና የውሳኔ አለመጣጣም ውጤት መሆኑን "Conflict is an evitable aspect of human interaction, an avoidable communication of choices and decisions (1991፣299) በማለት ያስረዳሉ፡፡

Levison and Ember (1996፡237) ደግሞ ግጭት የሰው ልጆች የሚያደርጓቸው ተግባራት አንድ መልክ ሲሆን የሁሉም ማህበራዊ ግንኙኝነቶች ገጽታ መሆኑን "Conflict is a feature of all human activities and potentially an aspect of all social relationships" በማለት ያስረዳሉ፡፡

ግጭት በጋራ በሚኖሩ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖርና ሰበብ ክስተቱም የድርጊት፣ የሀሳብና የሀብት የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚደረግ ፍትጊያ እንደሆነ (Spangler, 2003) ይገልጻሉ፡፡

እንደ Spangler ገለፃ ግጭት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖር ክስተት ከሆነ በዚህ የአብሮነት ስብስብ ውስጥ የሀሳብ፣ የእምነት፣ የቋንቋ፣ የባህልና የርዕተ ዓለም ልዩነት

የሚጠበቅ ነው፡፡ እነዚህ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መልክ ያላቸው አስተሳሰቦች በአንዱ ወገን ላይ ያለፍላጎቱ እንዲቀበል ለማድረግ ሲሞከር ግጭት አይቀሬ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ግጭት ‹‹የሁለት ኃይላት የህግጋት፣ የመመሪያ፣ የርዕዮተ ዓለም ልዩነት ተቃርኖ መሆኑን›› (Plano፣ 1973) ይገልጻሉ፡፡

ግጭት በሁለት ተፃራሪ ኃይሎች በአንድ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ ፍላጎት አድሮባቸው የእነዚህ ፍላጎቶች በተቃርኖ መቆም የግጭት ውልደት እንደሚሆን (Destsch & Coleman, 2000) ይገልጻሉ፡፡ ይህንኑ ሀሳብ በማጽደቅ "Conflict refers to perceived divergent interest between two or more parties" በማለት (Levison 1996) ግጭት የሰዎች የውስጣዊ ፍላጎት አለመጣጣም ውጤት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ግጭት ከሰው ልጅ ውስጣዊ ፍላጎት የሚመነጭ እና ከተፈጥሯዊ ማንነት (ባህሪው) ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ክስተት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው በሰው ልጅ የአብሮነት ሕይወት ውስጥ ያለና የሚኖር እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

Fisher (1982) Leslau (1973), Bohaman (1967) ግጭት ‹‹የሁለት ኃይላት የትግል፣ የልዩነት፣ የጠብ፣ የውጊያ፣ ያለመግባባት ውጤት›› መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በሌላ በኩል ግጭት ለለውጥና ለተሻለ አስተሳሰብ በር ከፋች እንደሆነ Coser ‹‹ማንኛውም ህብረተሰብ በውስጡ ባለው የግጭት ተነሳሽነት በለውጥ ሂደት ተሳታፊና የላቀ አስተሳሰብ ባለቤት ይሆናል›› (1970፣25) ይሉናል፡፡ በ Coser እምነት በየትኛውም ቦታና ሥፍራ የሚከሰት ግጭት አንድ ምክንያት የያዘ እንደሆነና ይህ ምክንያት ውጤቱ የህብረተሰቡን የለውጥ፣ የፍላጎት መሟላት በመመለስ ወደ ላቀ የሕይወት መንገድ እንደሚያሻግረው ይጠቁማሉ፡፡

ይህ አስተሳሰብ ግጭት አሉታዊ መልክ ብቻ አለው ከሚሉ ወገኖች ጋር የመከራከሪያ ነጥብ ሆኖ የቀጠለ ሲሆን ይህን ሀሳብ በመቃረን ‹‹ግጭት በሰው ልጆች ሁለንተናዊ ህይወትና ሠላም ላይ ከፍተኛና የማይሽር ጠባሳ የሚጥል ክስተት ነው›› (Rummel፣ 2007) በማለት የግጭትን አዎንታዊ ሳይሆን አሉታዊ መልክ ይገልጻሉ፡፡

በእርግጥም የግጭት መልካምነት በመሪ ደረጃ የትኛውንም የማህበረሰብ ክፍል የሚያስማማ ባይሆንም ከግጭቱ በፊትና በኋላ ባሉ ለውጦች በመመስረት ግጭቱ ያመጣው ውጤት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ከቻለ የCoser የመከራከሪያ ነጥብ የሚያስማማ

ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ውጤቱ የቱንም ያህል ይሁን ግጭት ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑ ብዙሀኑን ያስማማል፡፡

## 3.2. የግጭት መንስኤዎች

የግጭት መንስኤዎች ከማህበራዊ፣ ከኢኮኖሚያዊና፣ ከፖለቲካዊ ግንኙነቶች እንደሚፈጠሩ ያስረዳሉ (Kuper,1996, 124) Jeong በበኩላቸው የግጭት መንስኤዎችን ዘርዘር በማድረግ ስድስት ነጥቦችን ይገልጻሉ፡፡ ከሰዎች ሥነ-ልቦናዊ የእይታ አቅጣጫ (psyshoanaltic perspspective) የሚመነጭ የግጭት መንስኤ፣ ከቁጡነት ባህሪ (programmed aggressive behavior) ከፍላጎት አለመሟላት (Basic need interest)፣ በነገሮች ጣልቃ ገብነት (Relative deprivation)፣ እራስን ማስቀደም (Identify formation)፣ የግጭት መንስኤ ይሆናሉ (2000፣ 65) በማለት ይገልጻሉ፡፡

Jeong የግጭት መንስኤ ብለው የገለጹዋቸውን ነጥቦች ስንመለከት አብዛኛዎቹ ከሰዎች ሥነ-ልቦና፣ ፍላጎትና ባህሪ ጋር የተዛመዱ ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት ግጭት ከሰው ልጅ ውስጣዊ ፍላጎት ያለመሟላት የሚከሰት እንደሆነም መረዳት ይቻላል፡፡

## 3.3 የግጭት ዓይነቶች

የግጭት ዓይነትና ደረጃዎች የተለያዩ መሆናቸውን በመግለጽ የግጭት ዓይነቶችን ከመደቡ አጥኚዎች አንዱ (Heinz፣ 2006) ናቸው፡፡ Heinz የግጭት ዓይነቶች ሶስት መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም ‹‹ስነ-ልቦናዊ ግጭት፣ አላማዊ ግጭት፣ የውሳኔ ግጭት›› በማለት ይመድቧቸዋል፡፡

በሌላ መልኩ የግጭት ዓይነቶችን ግላዊ ግጭት (Inter personal conflict)፣ ሚናዊ ግጭት (Role conflict)፣ የቡድን ግጭት (Inter group conflict) መድብለ ፓርቲያዊ ግጭት (multi-party conflict)፣ አለማቀፋዊ ግጭት (international conflict) በማለት በአምስት ክፍሎች (Fisher፣ 1982) ይመድቧቸዋል፡፡

የሁለቱ ምሁራን የግጭት ዓይነቶች ምደባ የተቀራረበ ሲሆን ሁለቱም የሚስማሙባቸውን ግላዊ ግጭት (Inter personal conflict)፣ የቡድን ግጭት (Inter group conflict)፣ በግለሰቦች መካከል የሚፈጠር ግጭቶችን በመውሰድ እንመልከት፡፡ ግላዊ ግጭት ወይም ከራስ ጋር የሚደረግ ግጭት ማህበረሰቡ ይሁነኝ ብሎ የተቀበላቸው ባህላዊ ወይም

ኃይማኖታዊ እሴቶች የግለሰብ አይነት፣ አስተሳሰብና ምግባር በተቃርኖ ሲቆም ውስጣዊ ግጭት ይፈጠራል፡፡ ይህ ግጭት ከሰው ልጅ ሁለንተናዊ ሰብእና እና ስነ-ልቦና ጋር የሚዛመድ በመሆኑ በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈታና የባለሙያ እገዛን የሚጠይቅ የሚሆንበት አጋጣሚ ሰፊ እንደሆነ ይታመናል፡፡

በግለሰቦች መካከል የሚፈጠር ግጭት ሌላው የግጭት ዓይነት ነው፡፡ ይህ የግጭት ዓይነት በአብዛኛው ከሰው ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት በመነሳት የሚፈጠር ነው፡፡ በዚህ ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በአስተሳሰብ፣ በድርጊት በኢኮኖሚ ልዩነት አለመግባባቶች ይከሰታሉ፡፡ እነዚህ አለመግባባቶች ከፍ ወዳሉ ልዩነቶች በማምራት ግጭትን ይወልዳሉ፡፡ ለዚህም ይመስላል ‹‹ግጭት የታሪካዊ ሂደት ውጤት እንጂ የድንገቴ ክስተት አይደለም›› በማለት (Loomis፣ 1985፣49) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ግለሰቦች ከትላንት ዛሬ ይዘዋቸው የመጧቸው አስተሳሰብም ይሁን ድርጊት የግጭት መነሻ ይሆናሉ፡፡ ይህ የግጭት ዓይነት እንደ ግለሰቦቹ ማህበራዊ መሰረት (ማንነት) ወደ ቡድን አልያም ወደ ማህበረሰብ የመስፋት ዕድሉ ሰፊ ነው ፡፡

የቡድን ግጭት (Inter group conflict)፣ ከግለሰብና ከራስ ጋር ከሚደረግ የግጭት ዓይነቶች ለየት የሚያደርገው ታስቦና ታቅዶ ሊፈጠር የሚችል መሆኑ ነው፡፡ ይህ የግጭት ዓይነት በሁለት ጎሳዎች፣ የተለያየ ባህል ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ሊፈጠር ይችላል፡፡ በአብዛኛው በቡድን ውስጥ ሰፊ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ሊታቀፉ ስለሚችሉ ስፋትና ጥልቀት ይኖራቸዋል፡፡ ከሚይዛቸው የተሳታፊ ብዛት በመነሳት የግጭት አይነቶችን በራሱ በቡድን ውስጥ (Inter- group)፣ የግጭት አይነት መኖሩን በመጠቆም፣ በሀገር ውስጥ (Intera state)፣ በሁለቱ መካከል (inter state) የግጭት አይነቶች መኖራቸውን ይገልፃሉ (Medhane፣ 2004፣3)፡፡

በሌላ መልኩ የመከሰቻ መንገዳቸውን በመምዘዝ የግጭት አይነቶችን የእሴት ግጭት፣ የመዋቅራዊ ግጭት፣ የመረጃ ግጭት የግንኙነትና የፍላጎት የግጭት አይነቶች መኖራቸውን የሚገልፁ ምሁራን አሉ፡፡ የእሴት ግጭት በሰዎች የአመለካከት ልዩነት የሚፈጠር እንደሆነ ይታመናል፡፡ በአንፃሩ መዋቅራዊ ግጭት የሐብትና የኃይል ክፍፍል ባለመመጣጠን የሚከሰት የግጭት አይነት ሲሆን በአብዛኛው በሀገራት መካከል የሚፈጠር የግጭት አይነት እንደሆነ ይገለፃል፡፡ የመረጃና የግንኙነት የግጭት አይነቶች ከግለሰቦቹ ሰብእና ባህሪ የሚመነጭ መረጃን የመረዳት፣ የመተርጎም፣ ለሌሎች ሰዎች ከሚኖር አሉታዊ አመለካከት

የሚከሰት የግጭት አይነቶች ናቸው፡፡ እነዚህ የግጭት አይነቶች መንስኤአቸው ምን እንደሆነ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## 3.4 የግጭት መፍቻ ዘዴዎች

ከግጭት መፍቻ ዘዴዎች መካከል አንዱ ሽምግልና (mediation) ነው፡፡ ፈቃደ አዘዘ ሽምግልና ‹‹ሁነኛ የግጭት መፍቻ ስልት›› መሆኑን ይገልጻሉ (2004፣7)፡፡ ሽምግልና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታትና በተለይ ለቀጣይ የአብሮነት ሕይወት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት ይታመናል፡፡ ይህንን ሀሳብ በመጋራት (Gulliver 1997) Shellenberg (1996) ሽምግልና (Mediation) በተጋጩ ወገኖች መካከል ጣልቃ የሚገባ ሦስተኛ ወገን እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ እንደ አሸማጋዮቹ ጥንካሬ ችግሮችን ለመፍታት ይህ የተሻለ የግጭት መፍቻ ዘዴ መሆኑን ይስማማሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Bohaman(1967) Schellen berg(1996) ግጭት ወይም ሁከት (Violence) ሊፈታ የሚችለው ግጭቱን የፈጠረው አካል በሚጠቀመው የኃይል ሚዛን አሸናፊነት ሲሆን በሌላ መልኩ በማስማማት፣ በመዳኘትና በማስታረቅ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

ቀዳሚው መፍትሄ ግለሰቡ ወይም ቡድኑ የኃይል ሚዛን የሚፈጥረው ግጭቱን የማብረድ ስልት በመሆኑ ዘላቂነቱ አስተማማኝ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የራሱን ፍላጎትና እምነት በሌላው በመጫን የሚያመጣው ግጭት የማብረድ መንገድ በመሆኑ ሁለተኛው አማራጭ የተሻለ እንደሆነ ይታመናል፡፡

## 3.5 የተዛማጅ ጥናቶች ክለሳ /ቅኝት/

በዚህ ክፍል በድራሼ ብሔረሰብ ላይ የተደረጉ ጥናቶች በሁለት መልክ በመለየት ይቃኛሉ በቀዳሚነት በድራሼ ብሔረሰብ ላይ በተለያዩ የትምህርት ክፍሎች የተጠኑ ጥናቶች ብሔረሰቡን አስመልክቶ በጥናቶቻቸው ያነሷቸው ዋነኛ ጉዳዮችና በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፍክሎር የትምህርት መስክ የተደረጉ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ዝምድናና ልዩነት ይቀርባሉ፡፡

### 3.5.1. በድራሼ ብሔረሰብ ላይ የተደረጉ ጥናቶች

በዚህ ክፍል በድራሼ ብሔረሰብ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ቅኝት ይቀርባል፡፡

**Firew Tesfaye (2012)** «The Quest for Empowering Indigenous System Local Self Governance among the Dirasha of South Western Ethiopia» በሚል ርዕስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ Inistitute of Ethiopian Studies ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጓል፡፡ የፍሬው ተስፋዬ ጥናት ዓላማ ሀገር በቀል የአስተዳደር መዋቅርን ማጥናት ነው፡፡ በጥናቱም የድራሼ ብሔረሰብ ሀገር በቀል የሆነ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የአስተዳደር መዋቅር እንዳለው አሳይቷዋል፡፡ ይህ ሀገር በቀል የአስተዳደር መዋቅር ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገር የመጣ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ግን በዘመናዊ አስተዳደር እየተዋጠ መምጣቱን ጥናቱ ያመለክታል፡፡ የፍሬው ጥናት በሀገር በቀል የአስተዳደር መዋቅር ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የእኔ ደግሞ በባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓቱ ላይ በማተኮሩ ይለያያሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በብሔረሰቡ አንዳንድ የግጭት ዓይነቶች የሚፈቱት ሀገር በቀል በሆነው ባህላዊ መዋቅር ስለሆነ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

**Yednekachew Ayele (2011)** Ethnic Conflict Managment and Conflict Transformation፡ the Case of Derash and Konso" በሚል ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሰላምና ደህንነት ትምህርት ክፍል የቀረበው ጥናት በድራሼና በኮንሶ ብሔረሰቦች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ምን ዓይነት እንደሆኑ እንዴት እንደሚፈቱ ይተነትናል፡፡ ግጭቶች ሲከሰቱ ከዓለም አቀፍና ሀገራዊ ከሆኑ ህጎች አንፃር እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል ይጠቁማል፡፡ አጥኚው በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ውይይትና በምልከታ በሰበሰበው መረጃ የሁለቱ ህዝቦች የግጭት መነሻ በከብቶች የመሬት ግጦሽ፣ በድምበር፣ በመልካም አስተዳደር እጦት በአጠቃላይ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረት ባላቸው ጉዳዮች እንደሆነ አብራርቷል፡፡ በጥናቱ የሁለቱን ህዝቦች ግጭት ወደ ተሻለ የመግባባትና ወደ ለውጥ መንገድ ለመውሰድ የሚቻለው ዘመናዊ የዳኝነትን ስርዓት በማጠናከር፣ የፀጥታ ኃይሎችን በመመደብ፣ ውይይቶችን በማድረግ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በጥናቱ የባህላዊ ፍትህ ስርዓቶችን ከዘመናዊ አስተዳደርና የዳኝነት (እርቅ) መፍቻ ስርዓት ጋር በማጣመር ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደሚቻል አልተጠቆመም፡፡ በዚህ ረገድ የእኔ ጥናት የድራሼ ብሔረሰብን የባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓት በማሳየት በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደሚቻል የሚያመለክት በመሆኑ

ከይድነቃቸው ጥናት ይለያል፡፡ በተጨማሪም የይድነቃቸው ጥናት በሁለት ብሔረሰቦች ላይ ማተኮሩ እና ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትን አለመመልከቱ ከእኔ ጥናት ጋር ልዩነቱ የሰፋ ነው፡፡

**Tizazu Desalegn (2007)** "Inter Ethnic Conflict in south Western Ethiopia፡ A Case Study of Resource Based Interethnic Conflict Between Zayese and Dirashe Communities and Attempts For Transformation." በሚል ርዕስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ Inistitute of Ethiopian Studies ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አድርጓል፡፡ በርዕሱ እንደተመለከተው እንደ ይድነቃቸው ጥናት ከድራሼ ብሔረሰብ አጎራባች ከሚኖረው ከዘይሴ ብሔረሰብ ጋር በማጣመር የተጠና ነው፡፡ የትዕዛዙ ጥናት የግጭት መንስኤዎችን ከሀብት ጋር ብቻ አዛምዶ ማየቱ የብሔረሰቦችን የጎሳና የደም ትስስር ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት በማጎልበት ግጭቶችን መፍታት እንደሚቻል አለማመላከቱ የጥናቱ ጉድለት ነው፡፡ በሌላ መልኩ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓትን አለመመልከቱና በሁለት ብሄረሰቦች ላይ መመስረቱ ከእኔ ጥናት ይለያል፡፡

**ሐንሰሞ ሐመላ (1983)** " Internal History of Dirashe (Gidole) በሚል ርዕስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት የድራሼ ብሔረሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አካዳሚክ ውይይትና ጥናት በማምጣት የሐንሳሞ ሐመላ ጥናት ቀዳሚ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ጥናቱ የብሔረሰቡን ታሪክ፣ ባህላዊ እሴትና የአኗኗር ስልት በጥቅሉ የሚያሳይ ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት ምንም እንኳ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ቢሆንም የብሔረሰቡን ከየት መጣነት፣ የቋንቋውን ፣ የአኗኗር ስልቱና ሌሎች ጉዳዮችን በአጠቃላይ የብሔረሰቡን ማንነት በማስተዋወቅ ለሌሎች አጥኚዎች መነሻ የሆነ ጥናት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩትን ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር የሚያዛምዳቸው በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ብሔረሰቡን መሰረት ያደረጉ መሆናቸው ሲሆን በርዕስ ጉዳይና ትኩረት ግን ከእኔ ጥናት ይለያሉ፡፡

### 3.5.2 በባህላዊ የግጭት አፈታት ላይ የተደረጉ ጥናቶች

በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትን ርዕሰ ጉዳያቸው አድርገው የተጠኑ አስራ ስምንት ጥናቶችን

ተመልክቻለሁ ፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች መካከል ከእኔ የጥናት አካባቢ ቅርብ የሆኑትን አራት ጥናቶችን በመለየት እከልሳለሁ፡፡

**እንዷለም አባተ** (2004) ‹‹ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በመኤኒት ብሔረሰብ›› በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት የመኤኒት ብሔረሰብ በባህላዊ ሥርዓት ግጭትን እንዴት እንደሚፈታ፣ ግጭቶች ሲፈጠሩ በማን እንደሚፈቱ፣ የአፈታት ስርዓቱ እንዴት እንደሆነ አሳይቷል፡፡ በመኤኒት ብሔረሰብ የነፍስ መግደል እርቅ ‹‹አሻ›› ተብሎ እንደሚጠራ የመደፈር እርቅ ስርዓት ሂደት ‹‹ማጠብ›› እንደሚሰኝ ገልጿል፡፡

በብሔረሰቡ በአብዛኛው የግጭቶች መንስኤ ሰው በመግደል፣ ድንበር በመግፋት፣ በገንዘብ በመካካድ አስገድዶ በመድፈር እንደሆነ በጥናቱ ተመላክቷል፡፡ አጥኚው ለጥናቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቃለ-መጠይቅ ምልከታና የቡድን ውይይት መጠቀሙን ገልጿል፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በገላጭና በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ለመተንተን መሞከሩና የግጭት አፈታት ባህሉ ያለውን ፋይዳ ማሳየቱ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ጥናትና በእኔ ጥናት የግጭት መነሻ የሆኑ ጉዳዮች በአብዛኛው ተመሳሳይ ሲሆኑ ግጭቱ የሚፈታበት ሂደትና የሚያልፋቸው መዋቅራዊ እርከኖች ፍጹም የተለያዩ ናቸው፡፡

**አብርሐም ታደሰ** 1999 ‹‹ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሔረሰብ ›› በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት በብሔረሰቡ በአብዛኛው የሚከሰቱ ግጭቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ መልክ ያላቸው መሆናቸውን አሳይቷል፡፡ የአብርሐም ጥናት ተረትና ምሳሌዎች ለእርቅ ሥርዓቱ ያላቸውን ፋይዳ ትኩረት አድርጎ በሰፊው መግለፁ ጥንካሬው ሲሆን ከጥናቱ ዓላማ አንጻር የእርቅ ሥርዓቱን ሂደት በስፋት አለማሳየቱ ጉድለቱ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የእኔ ጥናት የእርቅ ሥርዓቱን ሂደት በማሳየት በኩል ከአብርሃም ጥናት ይለያል፡፡

**ተመስገን ምንዋጋው** 1998 ‹‹ሀገረሰባዊ የግጭት መፍትሄ ስርዓት በዶካ ጋሞ›› በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ዓላማ በዶካ ጋሞ ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ሂደትን ማሳየት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የዶካ ጋሞ ማህበረሰብ ግጭቶችን የሚፈቱ ‹‹መለኮታዊ ኃይል›› ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ወይም ግለሰቦች እንደሆኑ በጽኑ እንደሚያምኑ በጥናቱ ተገልጿል፡፡ እነዚህ መለኮታዊ ኃይል ያላቸውና በህብረተሰቡ ከፍተኛ እምነት የተጣለባቸው ግለሰቦችን እርቀ ሰላም ለማውረድ ስድስት ባህላዊ ተቋማትን እንደሚጠቀሙ

ተመልክቷል፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ግጭቶች የሚፈጠሩት በነፍስ ግድያ፣ በጎሳ፣ በድንበር፣ በሰው መሬት በመድፈርና በዘመዳሞች መካከል በሚፈጸም የግብረ- ስጋ ግንኙነት እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ የተመስገን ጥናት ያተኮረባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች የኔ ጥናት ከተመሰረተባቸው ብሔረሰቦች ጋር ቅርበት ቢኖራቸውም የግጭት አፈታት ስልትና ሂደታቸው ይለያያል፡፡ ጥናቱ የማህበረሰቡን የግጭት መፍትሄ ስርዓት በማሳየት በኩል ዓላማውን አሳክቷል ማለት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የግጭት መፍትሄ ስርዓቱ ለማህበረሰቡ የአብሮነት ሕይወት ያለውን ፋይዳ አለማሳየቱ የጥናቱ ጉድለት ነው፡፡

**ይልማ ተፈራ** 1998 ‹‹የሽምግልና እርቅ ሥርዓት በወላይታ›› በሚል ርዕስ ያደረገው ጥናት የወላይታ ብሔረሰብ አስተዳደራዊ እና ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት መዋቅር እንዳለው አሳይቷል፡፡ ለእነዚህ መዋቅሮችም ማህበረሰቡ ትልቅ ክብር እንዳለው ተገልጿል፡፡ ጥናቱ በነዚህ የፍትህ ሥርዓቶች ከህጻናት እስከ አዋቂ ተሳታፊ መሆናቸውን ጠቁሟል፡፡ የይልማ ጥናት ጥንታዊ መዋቅሮችን ጭምር በመለየቱ ጠንካራ ጎኑ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ጥናቱ በዚህም ከኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸው ጥናቶች በባህላዊ ግጭቶች አፈታት ስርዓት ላይ ማተኮራቸው፣ ግጭቶች ሲፈጠሩ የሚያልፉባቸውን ሂደት በማሳየት በኩል ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚያገናኛቸው ሲሆን የግጭት አፈታት ሂደቶችን በማሳየት የመረጃ አሰባሰብና ትንተና እንዲሁም በጥናት አደረጃጀት ስልታቸው ከእኔ ጥናት ይለያሉ፡፡

## 3.6 የድራሼ ባህላዊ አስተዳደርና የግጭት መፍቻ ስርዓት መዋቅሮች


በዚህ ክፍል የድራሼ ብሔረሰብ የባህላዊ አስተዳደር መዋቅርና የባህላዊ ፍትህ ስርዓት ምን እንደሚመስል፣ ግጭቶች ሲፈጠሩ በእነዚህ መዋቅሮች እንዴት እንደሚፈቱ እንዲሁም ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ አሁን ያለበትን ሁኔታ እንመለከታለን፡፡ እነዚህን ባህላዊ የአስተዳደር እና የፍትህ ተቋማት በዝርዝር መመልከቱ ብሔረሰቡ ለግጭት ያለውን አመለካከት ከማሳየቱም በላይ ለሕይወት ያለውን ፍልስፍና ይጠቁማል፡፡

### 3.6.1 የባህላዊ አስተዳደርና መዋቅር ገጽታ

የድራሼ ብሔረሰብ ጥንታዊ የሆነ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር አለው፡፡ ይህ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር እስከ 1890 ዓ/ም ድረስ ጠንካራ መሰረት እንደነበረው (ፍሬው፣2011)

ይገልፃል፡፡ እነዚህ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅሮች በአራት ዋና የባህላዊ አስተዳደር ምሰሶዎች ማለትም በዳመ፣ በፓልዳ፣ በሼላ እና በሻና ተብለው በሚጠሩ (መሪዎች) የቆሙ ናቸው፡፡ እነዚህ አራት ዋንኛ ባህላዊ (የአስተዳደር መዋቅሮች) በየውስጣቸው እንደ ማህበራዊ መሠረታቸው የሚያቅፏቸው ንዑስ የአስተዳደር መዋቅሮች አሏቸው፡፡ የትኛውም ዓይነት ግጭት የሚፈታውም ይሁን ዳኝነት የሚሰጠው በእነዚህ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅሮች ነው፡፡ የእያንዳንዳቸውን ሚናና ተግባር ቀጥሎ እንመልከት፡፡

**መዋቅር 1 የባህላዊ አስተዳደር መዋቅር ቅርጽ**




ምንጭ፡- Firew Tesfaye M.A. thesis, A.A.U. 2012./unpublished/

## የድራሼ ንጉስ (ዳማ)

ዳማ በድራሼ ብሔረሰብ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የበላይ መሪ ነው፡፡ የጎሳ መሪዎች በዳማው ውስጥ የታቀፉ ናቸው፡፡ የዳማው ስልጣን እምነታዊ እና አስተዳደራዊ ይዘት አለው፡፡ ይሁን እንጂ እምነታዊ መሪነቱ ጎልቶ የሚታይ ነው፡፡ በድራሼ ብሔረሰብ ‹‹ዳማው›› ዝናብ ያዘንባል አካባቢውንም በልምላሜ ይሞላል የሚል ፅኑ እምነት እንዳለ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ታደሰ ተሸባሌ፣ መስከረም 3/2008) ገልፀውልኛል፡፡ በዚህም ማህበረሰቡ ለዳማው ከሚያመርተው ወይም ከሚያረባው መገበር ግዴታው ነው፡፡ ዳማዎች ከሌላው ማህበረሰብ የሚለያቸው የስልጣን መግለጫ ምልክት አላቸው፡፡ ይህ የስልጣን መግለጫ ምልክት ‹‹ሚጫራ››[8] ይባላል፡፡

በዳማው የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ‹‹አራፋይታ›› የንጉስ ችሎት መሪዎች ይገኛሉ፡፡ የዳማውን አጠቃላይ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚከታተሉ እነዚህ መሪዎች ናቸው፡፡ የትኛውም የህብረተሰቡ ጉዳዮች ከበታች መሪዎች እንደ ፓልዳ፣ ሼላና ሻላ የመሳሰሉ መሪዎች ጋር በመገናኘት ወደ ንጉስ /ዳማው/ በማድረስ ውሳኔ ማሰጠት በእነሱ አቅም የሚፈቱ ካሉ የመፍታት ስልጣን አላቸው፡፡ ይህ መዋቅር አብዛኛውንና ትልቁን ስልጣን ጠቅልሎ እንደሚይዝ ‹‹The highest political function of the court community was manipulated by the court of elders called arfayta.›› /ፍሬው፣ 2011/ በማለት የአርፋይታን የዳኝነትና የውሳኔ ሰጪነት ስልጣንን ይገልፃል፡፡

በመሆኑም ዳማው ምንም እንኳ ውሳኔ ቢሰጥም የአርፋይታ ሚና ጎልቶ ይወጣል፡፡ ዳማውም በአምልኮአዊ ስልጣኑ ህዝቡን ይመራል፡፡ የዳማው ስልጣን በዘር ሐረግ ከትውልድ ትውልድ ለዳማው የመጀመሪያ ወንድ ልጅ እየተላለፈ የመጣ ሲሆን አርፋይታው ግን በማህበረሰቡ ውስጥ ካላቸው ተሰሚነት፣ ወግና ባህል አክባሪነት ይመረጣሉ፡፡

---

[8] ሚጫራ ጥቁር ቀለበትና ‹‹ሀራውቶት›› ተብሎ የሚጠራ የልምላሜ ምልክት ጥምዝ በራስ /አምባር/ እንደሆነ (ሐንሳሞ፣ 1993) ይገልፃሉ፡፡

የድራሼ ዳማዎች በዘር ሐረግ ቅብብሎሽ ዛሬም ድረስ ዘልቀው የመጡ ሲሆን የመጨረሻው[9] የድራሼ ዳማ የሞተው በ1991 ዓ/ም ሲሆን የዚህ ዳማ የመጀመሪያው ወንድ ልጅ ስልጣኑን በመቀበል በብሔረሰቡ ባህል መሠረት ‹‹ዳማ›› ተሰኝቶ ተሹሟል (የቡድን ውይይት፣ መስከረም 5/2008 ዓ/ም) ፡፡

**የጎሳ አለቃ (ፓልዳ)**

ፓልዳ በድራሼ ብሔረሰብ የአንድ ጎሳ መሪ ወይም አለቃ ነው፡፡ የመሪነት ሚናው አስተዳደራዊና አምልኮአዊ ቢሆንም እንደ ዳማው ሁሉ እምነታዊ (መንፈሳዊ) መሪ ተደርጎ እንደሚታይ ‹‹Poldha is like spiritual Father of members of his clan /Firew፣ 2012/ በማለት ያስረዳል፡፡

የጎሳ አለቃው የስልጣን መዋቅር ሁለት ዓይነት ቅርጽ ያለው ነው፡፡ አንደኛው የፓልዳውን አምልኮአዊ ስልጣንን የሚከታተል የሚመራ /ካዳይት/፣ ሁለተኛው ደግሞ ‹‹ማጋ›› የተሰኘው የህብረተሰቡን ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን የሚከታተል የመንደር ተጠሪ በፓልዳው የስልጣን መዋቅር ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ታደሰ ተሸባሌ፣ መስከረም 3/1/2008) ፡፡

የፓልዳው ዋንኛ ተግባር የጎሳውን አባላት ደህንነትና ሠላም በመንፈሳዊ ልዩ ኃይሉ መጠበቅ ነው፡፡ ከጎሳው አባላት ወጪ የሚኖራቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች በአግባቡና በስርዓቱ መከናወናቸውን መከታተል ነው፡፡ በዚህም ማህበራዊ ግንኙነቶች አለመግባባቶች ቢፈጠሩ ጎሳውን ወክሎ ከሌሎች የጎሳ መሪዎች ጋር በመደራደር ችግሮቹ እንዲፈቱ ያደርጋል፡፡ መፈታት ካልቻሉም ወደ ‹‹ዳማው›› የበላይ መሪ ይዞ የሚቀርበው ይህ መሪ ነው፡፡ በተለይ ወንጀል ነክ የሆኑ ጉዳዮች ሲሆኑ የፓልዳ ሚና ከፍ ያለ ነው፡፡

---

[9] የመጨረሻ የድራሼ ዳማ ጅምሩ ሰማ የሚባል ሲሆን ይህ ዳማ ከሞተ በኋላ ሰልጣኑን የተቀበለዉ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ “መስፍን ጅምሩ” ይባላል፡፡ መስፍን ጅምሩ ጥናቱ እስከ ተደረገበት ወቅት ከጊዶሌ በ55 ኪ.ሜ ላይ በሚትገኘዉ በአርባ ምንጭ ከተማ የሚኖር ሲሆን ብሔረሰቡ ወሳኝ ችግሮች ሲገጥሙትና የማይቀሩ የእምነት በአላት ሲከበሩ ወደ አካባቢዉ ተጠርቶ እንደሚመጣ በቡድን ውይይት ወቅት መረጃ አቀባዮቹ ገልፀውልኛል፡፡

ከፓልዳ በታች በመሆን በህብረተሰቡ የሚደርሱ ችግሮችን ለማቃለል ‹‹ካዳይት›› የማስተባበር መስመር የማስያዝ ግዴታ ያለበት ሲሆን ተግባሩ በአብዛኛው መንፈሳዊ ስርዓትን ማስፈፀም ነው፡፡ መሪው ዕለታዊ ክንውኖችን መሰረት በማድረግ የጎሳውን አባላት ከፓልዳው ጋር ያገናኛል፡፡

**የአንድ ንዑስ ጎሳ መሪ (ሼላ)**

ሼላ እምነታዊ (መንፈሳዊ) መሪነታቸው ያይላል፡፡ በዚህም ምክንያት በህብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ክብርና ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡ ከሰው የተለየ በሽታን፣ ድርቅን በአጠቃላይ ክፉ መንፈስን የማራቅ ኃይል አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዘጠኙም ጎሳዎች ትልቅ ጎሣ ከሚባሉት አራት ጎሳዎች የሚወጡ ናቸው፡፡ ሼላ ሆኖ የአርጋማይት ጎሣ ከሆነ ወፎችን የማባረር ልዩ ኃይል አለው ይባላል፡፡ የካላይት ጎሳ ሼላ ደግሞ በሽታን ይቆጣጠራል የሚል እምነት አለ፡፡

የብሔረሰቡ አባላት ከተለመደው ልማድና ወግ ወጣ ያለ ነገር ከሰሙ መከራና ቅጣትን በልዩ ኃይላቸው ያወርዳሉ ተብሎም ይታሰባል፡፡በእነዚህ አካላት አምልኮአዊ ስርዓት ካልተፈፀመ ከማህበረሰቡ ላይ ችግርና መከራው አይነሳም ስለሚባል በሚመሩት ንዑስ የጎሳ አባላት እንደ ‹‹ዳማ›› የመታየት ዕድላቸው ሰፊ ነው፡፡ ከአምልኮታዊ መሪነታቸው ጎን ለጎን የጎሳ አባላቱን የዕለት ተዕለት ችግር በመቅረፍ ረገድ የሚጫወቱት ሚና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

**የመንደር መሪ (ሻና)**

ሻና ሌላኛው የባህላዊ የአስተዳደር ቅርጽ ሲሆን በድራሼ ብሔረሰብ ውስጥ በሁለንተናዊ ሰብእናው የተከበረ፣ ለሌሎች አርአያ የሆነ ግለሰብ ለዚህ የመሪነት ሚና ይታጫል፡፡በሰብእናው የተሻለ ግለሰብ ለዚህ ኃላፊነት የሚመረጥ በመሆኑ እንደ መንፈሳዊ መሪ ይታያል፡፡ በመሆኑም በመንደሩ ነዋሪዎች ከፍተኛ ከበሬታ ስላለው ውሳኔዎቹም ሆኑ ትዕዛዞቹ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ በዳማውም በኩል ያለው ተሰሚነት ከፍ ያለ ነው፡፡ ይህም ከታች ካለው ህዝብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላለው ሕዝቡ ለዳማው ያለውን ምልከታ የሚያረጋግጠው ከዚሁ ከሻናው ስለሆነ ይመስላል ፡፡ በዚህ በሻና መዋቅር ውስጥ ሁለት አስፈጻሚዎች አሉ፡፡ አንደኛው‹‹ ሱጋ›› ሲሰኝ ሁለተኛው ደግሞ ‹‹አባ ቲምባ›› ይባላል (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ታደሰ ተሸባሌ፣ መስከረም 3/1/2008 ዓ/ም)፡፡

ሱ.ጋ፡- ይህ መሪ በሻና ውስጥ ሆኖ ከሕብረተሰቡ ለዳማው የሚሰጡ ግብሮች በአግባቡ መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል፡፡ የሱ.ጋ ሹመት ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ እንጂ በምርጫ የሚወሰን አይደለም (ሐንሳሞ፣1993)፡፡ የሱ.ጋ መሪ ሌላኛው ገጽታ የስራው ባህሪ ከጎሳው አባላት ጋር በቀጥታ የሚያገናኘው በመሆኑ የአባላቱ ሀዘን ይሁን ደስታ፣ ቅሬታም ይሁን ጥላቻ የመጋራት እድሉ ከፍ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም በላይኛው የባህላዊ አስተዳደር የሚወሰኑ ውሰኔዎች፣ የሚሰጡ ዳኝነቶች በጎሳ አባላቱ ዘንድ ቅሬታን የሚፈጥሩ ከሆነ ወደ ከፉ የልዩነትና የግጭት መንገድ ሳያመሩ ውሳኔዎችና ዳኝነቶች እንዲሻሻሉ የማድረግ ስልጣን አለው፡፡

አባ ቲምባ ፡- በስልጣን ረገድ ከሱ.ጋው ያነሰ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሕብረተሰቡ አብሮነት ውስጥ የሚፈጠሩ ማህበራዊ ሆነ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለማቃለል ህብረተሰቡን ያስተባብራሉ፡፡ አባቲምባ ከእዚህም ስልጣን ባሻገር የመንደሩ ነጋሪት (ጡሩንባ) ነፊ ነው፡፡ በተለይ በሀዘን ወቅቶች ህብረተሰቡን በማስተባበር ሀዘንተኛ ቤተሰቦች መጽናኛ እንዲያገኙ በማድረግ ሚናው ከፍ ያለ ነው፡፡

እነዚህ የድራሼ ብሔረሰብ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅሮች ዘመናትን አልፈው፣ ትውልድን ተሻግረው ዛሬም ድረስ በማህበረሰቡ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የመዋቅራዊ ትስስር ቅርጽና ይዘታቸውን ስንፈትሽ የተለያዩ ግን አንድ የሆኑ፣ የማህበረሰቡን ህልውና የሚጠብቁ ፍጹም ጥበባዊ መዋቅር ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ከላይ በዝርዝር ያየነው ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር ዋንኛ ተግባሩ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ችግሮችን በመለየት መፍታት ነው፡፡ በዚህ መዋቅር ውስጥ ባየናቸው የስልጣን እርከኖች በሙሉ ዳኝነት ወይንም የፍትህ ስርዓት አይሰጥም፡፡ ይሁን እንጂ የፍትህ መዋቅሩ የሚቀዳው ከዚህ ከባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር ነው፡፡ የፍትህ መዋቅሩ ምን እንደሚመስል እንመልከት፡፡

## 3.6.2 የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ መዋቅር ገጽታ

በድራሼ ብሔረሰብ የባህላዊ አስተዳደሩና የፍትህ ስርዓቱ ተዛምዶ የጠበቀ ነው፡፡ የፍትህ መዋቅሩ መነሻው የባህላዊ አስተዳደር መዋቅሩ ሆኖ በዚህ ቅርጽ ውስጥ በዋነኝነት የሚጠሩት ‹‹ዳማ››፣ ‹‹አራፋይታ›› (የንጉሱ ችሎት)፣ ‹‹ፓልዳ›› ሻላ/ሻና እና

አስማረ/የቤተሰብ መሪ/ ናቸው፡፡ እነዚህ መዋቅሮች በውስጣቸው ንዑስ ክፍሎችን በመያዝ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ይዳኛሉ፡፡

ቀደም ባለው የጥናቱ ክፍል እንደተጠቀሰው በድራሼ ብሔረሰብ የመጨረሻው የዳኝነት ችሎት ‹‹አራፋይታ›› የንጉሱ ችሎት ተብሎ የሚጠራው ነው፡፡ አራፋይታ የንጉሱ ችሎት አባላት ቁጥራቸው ከ7-12 ይደርሳል፡፡ የዚህ ችሎት አባላት ስልጣኑን የሚያገኙት እንደ ንጉሱ በዘር ሐረግ አይደለም፡፡ በማህበረሰቡ ካላቸው ተቀባይነት፣ ንቃተ ህሊና ነው፡፡ በአስተዳደራዊ ስልጣናቸው ሰፊውን የዳማውን /የንጉሱን/ ስልጣን ይጋራሉ፡፡ የዚህ ዋንኛው ምክንያት ዳማው እንደ አምልኮ መሪ ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ መሰሰ ማሞ፣ መስከረም 7/2008)፡፡

በዚህ በ ‹‹አራፋይታ›› ችሎት የሚቀርቡ ጉዳዮች የተመረጡና ለማህበረሰቡ የአብሮነት ህይወት አደጋ ናቸው ተብሎ የሚታሰቡ ችግሮች ናቸው፡፡ የተመረጡ ጉዳዮችም ቢሆኑ እንደ ስፋትና ጥልቀታቸው፤ ማህበረሰብ አቀፍ እና ግለሰባዊ መሆናቸው ተመዝኖ ዳማው (ንጉሱ) በችሎት እንዲገኝ ይደረጋል፡፡ ዳማው በአብዛኛው በግለሰቦች ጉዳይ አይገባም፡፡ የግለሰብ ጉዳዮች በታችኛው የፍትህ መዋቅር መፍትሔ ያገኛሉ፡፡

በዚህ ችሎት ከበድ ያሉ ውሳኔዎች ይወሰናሉ፡፡ በተለይ በቀደመው የድራሼ ብሔረሰብ የፍትህ ስርዓት ውስጥ የሞት ፍርድ፣ የአጥፊው ወገን ንብረት እንዲወድም ማድረግ የመሳሰሉት በዚህ የችሎት ደረጃ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ነበሩ፡፡ እነዚህ ውሳኔዎች በአብዛኛው ‹‹ዳማው›› በችሎት በአካል ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ ሌሎች ውሳኔዎች አራፋይታዎች በምክር በዳማው ስም የመወሰን ስልጣን አላቸው፡፡ በብሔረሰቡ የንጉሱ /ዳማ/ ውሳኔ ፍፁም ትክክልና ከመለኮታዊ ባህሪው በመነሳት የሚወስነው ውሳኔ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ (የቡድን ውይይት፣ መስከረም 5/2008)፡፡

የአራፋይታዎችም ይሁን የዳማው ውሳኔ በጋራ የተመከረበት ነው፡፡ በተለይም ከጎሳ መሪዎች /ፓልዳ/፣ ከሻና የመንደር መሪዎች የሚገኙ መረጃዎች ለውሳኔው መሰረቶች ናቸው፡፡ በዚህ ችሎት የሚወሰኑ ውሳኔዎች አጠቃላይ ማህበረሰቡን የሚመለከቱ ሊሆኑ ስለሚችሉ ጥንቃቄ ይደረግባቸዋል፡፡ በተለይም የሞት ፍርድ ሲሆን የጎሳው መሪዎች ስሜት፣ የተቀጪ ወገኖች ማንነት ከግምት ይገባል፡፡ የሞት ፍርድ ተፈፃሚ የሚሆነው

በሁለት መልክ ነው፡፡ አንዱ በስቅላት ሌላኛው ደግሞ በድንጋይ በመውገር፡፡ ይህንን የሚያስፈፅሙት የንጉሱ ችሎት አስፈፃሚዎች ‹‹ዋሎት›› ተብለው የሚጠሩት ናቸው፡፡

እነዚህንና መሰል ዳኝነቶች በዳማው ችሎት ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ ወሳኔዎች በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ካላገኙ በአራፋይታው ውስጥ ያሉ መሪዎች ችግር ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ምክንያቱም ንጉሱ ፍጹማዊ ተደርጎ ስለሚታሰብ ውሳኔዎቹ ስህተት እንኳ ቢሆኑ በአራፋይታው ውስጥ ያሉ መሪዎች ተንኮል ነው ይባላል፡፡ በመሆኑም ህዝቡ ለዳማው ጥያቄ ያቀርባል፡፡ ‹‹አራፋይታው ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ እያሳረፈ ነው፡፡ ህዝቡ አዝኗል ይውረድልን›› በማለት አቤቱታ ያሰማል፡፡ ንጉሱም ይህንን ተግባራዊ ካላደረገ ጋርዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ‹‹ጥንስስ ጦር[10]›› የሚባል ተቀላቢና የብሔረሰቡን ደህንነት ከውጭም ሆነ ከውስጥ የሚጠብቅ ጦር አለ፡፡

ይህ ጦር ጣልቃ በመግባት የአራፋይታ አባሎችን ከስልጣን ያወርዳል፡፡ በምትኩም ከማህበረሰቡ የተሻሉ የሚባሉትን በመሾም ፍትህዊ አሰራር እንዲኖር ያደርጋል (ቃለ መጠይቅ፣ ብሩ ሰማሎ፣ መስከረም 4/2008ዓ.ም) ፡፡

በዚህ ምክንያት የአራፋይታው አባሎች በሀቅ ላይ፣ በመረጃና ማስረጃ ላይ በመመስረት ያለ አድሎ የችሎት ስራዎችን ይሰራሉ፡፡ ህዝቡ ስለሚያስቀምጣቸው በታማኝነትና በቅንነት ያገለግላሉ፡፡ እነዚህ መሪዎች የስልጣን ገደብ አልተቀመጠላቸውም፡፡ ህዝቡን በታማኝነት እስካገለገሉ ድረስ እስከ ዕለተ ሞታቸው የመስራት ዕድል አላቸው፡፡ ይህ የአራፋይታ ችሎት በውስጡ የተለያዩ መዋቅሮችን ያቀፈ ነው፡፡ እነዚህም ፒሃ፣ ሆርቤና ዋሎት ይሰኛሉ፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ ከአስተዳደር መዋቅሩ ያሉ ፖልዳ ሼላ፣ ሻና እና ኦስማረ የፍትህ መዋቅሩ አካል ናቸው፡፡ እነዚህ የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ መሪዎች ሚናና የሚዳኟቸውን ጉዳዮች ቀጥሎ እንመልከት፡፡

---

[10] ጥንስስ ጦር፡- ይህ ጦር ራስ ልዑል ሰገድ አካባቢውን ሲቆጣጠሩ ከሞሲዬ ጦር ጋር በመሆን ከፍታኛ ተጋድሎ እንዳደረገ (ሐንሳሞ፣1993)ያስረዳሉ፡፡ጥንስስ ጦሩ የአራፋይታው ችሎት ህዝቡ ላይ የተዛባ ውሳኔ እንዳይሰጡ በዳማው አማካኝነት አራፋይታውን የመቆጣጠር ከስልጣንም የማውረድ ተግባር ይፈጽማሉ፡፡

### 3.6.3 በባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ የመዋቅሩ መሪዎች ሚና እና የሚዳኟቸው ጉዳዮች

**የፒሃ ሚና፡-** በዳማው ችሎት ውስጥ የሚከናወኑ አምልኮአዊ እና ባህላዊ ስርዓቶች የሚፈፅም የችሎቱ አንድ አካል ነው፡፡ ዳማው በቀጥታ በችሎቱ የተቀመጡ በዳይም ይሁን ተበዳይን መጠየቅ ክብሩን ይነካል ተብሎ ስለሚታሰብ ግንኙነቱ በ‹‹ፒሃ›› በኩል ያደርጋል፡፡ፒሃ ዳማው መጠየቅ የፈለጋቸውን ጉዳዮችና የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች ለችሎቱ ታዳሚዎች ያቀርባል፡፡ ፒሃ የንጉሱ አፍ በመሆኑ የዳማውን የመጨረሻ ቃል የሚያስተላልፈው እሱ ነው (የቡድን ውይይት፣ መስከረም 5/2008ዓ.ም)፡፡

**የሆርቤ ሚና፡-** ሌላኛው የዳማው ችሎት አባል ነው፡፡ ይህ የችሎት አካል ችሎቱ የወሰናቸው ውሳኔዎቸ ተፈፃሚ መሆናቸውን የሚከታተል ነው፡፡ በተለይም ውሳኔዎቹ በዓይነት (በሬ፣ እህል፣ የጉልበት ቅጣት) የመሳሰሉት ለንጉሱ የሚገቡ ከሆነ ተፈፃሚ መሆን አለመሆናቸውን ከጎሳ መሪዎች (ፓልዳ) ጋር በመሆን ተፈፃሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በዚህ ችሎት የሚወሰኑ ውሳኔዎች አጠቃላይ የጎሳ አባላትን እንደሚመለከት ስለሚቆጠር ተፈፃሚ የመሆን ዕድላቸው ሰፊ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተፈፅመው ባይገኙ እንኳ ለዳማው ሪፖርት የሚያቀርበው ይህ አካል ነው፡፡

**የዋሎት ሚና፡-** በዳማው ችሎት የእነዚህ አካላት ሚና የተወሰኑ ውሳኔዎች የሞት[11] ፍርድ፣ የንብረት ማውደም ቅጣት የመሳሰሉት ከሆኑ እነዚህ አካላት ተፈፃሚ ያደርጋሉ፡፡ የችሎቱ ውሳኔ የሞት ቅጣት ከሆነ በስቅላት ወይም ጋራዳ አካባቢ በሚገኘው ስፍራ በድንጋይ ወግሮ አልያም ወደ ገደል ጥሎ መቅጣት የእነዚህ አካላት ተግባር ነው፡፡ ዋሎቶች ከችሎት ውሳኔ አስፈፃሚነት ባለፈ እንደ ንጉስ ጠባቂ ናቸው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብሩ ሰማሎ፣ መስከረም4/2008)፡፡

---

[11]የሞት ፍርድ እንዲሁም በድንጋይ ወግሮ ወደ ገደል የመጣል ቅጣት በባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ ይፈፀሙ ከነበሩ ውሳኔዎች አንዱ ነበር፡፡ ይህም በተለምዶ ጋርዳ ተብሎ በሚጠራ ቦታ የሚፈፀም ሲሆን ይህ ቅጣት ከቀረ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ መሆኑን በቡድን ውይይት ወቅት የአገር ሽማግሌዎች ገልፀውልኛል፡፡

ሌላው በዚህ የባህላዊ ፍትህ መዋቅር ውስጥ ውሳኔ ከሚሰጡና በማህበረሰቡ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ከሚፈቱ መካከል ፓልዳ /የጎሳ መሪ/ ተጠቃሽ ነው፡፡

<u>የፓልዳ ሚና፡-</u> የጎሳ አባላት ማንኛውም ችግር ሲገጥማቸው መፍትሄ የሚያገኙት ከዚሁ ባህላዊ ስርአት መሪ ነው፡፡ ፓልዳው በጎሳው ውስጥም ሆነ ውጪ ለሚፈጠሩ ግጭቶች ኃላፊነት አለበት፡፡ በፍትህ ስርዓት ውስጥ በብሔረሰቡ የሚፈጠሩ እያንዳንዱ ጉዳዮች ወደ ዳማው ችሎት አይደርሱም፡፡ በየጎሳ መሪዎቹ መፍታትና መዳኘት ያለባቸው ጉዳዮች በፓልዳው የችሎት አደባባይ ‹‹ሞራ›› ያልቃሉ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብሩ ስማሎ፣ መስከረም 4/2008) ፡፡

በፓልዳው የችሎት አደባባይ የሚታዩ ጉዳዮች እንደ ዳማው ሁሉ የተመረጡና ከበድ ያሉ ግጭቶች ናቸው፡፡ የነፍስ ግድያ ወንጀል፣ የእርሻ ቦታ የድንበር ግጭት የመሳሰሉት የጎሳውን ማህበራዊ ህይወት አደጋ ላይ ይጥላሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ቀድሞ የሚታዩትና ውሳኔ የሚያገኙት በዚሁ የፍትህ ስርዓት ደረጃ ነው፡፡

በተለይ በሁለት የጎሳ አባላት መካከል ግጭቶች ተፈጥረው ከሆነ የግጭት ፈጣሪው ጎሳ መሪ ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ ሽማግሌዎችን ወደ ተጎጂው ጎሳ መሪ ዘንድ በመላክ ጉዳዩ በሽማግሌ እንዲታይ ያደርጋል፡፡ በዚህ አይነት የሚፈጠሩ ግጭቶች የሚታዩት ከሁለቱም ጎሳ አባላት በሚውጣጡ ሽማግሌዎች ይሆናል፡፡

በእነዚህ አካላት የማይፈታ ከሆነ ሁለቱ የጎሳ መሪዎች ተነጋግረው ለዳማው ችሎት ለ‹‹አራፋይታ›› እንዲቀርብ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ የችሎት መንበር የሚወሰኑ ውሳኔዎች የዳማውን ክብር ስለሚነኩ በጥንቃቄ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡ በዚህ ችሎት ጥፋተኛ የሆነው ጎሳ ቅጣቱን መቀበል ግዴታው ነው፡፡ የቅጣቶቹ ዓይነት የገንዘብ ወይም የከብት ክፍያ ከሆነ ሁሉም የጎሳ አባል በትብብር እንዲከፍሉ ይደርጋል፡፡ በጎሳው የአስተዳደር መዋቅር መሰረት ይህንን የሚያስተባብረው የፓልዳው አምልኮአዊ መሪ ‹‹ከዳይታ›› ተብሎ የሚጠራው ነው፡፡ በተለይ በዳማው ችሎት የሚሰጡ ውሳኔዎች የጎሳውን ክብር ጭምር የሚመለከት በመሆኑ ለውሳኔው ተፈፃሚነት ሁሉም የጎሳ አባል እርብርብ ያደርጋል፡፡

ከፓልዳው በታች ባሉ የዳኝነትና የግጭት መፍቻ እርከኖች ሼላ፣ ሻና እና ኦስማረ /የቤተሰብ መሪ/ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በተለይ ሼላ ና ሻና በአስተዳደር መዋቅር ውስጥ

የተለያየ ሚና ያላቸው ሲሆን በፍትህ ስርአቱ ወይም ግጭት በመፍታት ሂደት ውስጥ ሚናቸው ተመሳሳይ ነው፡፡

<u>**የሼላ/ሻና ሚና፡-**</u> በፍትህ ስርዓት ውስጥ ሚናቸው የሽምግልና እና የማስታረቅ ተግባር ነው፡፡ ሁለቱም መለኮታዊ ኃይል አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በተለይ ሻላ ከኮላይት፣ ኤላይት እና አርጋማይት ጎሳ የሚገኙ እና እነዚህ ጎሳዎች በብሔረሰቡ የተለዩና የተመረጡ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በሽምግልና ስርዓትም ውስጥ የ‹‹መሃላ›› ተግባርን የሚያስፈፅሙትም ሆነ ‹‹እርግማን›› የሚያደርሱት እነዚህ የባህላዊ ስርዓት አስፈፃሚዎች ናቸው፡፡

በአብዛኛው በአንድ መንደር ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮች እንደ ባልና ሚስት ፀብ፣ የጎረቤታሞች ግጭት የስርቆት፣ የስድብ የመሳሰሉት በዚህ መዋቅርና መሪዎች ታይተው መፍትሔ ያገኛሉ፡፡ በዚህ መዋቅር መፈታት ያልቻሉ ጉዳዮች ፓልዳው (የጎሳ መሪ) እንዲያይ ይደረጋል፡፡ የነፍስ ማጥፋት፣ ሰደድ እሳት በመፍጠር የሚፈጠሩ ግጭቶች በሼላና ሻና ደረጃ አይታዩም፡፡ በመሆኑም በፓልዳው የችሎት አደባባይ ‹‹ሞራ›› እንዲቀርብ ይደርጋል፡፡


ከሼላና ሻና በታች የሆኑ ቤተሰባዊ ጉዳዮች የሚታዩት በኦስማረ (በቤተሰብ መሪ) ነው፡፡ በድራሼ ብሔረሰብ ለቤተሰብ መሪ ኦስማረ /አፓ/[12] ትልቅ ክብር ይሰጣል፡፡ ቤተሰቡ እናትን ጨምሮ የሚመራው በኦስማረ ነው፡፡ የቤተሰቡ ራስ ተደርጎ ስለሚወሰድ ቃሉ ይታመናል ውሳኔው ይከበራል፡፡ በመሆኑም በወንድምና እህት፣ በልጅና በእናት፣ በአጎትና በአክስት መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ዳኝነት የሚሰጣቸው በኦስማረው /አፓ/ ነው፡፡ ኦስማረው /ኦፓ/ በጎሳ መሪዎቹም ዘንድ እውቅና ስላለው ቤተሰቡን የመቆጣጠር፣ የመምራት የመዳኘነትና የማስተማር ኃላፊነት አለበት (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ታደሰ ተሸባሌ፣ መስከረም 3/2008)፡፡

[12] አፓ በደራይታት አባት የሚለውን የአማርኛ ቃል ይወክላል፡፡ በፍትህ መዋቅሩ ኦሶማረ (የቤተሰብ መሪ) በመባል ይጠራል፡፡ በመሆኑም በቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን የመዳኘትና መፍትሔ የመስጠት ሀላፊነት አለበት

እነዚህ የድራሼ ብሔረሰብ ባህላዊ የአስተዳደርና የፍትህ ስርዓት መዋቅር በማህበረሰቡ የሚፈጠሩትን ግጭቶች ስርዓትና መልክ በማስያዝ ተደጋግፈው በመፍታት የተወሰኑ ዘመናትን ተሻግረዋል፡፡ የመዋቅራዊ ቅርጽና ይዘታቸውን ስንመለከት እርስ በራስ የተሰበጣጠሩ ነገር ግን የተለየ ሚና ያላቸው ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ከላይ በዝርዝር የቀረቡ የፍትህ ስርዓቱ መዋቅራዊ ቅርጽ ስዕላዊ በሆነ መልኩ ብንመለከት የበለጠ ግልጽ ይሆናል፡፡

**መዋቅር 2፡- የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ ቅርጽ**




**ምንጭ፡- በአጥኚው ከባህላዊ መዋቅሩ መነሻነት የተቀረጸ**

የባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱ የሚመሰረተው በባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ይህ የባህላዊ አስተዳደር መዋቅር ደግሞ 1890 ዓ/ም ጀምሮ እየተዳከመ መጥቷል (የቡድን ውይይት፣ መስከረም 5/2008ዓ.ም)፡፡ የባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱም ቀደም ሲል የነበረውን ዓይነት ጠንካራ ቁመናን ይዞ አናገኝም፡፡ በተለይ የዳማ (የንጉሱ) ችሎት አራፋይታ ሙሉ ለሙሉ አለ ማለት አይቻልም ከዚህ በታች ያሉ መዋቅሮች አሁንም በተግባር ላይ ናቸው፡፡ በእነዚህ መዋቅሮች አምለኮአዊ ስርዓቶች አሁንም ይፈፀማሉ፡፡ይሁን እንጂ በተለይ የፕሮቴስታንት እምነት በቦታው መስፋፋት ከጀመረ በኋላ አንዳንድ አምልኮአዊ ስርአቶች ተፈፃሚ እየሆኑ እንዳልሆነ የሀገር ሽማግሌዎች ይናገራሉ፡፡

ይህ ባህላዊ የፍትህም ሆነ የአስተዳደር መዋቅር በዘመን ታሪክ ውስጥ የተለያዩ ተጽዕኖዎችን ማለፍና መቋቋም ግድ ሆኖበታል፡፡ አብዛኞቹ የመረጃ አቀባዮቼ መደበኛው የፍትህ ስርዓት መምጣት፣ አስተዳደራዊ መዋቅር መዘርጋት፣ የተለያዩ እምነቶች መስፋፋታቸው ለመድከሙ ምክንያት እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ በአዜዎቹ፣ በደርግና አሁን ባለው ስርዓት የነበረውን በማነፃፀር የበለጠ የጨለመበትን ዘመን ከ1966-1983 እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ይህም ሆኖ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማንሰራራት እየታየበት ነው፡፡

በተለይም በመደበኛ የፍትህ ስርዓቱ ውሳኔ የተሰጣቸው ጉዳዮች ተመልሰው በማገርሸት ችግር እየሆኑ ሲመጡ በባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ ደግሞ እልባት እያገኙ መምጣታቸው የባህላዊ መዋቅሩ እንዲያገግም ምክንያት እየሆነ መጥተዋል፡፡ በዚህም መደበኛ የፍትህ ስርዓቱ የባህላዊ ዳኝነቱን የመፈለግ አዝማሚያ አሳይቷል፡፡ በመሆኑም አንዳንድ ግጭቶች የባህላዊ ስርዓት እርቅን መፈለግ ጀምረዋል፡፡

በዚህ ጥናት በባህላዊ ፍትህ ስርዓት ውስጥ የፓልዳ፣ የሼላ፣ሻና መዋቅሮች አሁን ድረስ በተግባር እንዳሉ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ‹‹ሞራ›› ላይ ቁጭ ብለው መፍረድ ውሳኔ መስጠት አሁንም ቀጥሏል፡፡ ከቀደመው ጊዜ የቀሩ ውሳኔዎች ውስጥ የሞት ቅጣት ብቻ ሲሆን እርግማን፣ ማግለል፣ ወሬታ[13] መክፈል ዛሬም ድረስ ይሰራባቸዋል፡፡

[13] ወሬታ በግጭት መካከል አጥፊ ሆኖ የተገኘ አካል ዳኞች በሚሰጡት ውሳኔ መሰረት ለተጎጂው ወገን የሚሰጠው የገንዘብ ወይም የአይነት የካሣ ክፍያ ነው፡፡

በተለይም ወሬታ መክፈል የጠነከረ ውሳኔ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ የዳማው ችሎት ‹‹አራፋይታ›› ባይኖርም በጎሳዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን ‹‹ዳማው›› ዛሬም ድረስ ተገኝቶ ይዳኛል፣ ያስታርቃል፡፡ የአራፋይታዎች ሚና የሀገር ሽማግሌዎች ይዘው እንዲቀጥሉ የተደረገ ይመስላል፡፡ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት እነዚህን ባህላዊ መዋቅሮች ጠብቆ ለማስኬድ ልዩ ልዩ አውደ ጥናቶችና የውይይት መድረኮችን ለማዘጋጀት ጥረት እንደሚያደርግ ማስተዋል ችያለሁ፡፡

## 3.6.4. የባህላዊ ግጭት መፍቻ ስርዓት

የድራሼ ብሔረሰብን ባህላዊ የአስተዳደርና የፍትህ ስርዓቱን መዋቅር ቅርጽ እንዲሁም የመሪዎቹን ሚና ተመልክተናል፡፡ በእዚህ ክፍል ደግሞ የግጭት መፍቻ ስርዓቱ፣ በስርዓቱ የሚታለፉ ሂደቶች እንዲሁም በባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ምን እንደሚመስሉ ከዚህ በታች ይቀርባሉ፡፡

### 3.6.4.1. ማስታረቅ፣ ማስማማት፣ መዳኘት፣ መቅጣት የባህላዊ ግጭት መፍቻ ስርዓት (አራርሳ /ሆሮታ/)

የድራሼ ብሔረሰብ በራሱም ውስጥ ሆነ ከሌሎች የአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር በሚኖረው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች የሚፈጠሩ ግጭቶችን የሚፈታበት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት አለው፡፡ ይህን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት ‹‹አራርሳ››ወይም ‹‹ሆሮታ›› በማለት ይጠራዋል፡፡ የቃሉም ትርጓሜ ማስታረቅ፣ ማስማማት፣ መዳኘት፣ መቅጣት የሚሉ ፍቺዎችን ይይዛል (ቃለ መጠይቅ፣ መሰለ ማሞ፣ መስከረም 7/2008ዓ.ም)፡፡

በ‹‹አራርሳ›› የፍትህ ስርዓት ውስጥ እንደ ግጭቶቹ አይነትና ደረጃ የተለያዩ ባህላዊ ስርዓቶችና ውሳኔዎች ይፈፀማሉ፡፡ እነዚህ ባህላዊ ስርዓቶችና ውሳኔዎች የሚሰጡት በዳማው ‹‹አራፋይታ› ችሎት፣ በፓልዳ የሽምግልና ተቋም፣ በሼላ/ሻና እንዲሁም በ‹‹ኦስማረ›› የቤተሰብ መሪ የእርቅ ስርዓት ነው፡፡ በመሆኑም በድራሼ ብሔረሰብ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች የሚፈጽሙት በዳኝነት፣ በእርቅና በሽምግልና ስርዓት ሲሆን እነዚህም የየራሳቸው መዋቅራዊ ስርዓት አላቸው፡፡

የነፍስ ግድያ፣ በሰደድ እሳት ንብረት ማውደም የመሳሰሉት ድርጊቶች በብሔረሰቡ በከባድ ወንጀልነት የሚታዩ የግጭት መከሰቻዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም እንደነዚህ አይነት ግጭቶች በ‹‹ዳማው›› (በንጉሱ) ችሎት ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡ አልፎ አልፎ የጎሳው መሪዎች /ፓልዳ/ ዎች እነዚህን መሰል ወንጀሎች የማየት ስልጣን አላቸው፡፡ ድንበር በመግፋት፣ በከብቶች ስምሪት የሚወድሙ ሰብሎች፣ በባልና በሚስት አለመግባባት የሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሄ የሚያገኙት በባህላዊ የሽምግልና ሥርዓት ነው፡፡ የሽምግልና ስርዓቱም ቢሆን የራሱ የሆኑ ሥርዓቶች አሉት፡፡ በተለይም በጎሳዎች መካከልና ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶች በልዩ እምነታዊና ባህላዊ የእርቅ ስርዓት መፍትሔ ያገኛሉ፡፡

ይህ የሽምግልና የእርቅ ስርዓት የሚከናወነው ‹‹ሞራ›› በተሰኘ የባህላዊ የዳኝነት ችሎት አደባባይ ነው፡፡ ‹‹ሞራ›› የዳኝነትና የፍርድ ችሎት ቦታ ሲሆን በአንድ ትልቅ ዛፍ ዙሪያ በድንጋይ ካብ ከፍ ተብሎ የተሰራ ይዞታነቱ የህዝብ የሆነ ቦታ ነው፡፡ ሞራን ለየት የሚያደርገው ህፃናትና ሴቶች በዚህ የችሎት አደባባይ ላይ መቀመጥ አለመቻላቸው ነው፡፡ በአከባቢው ማህበረሰብም የተከበረ ቦታ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡



**ምስል አንድ፡-** ሞራ ባህላዊ የዳኝነት ቦታ

### 3.6.4.2 በግጭት አፈታት ሥርዓቱ የሚታለፉ ሂደቶች

በድራሼ ብሔረሰብ በግጭት መፍታት ሂደት ውስጥ የሚታለፉ መሰረታዊ ደረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህ ደረጃዎች እንደ ግጭቱ አይነትና ስፋት የተለያዩ ቢሆኑም በይዘትም ይሁን በቅርጽ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ አንድ ጎሳ ከሌላ ጎሳ፣ አንድ ቤተሰብ ከሌላ ቤተሰብ ጋር ግጭት ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ የመጀመሪያ ተግባሩ ለቤተሰብ መሪ (ኦስማረ) አልያም (ለፓልዳ) ለጎሳ መሪ ክስ ማቅረብ ቀዳሚ ተግባሩ ነው፡፡ ይህ እንደ ወንጀሉ አይነት ቢለያይም በነፍስ ማጥፋት የተነሳ በሚፈጠሩ ግጭቶች አጥፊው ቀድሞ ወደ ፓልዳው (የጎሳ መሪ) ዘንድ በመሄድ እጅ ይሰጣል፡፡

ከዚህ በኋላ የወንጀል አይነቱን የማጣራት ሌሎች አጥፊዎችም ካሉ የመለየት ተግባር ይፈፀማል፡፡ ይህ በአብዛኛው የሚከወነው በመንደር መሪዎች ሼላ እና ሻና መዋቅር ውስጥ ባሉ መሪዎች ይሆናል፡፡ ወንጀሉ የተደበቀና ስውር ከሆነ የአውጫጪኝ ተግባር ይከናወናል፡፡ ወንጀል ፈፃሚው ከተገኘ ጉዳዩ በምስክር እንዲረጋገጥ ይደረጋል (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ካቶ ኩሾ፣ መስከረም 6/2008)፡፡ በሞራ የዳኝነት ሥርዓት ምስክሮችን በመቁጠር መከራከር ይቻላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በሰው ምስክሮችና በመሀላ የሚታሰሩ በመሆኑ በዳይም ሆነ ተበዳይ ከተፈፀመው እውነት ውጪ ዝንፍ አይሉም፡፡ ምክንያቱም በአምልኮ መሪዎች እርግማን ውስጥ ይወድቃሉ ተብሎ የሚታሰብ በመሆኑ ትክክለኛውን ነገር እንዲናገሩ ይገደዳሉ (የቡድን ውይይት፣ መስከረም 5/2008)፡፡

ግጭቶቹ የጎሳ ለጎሳ ከሆነ የበዳይ ጎሳ መሪ (ፓልዳ) ለተበዳይ መሪ ጎሳ ሽማግሌዎችን መላክ ይጠበቅበታል፡፡ ጉዳዩም የሚታየው ከሁለቱ ጎሳዎች በተውጣጡ ሽማግሌዎች ይሆናል፡፡ ይህን መሰል ግጭት ሲፈጠር ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም የማህበረሰቡን ህልውና አደጋ ውስጥ የሚከቱ ይሆናሉ ተብለው ስለሚታሰቡ፡፡በዚህ መሰረት የሁለቱ ጎሳ ሽማግሌዎች የነገሩን መሰረት በጥንቃቄ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ በተሰጠው ውሳኔ የማይስማማ ካለ ወደ ንጉስ ችሎት ‹‹አራፋይታ›› ይወሰዳል፡፡

በአጠቃላይ በድራሼ ብሔረሰብ በግጭት መፍታት ሂደት ውስጥ ግጭትን መጠቆም፣ ግጭትን ማጣራት፣ የግጭቱን ስፋትና ክብደት መመዘን፣ ውሳኔ መስጠት የባህላዊ ሥርዓቱ

የሚያልፍባቸው ሂደቶች ናቸው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የሚያልፉ የግጭት ዓይነቶች የሚወሰኑባቸውን የውሳኔና የቅጣት ዓይነቶች እንመልከት፡፡

### 3.6.4.3 የባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ውሳኔዎች

በባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ከሚወሰኑ ውሳኔዎች ዋና ዋናዎቹ ማግለል፣ እርግማንና ሞት ናቸው፡፡ እነዚህም ውሳኔዎች የራሳቸው የአፈጻጸም ሥርዓት አላቸው፡፡

**ማግለል፡-** ይህ ውሳኔ በአብዛኛው ተፈፃሚ የሚሆነው በፓልዳ /የጎሳ መሪዎች/ በሚይዟቸው ጉዳዮች ሲሆኑ ግለሰቡ ያጠፋውን ጥፋት ካላመነ እንዲሁም የተወሰነበትን ቅጣት ካልተቀበለ በማህበረሰቡ ሁሉ እንዲገለል ይደረጋል፡፡ በየትኛውም ማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ አይሳተፍም፡፡ ይህ ውሳኔ ጥፋተኛውን ግለሰብ ብቻ የሚመለከት ሳይሆን መላ ቤተሰቡን የሚያካትት በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ ስነ-ልቦናዊ ጫና ውስጥ ቤተሰቡ ሁሉ ይገባል፡፡ በመሆኑም የትኛውም የብሔረሰቡ አባል ወንጀል ቢሰራ ከፓልዳውና ከሽማግሌዎቹ ቃልና ውሳኔ ለመውጣት ጉልበት አይኖረውም፡፡ የማግለል ቅጣት ሁለት መልክ አለው፡፡ አንደኛው በጎሳ መሪና ሽማግሌዎች የሚከወን ሲሆን በሌላ መልኩ በቤተሰብ መሪው /ኦስማረ/ የሚደረግ ማግለል ነው፡፡

«ኦስማረው» በፍትህ ስርዓት ውስጥ እንደ አንድ ተቋም የሚታይ ነው፡፡ በመሆኑም ወንጀል የሰራው ከአንድ ቤተሰብ ሆኖ የጎሳ መሪውንም ሆነ የሽማግሌዎችን ቃል ካልሰማ ኦስማረው ጥቁር ድንጋይ በጥርሱ በመንከስ አርቆ ይወረውረዋል፡፡ ይህ ማለት እንደዚህ ድንጋይ ከቤተሰቡና ከጎሳው አውጥቸሀለሁ እንደ ድንጋይ ተወርውረህ ቅር የሚል መልዕክት አለው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ታደሰ ተሸባሌ፣ መስከረም፣3/2008 ዓ/ም) ፡፡

በመሆኑም በብሔረሰቡ የፍትህ ሥርዓት ውስጥ ይህ የቅጣት ውሳኔ በቁም የመሞትን ያህል ስለሚቆጠር የፍትህ ሰጪዎቹ ቃልና ውሳኔ ይከበራል፡፡

**እርግማን፡-** የድራሼ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር ስልጣን ሁለት መልክ ያለው ሲሆን አንዱ አምልኮአዊ ሌላኛው ደግሞ አስተዳደራዊ ነው፡፡ በዚህ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ዳማውን (ንጉሱን) ጨምሮ ካላይት፣ ሼላ፣ ሻና የመሳሰሉት የመዋቅሩ መሪዎች አምልኮአዊ (መለኮታዊ) ስልጣን አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በተለይም ሼላዎች ከፍ ካሉ ጎሳዎች የሚመረጡ ልዩ መንፈስን የማናገር፣ የማባረር ከፍም ሲል ህዝቡን በመናፍስት

ኃይል የመቅጣት ብቃት አላቸው ይባላል (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብሩ ሰማሎ፣ መስከረም 6/2008)፡፡ በመሆኑም በፍትህ ሥርዓት ውስጥ አንድ ግለሰብ ወይም ጎሳ ጥፋት አጥፍቶ የሚክድ ከሆነ በእነዚህ አምልኮአዊ መሪዎች አማካኝነት እንዲረገም ይደረጋል፡፡ እርግማናቸው ግለሰቡና ቤተሰቡ አብጠውና ፈንድተው እንዲሞቱ፣ በዘር ሐረጋቸው ሁሉ የቁምጥና በሽታ እንዲኖር፣ የሚዘሩትን እንዳያጭዱና የሚወልዱት እንዳያድግ ይረግማሉ፡፡ ይህ እንደሚደርስ በብሔረሰቡ በጽኑ ይታመናል (የቡድን ውይይት፣ መስከረም 5/2008)፡፡

በመሆኑም ይህ እርግማን ላለመቀበል ወንጀል የሰራ የብሔረሰቡ አባል የሰራውን ወንጀል ለዳማው፣ ለፓልዳውና ለሽማግሌዎች መናዘዝ የግድ ይሆናል፡፡ በብሔረሰቡም የቁምጥና በሽታ፣ አልያም የማይወልድ ቤተሰብ ካለ የአያት ቅድመ አያቶቹ እርግማን አለበት ተብሎ ስለሚታመን አንዳንድ አምልኮአዊ ሥርዓቶች ይፈፀማሉ፡፡

**ሞት፡-** ይህ ውሳኔ በፍትህ ስርዓት ውስጥ ከሚሰጡ ውሳኔዎች አንዱ ነው፡፡ ይህ ውሳኔ የሚሰጠው በብሔረሰቡ መሪ በዳማ የአራፋይታ ችሎት ነው፡፡ ይህ ውሳኔ በከፍተኛ ጥንቃቄና ጥናት የሚከናወን ነው፡፡ በተለይም እንዲህ አይነት ውሳኔዎች የሚሰጡት ለህብረተሰቡ ሰላምና የአብሮነት ህይወት አደጋ የሆኑ ግጭቶች ሲፈጠሩ፣ የብሔረሰቡን እሴቶችና ባህሎች የሚገፉ ተግባራት ከተፈፀሙ ውሳኔው ተግባራዊ ይሆናል፡፡የሞት ቅጣቱ የሚፈፀመው በስቅላት ወይም አጥፊው በድንጋይ ተወግሮ እንዲሞት ይደረጋል፡፡ ይህንንም የሚያስፈፅሙት የንጉሱ ችሎት አንዱ አካል የሆኑት ‹‹ዋሎት›› ተብለው የሚጠሩ ናቸው፡፡ **ወረታ /ክፍያ/፡-** በዚህ የውሳኔ አይነት ውስጥ የሚካተቱ ጉዳዮች ከባድ ወይም ቀላል ግጭቶች ሆነው ነገር ግን በጥፋት ደረጃቸው የማህበረሰቡን መሰረታዊ ባህሎች የማይጥሱ የጥፋት አይነቶች ውሳኔ ነው፡፡ ጠለፋ በዚህ ውሳኔ ውስጥ ከሚያልፉ ድርጊቶች አንዱ ነው፡፡ አንድ ጠላፊ ጠልፎ ሲወስዳት ቤተሰብ በሽምግልና ስርዓት ከተዳኘ በኋላ እንደ ሐብቱ መጠንና እንደ ሽማግሌዎቹ ውሳኔ ከ1-5 ከብቶች እንዲሁም እስከ አንድ ሺ ብር የሚደርስ ገንዘብ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ በሌላ መልኩ በሰደድ እሳት ንብረት ያወደመ፣ በእርሻ ቦታ ያለን ሰብል ያቃጠለ የገንዘብም የጉልበትም ቅጣት ይጣልበታል፡፡ የገንዘቡ መጠን እንደ ጠፋው ንብረት የሚወሰን ሲሆን በጉልበት እርሻውን ማረስ፣ የተዘራውን ማረም፣ ሲደርስ ማጨድ ሊወሰንበት ይችላል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ግጭቶቹ እርስ በእርስ የመደባደብ፣ ገንዘብ ወስዶ አለመመለስ ቤተሰብን የማዋረድ፣ የመሳደብ ጥፋቶች ከሆኑ ለሽማግሌዎቹ የዳኝነት የ‹‹ጨቃ›› መጠጫ በመክፈልና ይቅርታ በማለት የሚፈቱ ግጭቶችና የሚሰጡ ውሳኔዎች አሉ፡፡

## 4. የግጭት እሳቤ፣ የግጭት አይነቶች፣ ምክንያቶችና የአፈታት ሥርዓታቸው

የድራሼ ብሔረሰብ የራሱ ባህላዊ አስተዳደርና የፍትህ መዋቅር አለው፡፡ በዚህ ክፍል በእነዚህ ተቋማት ዳኝነት የሚሰጥባቸው የግጭት አይነቶችና ግጭቶቹ የሚፈጠሩባቸው ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ማሳያዎችን በመጥቀስ እተነትናለሁ፡፡ የድራሼ ብሔረሰብ ስለ ግጭት ያለው እሳቤ ምን እንደሚመስል በማየት በብሔረሰቡ ተዘውትረው የሚከሰቱ ግጭቶችን በመለየት በባህላዊ ሥርዓቱ እንዴት እንደሚፈቱ ከዚህ በታች አቀርባለሁ፡፡

በድራሼ ብሔረሰብ የሰውን ንብረት መውሰድ፣ ሰዎችን መግደል፣ መስረቅና መዋሸት ‹‹በዳውራ›› ባህል የተወገዘና የተረገመ ነው፡፡ የብሔረሰቡም የግጭት እሳቤ ከዚህ የሚመነጭ ነው፡፡ ብሔረሰቡ ግጭት የክፉ ዕድል፣ የመጥፎ መናፍስት ውጤት እንደሆነ ያምናል፡፡ በመሆኑም በግጭት አፈታት ሥርዓቱ ባህላዊ የአምልኮ ሥርዓቶች ይፈጸማሉ፡፡ በድራሼ ብሔረሰብ ግጭት የለውጥና የአዲስ አስተሳሰብ መነሻ ተደርጎ አይወሰድም፡፡ እንዲሁም የቀደምት አያቶችን ባህልና ወግ ባለማክበር የሚመጣ ውጤት እንደሆነ ይታመናል (የቡድን ውይይት፣ መስከረም 5/2008)፡፡ ይሁን እንጂ በአብሮነት ህይወቱ ግጭት አይቀሬ መሆኑን በመገንዘብ ባህላዊ የአስተዳደርና የፍትህ ተቋማትን በመመስረት በብሔረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ይፈታል፣ ልዩነቶችን ይዳኛል፡፡

### 4.1 የግጭት ዓይነቶችና አነሳሽ ምክንያታቸው

በድራሼ ብሔረሰብ የግጭት አይነቶች በአብዛኛው በድንበር መግፋት፣ በገንዘብ መካካድ፣ በጠለፋ፣ በሰው እርሻ ላይ ሆን ብሎ እሳት መልቀቅ፣ ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር በሚኖር ግንኙነት፣ ከብት በሌላኛው ብሔረሰብ እርሻ ውስጥ ገብቶ በመብላት፣ በነፍስ ማጥፋት፣ በይዞታ ይገባኛል ምክኒያት የሚከሰቱ ናቸው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ይልማ ከተማ፣ መስከረም 2/2008 ዓ/ም)፡፡

የእነዚህም ግጭቶች ሰበብ ዛቻ፣ ስድብ፣ ማዋረድ፣ መደባደብ፣ ሆን ብሎ ንብረትን በእሳት ማያያዝ፣ ግድያ ናቸው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብሩ ስማሎ፣ መስከረም 4/2008 ዓ/ም)፡፡በተለይ ከእነዚህ የግጭት አይነቶች ተደጋግመው የሚፈጠሩና በአካባቢው እንደ ከባድ ግጭት ተደርገው የሚታዩት ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚደረግ ግጭት፣ ከሌላ ጎሳ ጋር፣ በሰደድ እሳት ንብረት ማውደም፣ በጠለፋ ነፍስ ማጥፋት ዋንኛዎቹ እንደሆኑ የመረጃ አቀባዮች ይገልፃሉ፡፡

በተለይም ከአሌ፣ ከኮንሶ፣ እና ዘይሴ ብሔረሰብ ጋር ተደጋጋሚ ግጭቶች ይፈጠራሉ፤፡ከኮንሶ ብሔረሰብ ጋር በርካታ ግንኙነቶች ስላሉ ግጭቶቹ ከግለሰብ እስከ ጎሳ ሊዘልቁ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ሁለት ወንድማማች ህዝቦች ከቀላል የግለሰብ ፀብና አለመስማማት ጀምሮ እስከ ከባድ ግጭት የሚያስከትሉ የነፍስ ማጥፋት ግጭቶች ውስጥ የሚገቡበት ጊዜያት ነበሩ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በተደጋጋሚ የሚፈጠሩ ግጭቶች ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የግጭቶቹም ምክንያት በድንበር ይገባኛል፣ በከብት ግጦሽ ቦታና በሌሎች ፖለቲካዊ ይዘት ባላቸው ጥያቄዎች ነው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ዘላለም አምሳሉ፣ ሐምሌ 19/2007 ዓ/ም)፡፡

ተዘውትረው ከሚፈጠሩ የግጭት ዓይነት አንዱ በሰው እርሻና ንብረት ላይ እሳት መልቀቅ ነው፡፡ ይህ ከከባድ የግጭት ዓይነት የሚመደብ ሲሆን በብሔረሰቡ የእርሻ ጥበብ የመሬት ውስጥ ጎተራ አዘጋጅቶ ለረዥም ጊዜ ማቆየት የተለመደ ነው፡፡ በዚህ የመሬት ውስጥ ጎተራ የሰደድ እሳት መልቀቅ በአካባቢው የግጭት መነሻ ሲሆን በአንድ ወቅት የተከሰተውን ድርጊት እንዲህ ሲሉ አቶ ታደሰ ተሸባሌ አጫውተውኛል፡-

> በለተምዶ አጠራሩ ‹‹ሽሌሌ›› በሚባልበት ሥፍራ የአርጋማይት ጎሳ አባል የሆነ አሁን ስሙን የማላስታውሰው አንድ ግለሰብ መጠጥ ቤት (ጨቃ ቤት) ዘሎ በመግባት በቤት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ስማቸውን እየጠራ ልክ ልካቸውን ይነገር ጀመር፡፡ ብዙዎቹ አባቶች ስለነበሩ እባክህ ተው ነውር ቃል ከአፍ አይውጣ ቢያንስ በዕድሜ እንበልጥሀለን በማለት ይገስጹት ጀመር፡፡ ይሁን እንጂ ግለሰቡ ስድቡንና ዘለፋውን ማቆም አልቻለም፡፡ በዚህ መካከል በዕድሜው ወደ ጎልማሳዎች ውስጥ የሚጠጋ ኩስያ የተባለ ግለሰብ ንዴቱን መቆጣጠር አቅቶት ይህንን ተሳዳቢ በያዘው ዱላ ወገቡን ይለዋል፡፡ ተመችውም መሬት ላይ ይወድቅና ተነስቶ ለያዥ ገላጋይ ያስቸግራል፡፡ በአካባቢው ያሉ ሰዎች ሁለቱን ሰዎች ይገላግላሉ፡፡ ተመችውም እሰራልሀለው ብሎ በመዛት ወደ ቤቱ ይሄዳል፡፡ ይህ በተፈጠረ በሁለተኛው ቀን ቆላ የሚገኘው የኩስያ የእህል ጉድጓድ መቃጠሉ ተሰማ፡፡ የአካባቢው

ሰዎችም የተፈጠረውን ያውቃሉና ይህን ያደረገው ኤክሌ ነው አሉ፡፡ በሽማግሌዎችም ተይዞ ተጠይቀ፡፡ አልካደም፡፡ ለምን አደረክ ተባለ? በሰው ፊት ደብድቦ አዋረዶኛል በዚህም ልበቀለው ይህንን አደረኩ አለ፡፡ ኩስያ ካልገደልኩት ቢልም ሽማግሌዎች ገዘቱት፡፡ ሽምግልና ይግቡ ተባለ፡፡ ሰውየው መናጢ ደሃ ነበርና የሚከፈለው የለውም፡፡ ሽማግሌዎችም ያጠፋውን በጉልበት ይካስ በእርሻ፣ በአረምና በአጨዳ ወቅት በነፃ የጉልበት አገልግሎት ይስጥ ብለው ወሰኑ፡፡ ኩስያም የሱ ጉልበት የቱን ያህል ይጠቅመኛል ዳግመኛ እንዲህ አይነት እንዳይፈፅም በኔ በኩል ይቅር ብየዋለሁ ባይሆን ሽምግልናውን ይክፈል በማለት አጥፊውም የሽምግልና ክፍሎ በመካከላቸው እርቀሰላም ወረደ (ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም 3/2008)፡፡

በድራሼ ብሔረሰብ እንዲህ እና መሰል የግጭት ምክንያቶችና እንዲሁም እርቆች ይከናውናሉ፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ ተፈፃሚ የሚሆኑ ስርዓቶችና ሂደቶች አሉ፡፡ በተለይም አንድ ጎሳ ከሌላ ጎሳ አባል ጋር ከባድ ግጭት ውስጥ ቢገባ ጉዳዩ ከፍ ባሉ የባህላዊ ስርዓቱ መሪዎች ፓልዳና ዳማ የሚታዩ ይኖራሉ፡፡ በአካባቢው ሽማግሌዎች የማይፈቱ እንደ ግጭቶቹ አይነትና ስፋት የሚለያይ እንደሆነ ቁልፍ መረጃ አቀባዮቹ ይገልፃሉ፡፡ እንደእነዚህ አይነት ግጭቶች በአብዛኛው ከጥቅም ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ድንገት ባልታሰበ ሁኔታ የሚፈጠሩ የነፍስ ማጥፋት ግጭቶች ይኖራሉ፡፡ እንደእነዚህ አይነት የግጭት ሰበቦች በባህላዊ ዳኝነት ሂደትም በሚሰጡ ውሳኔዎች ሆን ተብለውና በድንገት መሆናቸው ተመርምሮ ውሳኔዎች እንዲቀሉ እንደሚደረግ አቶ ካቶ ኩሽ የሚከተለውን ታሪክ አንስተው እንዲህ ሲሉ ገልጸውልኛል፡-

አሁን በቀደም ከሁለት ሳምንት በፊት አንድ ሽምግልና ነበር በማለት ጀመሩ ጣቂጣይታ የተባለ አንድ ወጣት እርሻ ቦታ ውሎ ምሽቱ ላይ ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ ደክሞት ነበርና በቤቱ ደጃፍ ባለ ድንጋይ ላይ አረፍ እንዳለ ከወደ ዳገቱ ላይ ጩኸት ይሰማና ወደዚያው እየገሰገሰ ይሄዳል፡፡ በዳገቱ ላይም የሰፈሩ ወጣቶች በዱላ ይተላለቃሉ፡፡ የዚህም ግጭት ምክንያት በሴት ነው ይላሉ አልታውቀም እንጂ ጣቂጣይታም የሰፈሩ ልጆች ናቸውና ለግልግል መሀል ይገባል፡፡ በዚህ ጊዜ አንዱ በጸብ ውስጥ ያለ ይመስለውና ዱላ ይሰነዝርበታል፡፡ ዱላውም ሳያገኘው ያልፋል፡፡ ጣቂጣታ ዱላ የሰነዘረበትን ሰው ገፋ ሲያደርገው ይወድቃል፡፡ ሲወድቅ ድንጋይ አናቱን ያገኛል፡፡ ወጣቱም ህይወቱ ያልፋል፡፡ በአጋጣሚ ሟች የኮላይት ጎሳ አባል ነው፡፡ ጣቂታ ደግሞ የእኔ ጎሳ አባል (ካላየይት) ከፍተኛ ግርግር ተፈጠረ፡፡ አካባቢው ተረበሸ ማን ገደለው? ተባለ ለጊዜው ቢሰወርም ጣቂታ ለፖሊስ እጁን ሰጠ፡፡ ለኛም ጉዳዩን አስረዳን፡፡ (ለኛ ያሉት የጎሳ መሪ ስለሆኑ ነው) የኋላ

ኋላ ወጣቶቹም እሱ በቦታው እንዳልነበረ ተናገሩ፡፡ እርሻ ቦታ መዋሉንም ያዩ ሰዎች አስረዱ፡፡ የሁለቱም ጎሳ ቤተሰቦች መረጋጋት አሳዩ፡፡ ከፍተኛ ውጥረት ነበር፡፡ ህግ ግን አለቀቀውም 7 ዓመት ፈረደበት፡፡ ይኸው ባለፈው ሳምንት ፍርዱን ጨርሶ ወጣ፡፡ የሁለቱ ጎሳ ቤተሰቦች አብረው የሚኖሩ ናቸው እና የጎሳ መሪዎችና ሽማግሌዎች ተሰባስበን ይቅር አሰኘናቸው (ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም 4/2008 ዓ/ም)፡፡

ከላይ የተገለፀው በብሔረሰቡ ከባድ የግጭት ዓይነት ውስጥ የሚመደብ ነው፡፡ ለዚህም ነው በጎሳ መሪዎች እንዲታይ የሆነው፡፡ ግጭቱ ደግሞ ልዩ ትኩረት የተሰጠው የሁለቱ ግለሰቦች ጎሳ የተለያ መሆን እያደር ቂም ተይዞ ወደ ሌላ ደም ማፋሰስ ውስጥ እንዳይገባ እንደሆነ አቶ ካቶ ኩሹ ጨምረው ገልፀውልኛል፡፡

በብሔረሰቡ ቀላል ግጭቶች በዚያው በመንደር መሪ ሼላና ሻና ሲያልቁ የቤተሰብ ግጭቶች ደግሞ በቀላሉ በቤተሰብ መሪው ኦስማረ መፍትሄ ያገኛሉ፡፡ ሂደቱም ቀላልና ከመገሰጽና ከመምከር ያለፈ አይሆንም፡፡ የነፍስ ግድያና መሰል ከባድ ጥፋቶች የሚፈቱበት መንገድና ሂደት ውስብስብ እንደሆነ መረጃ አቀባዮቼ ይገልፃሉ፡፡ ይህም መነሻው ብሔረሰቡ በጎሳ በመንደር፣ በማህበራዊ አደረጃጀት የተለያየ በመሆኑ ግጭቶች ሲፈጠሩ ከእነዚህ ጉዳዮች ጋር የማዛመድ እና መሰረቱ ምንድነው? የሚለው ነጥብ ሁሉንም አካል የሚያሳስብ በመሆኑ እንደሆነ ሽማግሌዎች ይገልፃሉ፡፡

በሌላ መልኩ ማህበረሰቡ በእለት ተዕለት ህይወቱ ውስጥ ከብቶችን ማሰማራትና ማገድ አንዱ ተግባሩ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአብዛኛው የሚከወነው ዕድሜያቸው ከ7-13 ዓመት ባሉ ልጆች ነው፡፡ እነዚህ ልጆች ጨዋታ ያታልላቸውና እረኝነቱን ችላ ይሉታል፡፡ ከብቶቹም እህል በተዘራ ወቅት ከሆነ በሰው ማሳ በመግባት የተዘራውን እህል እንዳልነበረ ያደርጉታል፡፡ በዚህ ሁኔታ በአንድ ወቅት የተከሰተውን ድርጊት እንዲህ ሲሉ አቶ መለሰ አውግተውኛል፡-

> አቶ ዳትኮ የተባሉ የከላይት ጎሳ አባል የሆኑ ግለሰብ ከእርሻ ስራቸው ጎን ለጎን በከብት እርባታ የሚታወቁ ታታሪ ሰው ናቸው፡፡ በአንድ ወቅት ታዲያ ከብቶቻቸው ከተሰማሩት ስፍራ መጥፋታቸውን ይሰሙና ከወንድ ልጆቻቸው ጋር በመሆን ፍለጋ ይወጣሉ፡፡ እጅግ መሽቶ ስለነበር ፍለጋቸው ሳይሳካ እረኛውን እየረገሙ ወደ ቤት ይመለሳሉ፡፡
>
> እንቅልፍ በአይናቸው ሳይዞር ማልደው በመነሳት ፍለጋውን ይቀጥላሉ፡፡እስከ ረፋድም ከብቶቹን አየሁ የሚል ይጠፋል፡፡ ተስፋ በመቁረጥ ወደ ቤታቸው በመመለስ ላይ እያሉ

ከቤት አንዷ ልጃቸው ከብቶቹ ‹‹ጋንድገማ›› በተባለ ስፍራ መገኘታቸውን ነገር ግን የሰውን እህል እንዳጠፉ ትነግራቸዋለች፡፡ አቶ ዳትኮም ወደ ተባለው ስፍራ እየገሰገሱ ይሄዳሉ፡፡ በአካባቢው ደርሰው ሲያጠያይቁ በጥቆማ በጥቆማ የተባለበት ስፍራ ይደርሳሉ፡፡ ዛፉ በተባለ ግለሰብ ማሳ ውስጥ የተዘራውን የበቆሎ ሰብልን እንዳልነበረ ሲያደርጉት አድረዋል፡፡ የአካባቢው ሰው ተሰብስቦ ግማሹ ያፅናናል ግማሹ ጉድ!! ጉድ!! እያለ የተፈጠረውን ያዳምቃል፡፡ ከብቶቹም በአንድ አካባቢ እንዲታገቱ ተደርጓል፡፡ አቶ ዳትኮም የተፈጠረው ነገር ተፈጥሯል ሽማግሌዎች ይዩልንና ‹‹አፋ ላማ እከፍላለሁ›› በማለት ለአካባቢው ሽማግሌዎች ተማጽኖ አቀረቡ፡፡ ሽማግሌዎችም አቶ ዛፉን በመያዝ እንግዲህ የከብቶቹም ባለቤት ተገኝቷል፡፡ ሆን ተብሎ የተደረገ አይደለም፡፡ ይኸው እሱም ‹‹አፋ ላማውን›› እከፍላለሁ እያለ ነው፡፡ስለዚህ ጉዳዩን በሽምግልና እንጨርሰው በማለት ያስማሙ ጀመር፡፡ አቶ ዛፉም ልፋታቸው እየታያቸው ነገሩ አልዋጥ ቢላቸውም ምርጫ የላቸውምና በሽማግሌዎቹ ሀሳብ ተስማሙ፡፡ቀንም ተቆረጠ፡፡ ሁለቱም ወገኖች ሽማግሌዎችን መረጡ፡፡ጉዳዩም በሁለቱም ሽማግሌዎች ተመረመረ፡፡ የአቶ ዛፉ ድካም ሰብሉ ደርሶ ለገበያ ቢቀርብ የሚያወጣው የገንዘብ መጠን የመሳሰሉ ጉዳዮች ታዩ፡፡ ሆነ ተብሎ የተደረገ ሳይሆን በከብት እረኞቹ ቸልተኝነት እንደሆነ ይህ ጥፋት እንዳይደርስ አቶ ዳትኮም በዕለቱ ከልጆቻቸው ጋር ሲፈልጉ ማደራቸው በሽምግልናው ግራ ቀኝ ታየ፡፡ በመጨረሻም 2000 ሺ ብር እና ለዘር የሚሆን አንድ ‹‹ስልቻ›› በቆሎ ‹‹አፋ ላማ›› እንዲከፍሉ ለሽማግሌዎች ደግሞ የ‹‹ጨቃ›› 50 ብር እንዲጥሉ ተወሰነ፡፡ አቶ ዳትኮም የሽማግሌዎቹ ውሳኔን እንደሚቀበሉ ነገር ግን ሁለት ሺ ብር የተባላው ወደ 1500 ብር ዝቅ እንዲልላቸው ጠየቁ፡፡ ሽማግሌዎቹም ጉዳዩን መርምረው የተባለውን አንድ ስልቻ የዘር በቆሎ 1500 ብር ለጠፋው ሰብል መተኪያና ‹‹50›› ብር ለሽማግሌዎች ጨቃ መጠጫ ወስነው እርቀ ሰላም እንዲወርድ ተደረገ (ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም 7/2008 ዓ/ም)፡፡

በዚህ መሰረት የሁለቱ ግጭት በሽማግሌዎች ዳኝነት መቋጫ ማግኘት ችሏል፡፡ በአብዛኛው ለሽማግሌዎች (ጨቃ) መጠጫ የሚባለው ሁለቱን ባላንጣዎች ለማቀራረብና ችግሩን ከመፍታት ባለፈ በአንድ ማዕድ እንዲቋደሱና እንደ ቤተሰብ እንዲተያዩ ለማድረግ እንደሆነ አቶ መለሰ ገልፀውልኛል፡፡ ይህም አልፎ አልፎ አንዳንድ ጉዳዮች በሽማግሌዎች እርቅና ሰላም እንዲወርድ ከተደረገ በኋላ ቆይቶ በሌላ ጊዜ ያገረሻል፡፡ እንዲህ እንዳይሆን በእርቅ ጊዜ ሁለቱ ወገኖች አብረው በጋራ ማዕድ እንዲቋደሱ ለማድረግ እንደሆነ ይነገራል ይህን ካለፈ እንደ ጉዳዩ ዓይነት የጎሳ መሪዎች እንዲያዩት የሚደረግበት ጊዜ እንዳለ መረጃ አቀባዮቹ ይገልፃሉ፡፡

በቤተሰብ ደረጃ የሚፈጠሩ የግጭት ዓይነቶች የሚፈቱት ቀደም ሲል እንደተገለፀው በኦስማረ /አፓ/ የቤተሰብ ኃላፊ ነው፡፡ አብሮ በሚኖር ቤተሰብ ውስጥ አለመስማማቶች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ አለመስማማቶች ገንዘብ በመውሰድ፣ በስድብ፣ የአንዱን ዕቃ ሌላኛው በመውሰድና በሌሎችም የግጭት ምክንያቶች አለመግባባቶች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ለኦስማረው /አፓ/ በተዘዋዋሪ በእናት በኩል የተፈጠረው አለመግባባት እንዲቀርብ ይደርጋል፡፡ ይህ ማለት ክስ እንደማቅረብ ይወሰዳል፡፡ የክሱ አቀራረብ የራሱ የሆኑ መንገዶች አሉት፡፡ ኦስማረው ከእርሻ ቦታ እንደመጣ አሊያም ወደ ቤት እንደገባ አይነገረውም ምክንያቱም በብሔረሰቡ ባህል ‹‹ውጪ የዋለ ድካሙን እቤት ያሳርፋል›› ስለሚባል ምግብ ቀርቦለት እግሩን ታጥቦ አረፍ ካለ በኋላ እንደ ግጭቱ አንገብጋቢነት ቤተሰቡ ሳይተኛ እንዲነገረው አሊያ ግጭቱ ፋታ የሚሰጥ ከሆነ ቤተሰቡ ከተኛ በእናት አማካኝነት ይነገረዋል፡፡ በአብዛኛው ይህ የሚሆነው ቤተሰቡ ለኦስማረ ልዩ ክብርና ቦታ ስለሚሰጥ ነው፡፡ የቤተሰብ መሪ (ኦስማራው) የተፈጠረውን ግጭት እንደሰማ ወደ ውሳኔና ማስታረቅ ሂደት አይገባም፡፡ ተጋጬ የተባሉትን የቤተሰቡን አባላት አንድ በአንድ ተራ በተራ እያስጠራ ይጠይቃል፡፡ የሁለቱንም ሀሳብ ይሰማል፡፡ ቀደም ሲል በቤተሰቡ እናት ከሰማው ጋር ያመዛዝናል፡፡ በመጨረሻም የሚያስማማበትን ብልሀት ይፈልጋል፡፡ በኦስማረ /አፓ/ የፍትህ ስርዓት ውስጥ በአብዛኛው በመግባባት፣ በማስታረቅና በማስማማት የቤተሰቡን ሰላም ጠብቆ ማስቀጠል እንደሆነ አቶ ታደሰ ተሸበሌ በአንድ ቤተሰብ ውስጥም የሆነውን እንዲህ ሲሉ አውግተውኛል፡-

*ታላቅና ታናሽ በአካባቢቸው ወደ ተዘጋጀው ሰርግ ለመሄድ ይሰነዳዳሉ፡፡ ታናሽየዋ ለሰርጉ መዋቢያ ካሰነዳዳቸው የአንገት ጨሌዋ መካከል አንዱ ይጠፋል፡፡ የእህቷን የአንገት ጨለዎች ስትመለከት ከጠፋው ጨሌ ጋር ተመሳሳይ በአንገቷ አጥልቃለች፡፡ ጨሌየን ወስደሻል? ለምን ወሰድሽ? አለቻት፡፡ ታላቅም የምትቀልድ እንጂ እውነቷን አልመሰላትም እና ስላማረብኝ የሚል ምላሽ ትሰጣለች፡፡ ታናሽም አውልቂ ብላ ወጥራ ትይዛታለች፡፡ ታላቅም እንዳመረረች ይገባት እና እንዳልወሰደችባት ይህንን ትላንት እንደገዛች ምላ ተገዝታ ታስረዳለች፡፡ ታናሽ አላመነችም አንገቷ ላይ ያለውን ጨሌ ለመውሰድ ትታገላት ጀመር፡፡ በዚህ በዚህ መሀል ጨሌው ይበጠሳል፡፡ ታላቅም ትናደድና በጥፊ ትላታለች፡፡ ታናሽም እልኸኛ ነበረችና ፊቷን በሁለት እጆቿ ትቧጭራለች፡፡ በዚህ መሀል ላይ ሌሎች የቤተሰቡ አባላት ይመጡ እና ይገላግሏቸዋል፡፡ ሰርጉንም መሄድ ይቀርና ተኳርፈው ያመሻሉ፡ አባት ማታ አመሻሽቶ ሲመጣ የሆነው ሁሉ ይነገረዋል፡፡ ማታ ምንም አላላቸውም ጠዋት በማለዳ ታናሽቱን ጠርቶ ጠየቃት የተነገረውን በድጋሚ ሰማ፡፡ ታላቅ*

ተጠራች ወስደሽበታል? አልወሰድኩም፡፡ በማለት በመሃላ አረጋገጠች፡፡ አባት ግራ ገባው በድጋሚ ታናሽ ተጠራች በእርግጥ እንደዚህ ዓይነት የአንገት ጨሌ ነበረሽ? አዎ አለች በቁጭትና በእህልህ ውስጥ ሆና፡፡ አባት ዘዴ ዘየደ፡፡ እናታቸውንም ጠርቶ አንድ ነገር ሹክ አላት፡፡

ከቀናት በኋላ ቤተሰቡ ሁሉ በተሰባሰበበት እናት ከሌላኛው ቤት እየገባች ይህ ደግሞ የማነው? እዚህም እዚያም ትጥሉና ነገ ትባላላችሁ? ስትል ታናሽየው ተነስታ የኔ ሳይሆን አይቀርም አለች፡፡ የታላቋን ስታይ አድርጋዋለች፡፡ በሆነው ነገር አፈረች፡፡ አባትም በይ እህትሽን ይቅርታ ጠይቂ አላት፡፡ አባትና እናት በጆሮ የተንሾካሾኩት ተመሳሳዩን በመግዛት ሁለቱን ማስታረቅ ነበር፡፡ በዚህ ብልሃት አባት ሁለቱን ልጆች አስማምቷል (ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም፣ 3/2008 ዓ/ም)፡፡

በቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶች በመነሻ ሰበባቸው አነስተኛ የቤተሰቡን ሰላም በማደፍረስ ግን ከፍተኛ የሚሆኑባቸው ጊዜያት አሉ፡፡ እነደዚህ ዓይነት ግጭቶች ታዲያ በድራሼ ብሔረሰብ ከቤተሰቡ መሪ አስማረ አያልፍም፡፡ይህ የቤተሰቡ መሪ ደግሞ በጥበብና በብልሃት የቤተሰብ አባላት በሙሉ የመምራትና የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት፡፡ ከረር ያሉ የቤተሰቡ ግጭቶች ሲሆኑ የመንደር መሪዎች እንደ ሼላ ወይም ሻና የሚገቡባቸው ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ ይህም የሀብት ክፍፍል አልያም አባት ወደ አንድ ልጁ አድልቶ የእርሻ መሬት ለሌሎቹ ካላዳረሰ የመሳሰሉ ጉዳዮች ወደ መንደር ሽማግሌዎች የሚሄዱበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ይህም ቢሆን በመጀመሪያ ለጎሳው የአምልኮ መሪ ሼላ ይደርሳል፡፡ ይህ የአምልኮ መሪ ‹‹ሼላ›› ለጎሳው አባላት የቀረበ የመንደር መሪ ተደርጎ ስለሚወሰድ ለህይማኖት አባት ወይም መሪ እንደመንገር ይቆጠራል፡፡ ሼላውም ቢሆን በቀጥታ ወደ ቤተሰቡ አይገባም፡፡ የቤተሰቡን መሪ አሊያም ደግሞ ለቤተሰቡ ትልቅ ሰው ለሚባል ችግሩን እንዲፈቱ ያሳስባል፡፡

በዚህ መንገድ ለመጣ የቤተሰብ አለመግባባቶች አስማረው በፍጥነት ለመፍታት ይጥራል፡፡ ምክንያቱም የራሱንም ሆነ የቤተሰቡን ክብር ይነካል፡፡ በመሆኑም የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ይሞክራል (የቡድን ውይይት፣መስከረም 5/2008 ዓ/ም)፡፡

ከዚህ በላይ በድራሼ ብሔረሰብ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ የግጭት ዓይነቶችና ሰበበ ምክንያታቸውን በተወሰነ መልኩ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ አንዳንድ አብነት የሚሆኑ በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያየ ጊዜ ተፈጥረው የነበሩ ግጭቶችን በማንሳት ተወስቷል፡፡

እነዚህ ግጭቶች ሲፈቱ በየእራሳቸው ተቋም እንደሆነ በጥናቱ ቀዳሚ ክፍል ተገልጿል፡፡ ግጭቶቹም መፍትሔ የሚያገኙት የየራሳቸው ባህላዊ ስርዓቶችንና ደንቦችን ተከትለው ነው፡፡ በመሆኑም በብሔረሰቡ በዋነኛነትና በተደጋጋሚ የሚፈጠሩ የግጭት ዓይነቶችን በመለየት የሚፈቱበትን ሂደት ወይም ሥርዓት ከዚህ በመቀጠል እንመልከት፡-

## 4.2. ዋና ዋና የግጭት ዓይነቶችና የአፈታት ስርዓታቸው

የድራሼ ብሔረሰብ በውስጡም ሆነ ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የተለያዩ ግጭቶች ውስጥ ይገባል፡፡ የሚፈጠሩ ግጭቶችንም በራሱ መንገድና ብልሃት ይፈታል፡፡ በብሔረሰቡ ከሚፈጠሩ የግጭት ዓይነቶች የነብስ ማጥፋት የጠለፋ፣ የጎሳ፣ ከአጎራባች ብሔረሰብ ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶች ዋነኛ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በዚህም ክፍል በብሔረሰቡ የሚፈጠሩ ዋና ዋና ግጭቶችና እነዚህን ግጭቶች የሚፈታበት ባህላዊ ስርዓት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 4.2.1 የነፍስ ማጥፋት ግጭት የአፈታት ሥርዓት

ነፍስ ማጥፋት በድራሼ ብሔረሰብ በዳውራ የማስተማር ባህል እጅግ የተወገዘ ተግባር ነው፡፡ ይህም ሆኖ በአካባቢው በተለያዩ ምክንያቶች በነፍስ ማጥፋት ግጭቶች ይፈጠራሉ፡፡ በብሔረሰቡ ባህል ይህ የግጭት ዓይነት የራሱ የሆነ ሂደትና ግጭቱ የሚፈታበት ሥርዓት አለው፡፡ በጥናቱ ክፍል ሁለት እንደተገለፀው በነፍስ ማጥፋት የሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሄ የሚያገኙትና ዳኝነት የሚሰጥባቸው በሁለት ባህላዊ የፍትህ ተቋማት ማለትም ‹‹በዳማው›› አራፋይታ ችሎት እና በፓልዳው (የጎሳ መሪ) ብቻ ይሆናል፡፡ በሼላ እና ሻና ደረጃ የነፍስ ግድያ ግጭት መፍትሄ አይሰጥባቸውም፡፡ በዚህ መሰረት በብሔረሰቡ በነፍስ ማጥፋት የሚፈጠር ግጭት የሚፈታበትን ባህላዊ ሥርዓተ ሂደት እንመልከት፡፡

በድራሼ ብሔረሰብ አንድ ግለሰብ በስህተትም ይሁን ሆን ብሎ የአንድን ግለሰብ ሕይወት ካጠፋ ወደ ጎሳ መሪው ቤት በመሄድ ‹‹ኤርጋዳማ›› በማለት ለጎሳ መሪው ይገልፃል፡፡ ይህ ማለት ነፍስ በእጄ ጠፍታለች እኔም እጄን ሰጥቻለሁ፡፡ ማለት እንደሆነ የመረጃ አቀባዮቹ ይገልፃሉ፡፡ በጥንታዊ የድራሼ ባህል ነፍስ ያጠፋ ሰው በችሎት አደባባይ (ሞራ) ባለው ዛፍ ውስጥ ዘሎ ከገባ የሚያሳድዱት እንኳ ቢኖሩ እጁን እንደሰጠ ስለሚቆጠር አይነካም (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ መሰለ ማሞ፣ መስከረም 7/2008 ዓ/ም)፡፡

ይህ ባህል እየቀረ በመምጣት የትኛውም የብሔረሰቡ አባል ወደ ጎሳው ቤት በመሄድ ‹‹ኤርጋዳማ›› ይላል፡፡ በፓልዳው ቤት ሄዶ እጁን የሰጠ ጥፋተኛ ጥቃት አይደርስበትም፡፡ የሟች ቤተሰቦችም ለበቀልና ለጥፋት አይነሳሱም፡፡ ገዳይም እጁን በመስጠቱ ጉዳዩ በሽምግልና ተይዞ እንዲጣራ ያደርጋል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው የጎሳ መሪው ፓልዳ ይሆናል፡፡

ፓልዳው በጎሳው ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮችን የመፍታት፣ የመቆጣጠርና ዳኝነት የመስጠት ስልጣን እንዳለው ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ በዚህም መሰረት ምንም እንኳ ገዳይ ጥፋተኛና ወንጀለኛ ቢሆንም የበለጠ ጥፋት እንዳይከሰት የጎሳ መሪው የጉዳዩ ዋና ተዋናይ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ከብሔረሰቡ አምልኮዊና አስተዳደራዊ መሪዎች እንዲሁም የሀገር ሽማግሌዎችን መርጦ በፍጥነት ወደ ሟች ቤተሰቦች ይልካል፡፡ እነዚህ ሽማግሌዎች ከ3-5 የሚደርሱ ሲሆን ወደሟች ቤተሰብ ዘንድ ሲደርሱ (ኦካ ሱራ ኦርማሬ) የሚል መልዕክት ያስተላልፋሉ ይህ ማለት ልጆቻችን ተጠፋፉ ወንድሙም በእጃችን አለ ማለት ነው (አቶ ካቶ ኩሻ፣ መስከረም 6/2008ዓ/ም)፡፡

መልዕክቱ ሁለት ይዘት እንዳለው አቶ ካቶ ሲገልጹልኝ አንደኛው ሟችም ሆነ ገዳይ የአንድ ቤተሰብ ልጆች ናቸው፡፡ የአንድ ቤተሰብ ልጆች እንዲህ በመሆናቸው ሁላችንም አዝነናል የሚል ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ወንድሙም በእጃችን አለ በማለት የሟች ቤተሰቦችን ወደ ድርድር ለማምጣት መጠቆሚያ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

በዚህ ጊዜ የሟች ቤተሰብ ለብቀላም ይሁን ገዳዩን ለማፈላለግ አይነሱም፡፡ በባህሉ መሰረት ሟች የቀብር ስነ-ሥርዓት ሳይፈፀምለት ወደ ሽምግልናው ሆነ ወደ ድርድር አይገባም፡፡ የሟች ቤተሰብ ሲረጋጋ ቀደም ሲል ፓልዳው የላካቸው ሽማግሌዎች በድጋሚ በመሄድ እንግዲህ የሟች ነፍስም አይመለስ፣ ውሃም አይታፈስ፣ በአውዱማ የተበተነ ፍሬ አይለቀም በልጆቻችን መሀል የገባ ክፉ መንፈስ ውሉ ካደረ ጥሩ አይደለም፡፡ ሀዘንም ቂምም በውስጣችን ይዘን መሰንበት ለቀሪውም ለቤተሰቡም ጥሩ አይደለም፡፡ የሚሉ የመሸንጋያ ሀሳቦች በማውረድ ቤተሰቡ ወደ ድርድር እንዲመጣ ይማጸናሉ፡፡

ይህን ተማጽዕኖ የሚያቀርቡት በአካባቢው የታወቁ የእምነት መሪዎችና ሽማግሌዎች በመሆናቸው ቤተሰቡ ምንም እንኳ ሀዘን ውስጥ ቢሆንም ወደ ድርድር ለመምጣት ፍቃደኛ ይሆናል፡፡ ቀንም ይቆረጣል፡፡ የጎሳ መሪው የላካቸው ሽማግሌዎችም እሺ እንዳላችሁን

እሺ ይበላችሁ፣ የልጃችን ነፍስ ትለምልም የሚል ምርቃት አውርደው ይሰናበታሉ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ካቶ ኩሽ፣ መስከረም 6/2008 ዓ/ም)፡፡

በቀነ ቀጠሮው ቀንም በፓልዳው የችሎት አደባባይ ‹‹ሞራ›› የሚች ቤተሰቦች እንዲሁም የገዳይ ቤተሰቦች ይገኛሉ፡፡ፓልዳው (የጎሳ መሪው) በችሎት አደባባዩ ባለውና ከፍ ብሎ በተሰራው ስፍራ ላይ መሀል ለመሀል ይቀመጣል፡፡ በድርድር ሂደቱ የነበሩና የተመረጡ ሽማግሌዎች በፓልዳ ግራና ቀኝ ይሆናሉ፡፡ የሚችና የገዳይ ቤተሰብ ከዳኞቹ ፊት ለፊት ግራና ቀኝ በመሆን ይቆማሉ (ምልከታ፣ መስከረም 10/2008 ዓ/ም) ፡፡ በዚህ መሰረት ችሎቱ ቦታውን ከያዘ በኃላ ገዳይ በችሎቱ ፊት እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡



**ምስል ሁለት፡-** በሞራ የዳኝነት ስፍራ በዳይና ተበዳይ ፍትህ ሲሰጣቸው፡፡

ሽማግሌዎችም ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ፡-

እንሻላይት አይላ አኪት?

አሬ?

ማናን ኦራ አኪታኔ?

ኮዳሸት አን ቃራ ቄድሎ ምታትሳ ሂትዬ?

የማ ኮዳሼት አንካሳይት ቃራ ሂሰ ጫልም?

እዮኮ ቃይ ሰብ አንኮየ! አንካሶታ አልሃቶ አን ኮያ ሄኔቂዬ?

ቂም ናማብ ካላታ አንፉዶላንያም?

ትርጉም፡-

ወንድምህን የት አገኘው?

እዚህ ቦታ?

ምን አገናኛቹሁ?

ገንዘብ ወስዶ አልመልስ አለ?

ገንዘብ ከወንድምህ በለጠብህ?

አይ ክፉ መንፈስ ውስጤ ገብቶ አሳሳተኝ? ይቅር በሉኝ፣ ማሩኝ

እንደ ባሪያ ልሁን እንደ ሰው አልሆንኩምና?

(የሚሉ ተማፅኖዎችን ያቅርባል)፡፡

ሽማግሌዎችም ያለው ይጣራ፣ በሰፈርና በቤተሰቡ አካባቢ የሚያሳየው ስነ-ምግባር ይመርመር በማለት ለውሳኔ ሌላ ቀጠሮ ይይዛሉ፡፡ ገዳይም ወደ ፓልዳው ቤት ይወሰዳል፡፡ ገዳይ በፓልዳው ቤት በሚቆይበት ጊዜ የጉልበት ስራ መስራት፣ የታዘዘውን መፈፀም ግዴታው ነው፡፡ ምንም እንኳ ጉዳዩ በሽምግልና ቢያዝም የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማው ይደርጋል፡፡ የተባለው ቀጠሮ ቀን ሲደርስ ሽማግሌዎች ሁለቱን ቤተሰቦች ማስማማትና ይቅር ለማባባል ቅድመ ዝግጅት እንዲደረግ ያዛሉ፡፡ በዚህም መሰረት የበዳይ ወገን (ጎሳ) ለእርቅ ሥርዓቱ የሚሆን ‹‹ጨቃ››[14] እና ባህላዊ ምግብ ያሰናዳል፡፡ እርቀ ስርዓቱም ይጀመራል፡፡ ገዳይ ጥፋተኝነቱን አምኖ በመቀበሉና ባህሉን አክብሮ ለፓልዳው እጁን መስጠቱ መፀፀቱን ያሳያል፡፡

[14] ጨቃ ባህላዊ የመጠጥ አይነት ሲሆን በአንድ ማህበራዊ ክንውኖች እንደ፣ ለቅሶ፣ የእርቅ ሂደት በመሳሰሉት ክንውኖች ከምግብነት ያለፈ ፋይዳን ይዞ ይመጣል፡፡ በተለያዩ እርቅ ሂደት ውስጥ የተጋጩ ወገኖች በአንድ መጠጫ በጋራ አፍ ለአፍ ገጥመው በመጠጣት ያለፈ ቂማቸውን ለመርሳትና ይቅር እንደተባባሉ ለማሳየት

የጠፋውን ሳይሆን ያለውን ነፍስ ማስተማር ይገባል አሉ ሽማግሌዎች፡፡ በዚህም መሰረት በዳኝነቱ ለሚች ቤተሰብ የሀዘን ማስረሻ ከሁለት እስከ አራት የሚደረሱ ከብቶች እንዲሁም ቤተሰቡ በሚያደርገው የእርሻ ስራ ሁሉ የጉልበት አገልግሎት የገዳይ ቤተሰብ እንዲሰጥ ይወሰናል፡፡ በውስጥ ያለም ቂም እንዲወጣ ሁለቱ ወገኖች እንደ ቤተሰብ እንዲተያዩ የተዘጋጀውን ጨቃ በአንድ ቅል እንዲጠጡ አደረጉ፡፡



**ምስል ሶስት፡-** በዳይና ተበዳይ በአንድ ቅል ጨቃ በመጠጣት እርቅ ሲፈጽሙ፡፡

የካሳው ዓይነት የሚችን ደምና ነፍስ ይተካል ተብሎ ሳይሆን ለማፅናኛ በሚል የሚሰጥ ነው፡፡ ሁለቱም ወገኖች ፊት ለፊት በመቆም የገዳይ ቤተሰብ በሚች ቤተሰብ እግር ላይ በመውደቅ

ይቅር በሉን አሉ፡፡ በባህሉ መሰረት የሟች ቤተሰብም ከወደቁበት በማንሳት ግንባር ለግንባር ይሳሳማሉ፡፡ ይቅር ተባብለናል ይላሉ፡፡ በአንድ ቅልም የተዘጋጀውን ‹‹ጨቃ›› ይጠጣሉ፡፡ በዚህም እርቀ ሰላም ይወርዳል፡፡

በዚህ መሰረት የዕርቅ ሥርዓቱ ከተፈፀመ በኋላ በሽማግሌዎች ዳኝነት የተሰጠውን የዓይነት ውሳኔ የሟች ቤተሰብ መክፈል ካልቻለ በጎሳ መሪው ውስጥ ያለው ካዳይት ማህበረሰቡን በማስተባበር ውሳኔው ተግባራዊ እንዲሆንና ለሟች ቤተሰብ የተባለው ካሳ እንዲከፈል ያደርጋል፡፡ በዚህ መልኩ የተፈፀመን ታሪክ በማንሳት አቶ ካቶ እንዲህ ሲሉ አጫውተውኛል፡-

> ጊዜው በጣም ቆይቷል የአርጋማይታ ጎሳ አባል ነው፡፡ ጨለማን ተገን አድርጎ የሟችን ነፍስ ያጠፋል፡፡ በወቅቱ በስፍራው ማንም ስላልነበረ ሟችን ማን እንደገደለው አልታወቀም፡፡ የተጋጩት ሰዎች እንዳሉም ታሰሰ ምንም አልተገኘም፡፡ የሟች ቤተሰቦችም ሀዘናቸው በረታ፡፡ይህም በመሆኑ የአምልኮ መሪዎች እርግማን አወረዱ፡፡ ይህንን ሰምቶ መሰለኝ ገዳይ እኔ ነኝ የገደልኩት ብሎ ወደ ጎሳ መሪው ሄዶ ኤርጋዳማ አለ፡፡ የሟችም ቤተሰቦች ካላጠፉነው አሉ፡፡ ጉዳዩ በሽምግልና ተይዞ የማስማማት ስራ መስራት ተጀመረ፡፡ በመጨረሻም ሽማግሌዎች ከብትና የገንዘብ ቅጣት ጣሉበት ይህንን መክፈል አልቻለም፡፡ ለጎሳ መሪው አቤት አለ፡፡ የጎሳ መሪውም ጥፋቱን አምኗል የሽማግሌዎች ውሳኔ መከበር አለበት፡፡ ለጎሳችንም ውርደት ነው እንተጋገዝ የሚል መልዕክት በካዳይታው ላከ ህዝቡም ተባበረ፡፡ ውሳኔውም ተፈፃሚ ሆነ (ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም 6/2008 ዓ/ም)፡፡

የነፍስ ማጥፋት ግጭት በአካባቢው በተደጋጋሚ ከሚከሰቱ የግጭት ዓይነቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ አሁን አሁን ይህን መሰል ወንጀል በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ቢዳኝም በባህላዊ ሥርዓቱ እርቅ መፈፀም የግድና ያልቀረ ባህል እንደሆነ የመረጃ አቀባዮቹ ገልጸውልኛል፡፡ ይህም አጥፊው በመደበኛ ፍርድ ቤት ቅጣት ቢቀበልም ወደ ህብረተሰቡ በቀላሉ አይቀላቀልም፡፡ በመሆኑም በባህላዊ ሥርዓቱ እርቅ ለመፈፀም ይገደዳል፡፡

### 4.2.2 የጠለፋ ግጭት አፈታት

በድራሼ ብሔረሰብ ‹‹ጠለፋ›› እንደ አንድ የጋብቻ ባህል ዓይነት ነው፡፡ ዛሬም ድረስ በአንዳንድ አካባቢዎች እንዳለ ይነገራል፡፡ በድራሼ ብሔረሰብ ጠለፋ ብቻውን ወደ ጋብቻ

አይወሰድም፡፡ ምክንያቱም በብሔረሰቡ ባህል ተመሳሳይ የጎሳ አባላት ጋብቻ አይፈቀድላቸውም፡፡ በመሆኑም ጠላፊው የተጠላፊው የዘር ሐረግ ከስር መሰረቷ ማጥናት ይጠበቅበታል፡፡ በአብዛኛው ጠለፋ የሚከናወነው በገበያ፤ በእንጨት ሰበራና ውሃ ለመቅዳት ወንዝ ሲወርዱ አሳቻ ቦታን በመያዝ የጠላፊው ጓደኞች በህብረት ሆነው ጠለፋውን ያከናውናሉ፡፡

ጠለፋው ከተከናወነ በኋላ ልጅቱ በቀጥታ ወደ ተጠላፊው ቤት አትሄድም፡፡ ምክንያቱም በባህሉ የምትጠለፈው ልጅ ቤተሰቦች በማንኛውም ጊዜና ሰዓት ከተገኘች ወደ ቤቷ የመመለስ ባህል ስላለ ልጅቱን ለመደበቅ ይገደዳሉ፡፡ ጠላፊውም ስውርና እሩቅ በሆነ የአክስቱ ወይም የታላቅ እህቱ ቤት ይደብቃታል (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ መለሰ፣ መስከረም 7/2008 ዓ/ም)፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ በቅድሚያ ድርጊቱን የሚገልፀው ለአባቱ ነው፡፡ ምንም እንኳ ማህበረሰቡ እንደ አንድ ባህል ቢያየውም ከፍተኛ ግጭት ውስጥ የሚያስገባ ሊሆን ስለሚችል አባቱም ቢሆን በቀላሉ ጥሩ ሥራ ሰርተሃል ብሎ አይቀበለውም፡፡ አንድ ወጣት በአንድ ወቅት የአክስቱ ልጅ ተጠልፋ ስትወሰድ መንገድ ላይ ተገጣጥሞ የተፈጠረውን አቶ መለሰ እንዲህ ሲሉ አውግተውኛል፡-

> ዋላይቴ በተባለ አካባቢ ነው፡፡ አንድ ምሽት ወጣት ከእርሻ ሲመለስ አራት ጎረምሶች የአክስቱን ልጅ ጠልፈው ተሸክመው ይዘው ይሮጣሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ከዚህ ወጣት ጋር ፊት ለፊት ይገጣጠማሉ፡፡ ልጁም የተሸከሙትን ሲመለከት የአክስቱ ልጅ ነች፡፡ በያዘው ዱላ ከጎረምሶቹ ጋር ግብግብ ይገባል፡፡ በዚህ ጊዜ ግማሾቹ ልጅቱን ይዘው ሲሮጥ ሌሎቹ ደግሞ ከዚህ ወጣት ጋር ግጥሚያ ውስጥ ገቡ፡፡ በድንገት በአካባቢው ሰው ሲደርስ ሸሽተው ይሄዳሉ፡፡ ልጁም በከፍተኛ ሁኔታ ይጎዳል ፡፡ በአካባቢውም ከፍተኛ እረብሻ ይነሳል፡፡ የሟች ቤተሰብ በስፍራው ነበሩ ወደተባሉት ጎረምሶች ቤት በመሄድ በእሳት ቤት ንብረታቸውን ያያይዛሉ፡፡ ከፍተኛ ግጭትም ውስጥ ይገባሉ፡፡ የኋላ ኋላ የአካባቢው ሽማግሌዎች፣ የጎሳ መሪዎች ሁሉ ሳይቀር በጉዳዩ ውስጥ በመግባት ሁለቱን ቤተሰቦች አስማምተው አሁን ቤተ-ዘመድ ሆነው ይኖራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መስከረም 7/2008 ዓ/ም)፡፡

የጠላፊው አባት ጋብቻው መልካም ቢሆንም ግጭትን ያስከትላልና ቁጣውን ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩ ጥፋት ሳያመጣ በሀገሩ ባህልና ወግ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡ ወደ መንደር መሪው ሻና በመሄድ ጉዳዩን ይመክራል፡፡ ሽማግሌዎችም ይመረጣሉ፡፡ በዚህም መካከል

የልጅቱ ቤተሰቦች እንዳይረብሹ መጠለፏ በወሬ ሆን ተብሎ እንዲደርሳቸው ይደርጋል፡፡ የጠላፊው ማንነት ግን ምስጢር ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ግጭቶች ይፈጠራሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ሽማግሌዎች እስከሚሄዱ ምስጢርነቱ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጠለፋው ከታወቀ የተጠላፊ ቤተሰቦች ልጅቱን ለማስመለስ መሞከራቸው አይቀርም፡፡

ለሽምግልና የተመረጡ የአካባቢው ሽማግሌዎች ወደ ተጠለፈችው ልጅ ቤተሰብ ዘንድ ማልደው ይሄዳሉ፡፡ ወደ ቅጥር ግቢው ሳይገቡ ‹‹ልጇችን አጥፍቷል›› የሚል መልእክት ያሰማሉ የልጅቱ ቤተሰቦች ተቃውማቸውን ለመግለጽ የቤታቸውን በርና መስኮት ይዘጋሉ፡፡ አልፎ አልፎ ስድብና ዛቻም ሊገጥማቸው ይችላል፡፡ ምክንያቱም በድራሼ ብሔረሰብ ሴት ልጅ ለቤተሰቦቿ ከቤት እስከ እርሻ ሥራ ሰፊ አስተዋጽኦ ስላላት ትልቅ ነገር እንደጎደለባቸውና እንደተደፈሩ ጭምር ስለሚታሰብ በቀላሉ ሽማግሌዎችን አይቀበሉም፡፡ ሽማግሌዎችም ለመጀመሪያ ጊዜ የጠላፊው ቤተሰብ ክብር እንደሰጣቸው ለማሳየት ተደርጎ ስለሚታሰብ በር ቢዘጉ አይቀየሙም፡፡ ወደ ጠላፊው ቤተሰብ ዘንድ በመመለስ ቀጠሮ ይዘው ይለያያሉ፡፡ በእነዚህ ቀናት ሁሉ የተጠለፈችው ልጅ በጠላፊው ታላቅ እህት ወይም አክስት ቤት በመሆን ልዩ እንክብካቤ ይደረግላታል፡፡ ልጁንም እንድታገባ ያግባቧታል ከልጁ ጋርም ምንም ዓይነት የግብረ ሥጋ ግንኙነት አታደርግም፡፡ ይህም ከእሷ ፍቃድ ውጪ የሚሆን ምንም ነገር እንደሌለ ለማሳየት እንደሆነ የመረጃ አቀባዮቹ ገልጸዋል፡፡

የሽምግልና ሂደቱም ይቀጥላል፡፡ የልጅቱም ቤተሰቦች እረገብ ማለት ይጀምራሉ፡፡ በተለይም የልጁ ቤተሰቦች ማንነት ሲታወቅና ለልጃቸው የሚመጥን መሆኑን ሲያውቁ ለሽምግልና ድርድሩ እራሳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡

ሽማግሌዎቹም በድጋሚ ወደ ተጠላፊዋ ልጅ ቤተሰብ ዘንድ ይሄዳሉ፡፡ እንደ ቀደመው ሳይሆን ወደ ግቢው ውስጥ በመግባትና በቤቱ በር ላይ በመሆን ‹‹ወጉን አፍርሰናል፣ የልጅ ነገር ሆኖ ነው፣ እንሞላለን፣ እንክሳለን›› ይላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ለሁለተኛ በመምጣታቸው ለሽማግሌዎቹ አክብሮት ይሰጣሉ፡፡ በራቸውንም ይከፈታሉ፡፡ ይህ ማለት ለድርድሩ ተስማምተናል የሚል ይሆናል፡፡ ሽማግሌዎቹም ልጅቱ ያለችበትን ቦታ በይፋ ይገልፃሉ፡፡

ይህ የሚሆነው በባህሉ መሰረት የቤተሰቡ ስምምነት ከመደረጉ በፊት የልጅቱ አክስቶችና እህቶች ወደ ልጅቱ ዘንድ ሄደው ያለችበትን ተመልክተው ፍቃደኝነቷን ጠይቀው መምጣት ስላለባቸው ነው፡፡ በመሆኑም ለሽማግሌዎቹ ሌላ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ መካከል

ያገኟታል፡፡ ፍቃደኝነቷንም ይጠይቃሉ፡፡ በአብዛኛው ለሥርዓት-ባህሉ ይደረጋል እንጂ የተጠለፈችው ሴት በዚህ ድርድር ወደ ቤቷ የመመለስ እድል እንደሌላት የመረጃ አቀባዮቹ ይገልፃሉ፡፡

በሶስተኛው ቀጠሮ የተጠላፊ ቤተሰቦች የልጅቱን ፍቃደኝነት እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለልጃችን ‹‹ኩሲያታ›› ይገባታል ይላሉ፡፡ ኩሲያታ ጥሎሽ ወይም ካሳ እንደማለት ነው፡፡ ይህ ጥሎሽ እንደማንኛውም ሰርግ ላይ እንደሚሰጥ ሳይሆን ልጅቱ ከቤተሰቦቿ ጋር ብትኖር የምትሰጠውን የጉልበትና ሌሎች ጥቅሞችን ከግምት የሚያስገባ ነው፡፡ ይህም ልጅቱ ከቤተሰቧ ጋር ብትሆን የእርሻ ወቅት ከሆነ እርሻ የማረስ፣ የአጫዳ ወቅት ከሆነ የማጨድና ሌሎች ተግባራትን ስለምታከናውን ይህንን ልንካስ ይገባል ይላሉ፡፡ የዓይነት ጥሎሽም ይታከልበታል፡፡ በተለይ በቀደመው ባህል ከ1-5 ከብት ጥሎሽ መስጠት ግዴታ ነው (የቡድን ውይይት፣ መስከረም 5/2008)፡፡

በዚህ መሰረት ሽማግሌዎቹም የልጅቱን ቤተሰቦች ሀሳብ፤ የጠላፊ ቤተሰቦችን አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት የወደፊቱን በማሳየት ሁለቱን አስማምተው የተባለው ተፈፃሚ እንዲሆን በማድረግ በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል ሰላም እንዲወርድ ያደርጋሉ፡፡ ልጅቱም ለሶስት ወራት ተቀልባ ግጭቱ በሠርግ  የመጨረሻ እልባት አግኝቶ ይቋጫል፡፡

### 4.2.3 የጎሳ ግጭት አፈታት

በድራሼ ብሔረሰብ ዘጠኝ ጎሳዎች አሉ፡፡ በእነዚህ ጎሳዎች መካከል ከቀላል እስከ ከባድ ግጭቶች ይፈጠራሉ፡፡ የግጭቶቹ መንስኤዎች ቀደም ሲል የተገለፁት የድንበር፣ የነፍስ ማጥፋት፣ ሰደድ እሳት መልቀቅ የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በሁለት ጎሳዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን መፍታት የሁለቱ ጎሳ መሪዎች (ፓልዳ) ኃላፊነት ነው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ካቶ ኩሾ፣ መስከረም 6/2008 ዓ/ም)፡፡

በተለይ በነፍስ ማጥፋት፣ በንብረት ማውደም የተፈጠረ ግጭት ከሆነ ሌላ ጥፋት ሳይከተል የአጥፊው ግለሰብ ወይም ቡድን የጎሳ መሪ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ የአምልኮ መሪዎችን (ሻና)የመንደር መሪዎችን /ሼላ/ መርጦ ወደ ተጎዳው ቤተሰብ ጎሳ መሪ (ፓልዳ) ቤት ይልካል፡፡ እነዚህ መልዕክተኞች በማህበረሰቡ ውስጥ የአምልኮአዊና አስተዳደራዊ የመሪነት ሚና እንዳላቸው ስለሚታወቅ የተጎጂ ጎሳ መሪ በአክብሮት ይቀበላቸዋል፡፡

በባህሉ መሠረት መልዕክተኞቹ ወደ ተጎጂ ፓልዳ መሪ ዘንድ የሚሄዱት በማለዳ ነው፡፡በፓልዳው መኖሪያ ቤት ሲደርሱ በደጃፍ ሆነው ‹‹ተጠፋፍተናል›› የሚል መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡ ይህም በድራሼ ብሔረሰብ እያንዳንዱ ጎሳ በጋብቻም ይሁን በጥንት ዘር አመጣጡ የደም ትስስር አለው ተብሎ ስለሚታመን የተጎዳው ሆነ ጎጂው ጎሳ አንድ አካል ተደርጎ ይወሰዳል (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ መለሰ፣ መስከረም 7/2008 ዓ/ም)፡፡

የጎሳ መሪውም የመጡ ሽማግሌዎችን በግቢው ውስጥ በተዘጋጀው የእንግዳ ማረፊያ በማስቀመጥ የመጡበትን ጉዳይ በዝርዝር እንዲያስረዱት ያደርጋል፡፡ ሽማግሌዎችም የጎሳ መሪያቸው እንደላካቸው በመግለጽ የመጡበትን ያስረዳሉ፡፡ የተጎጂ ጎሳ መሪም በሁለቱም ጎሳዎች ያሉ ሼላዎች፣ ሻናዎች እንዲሁም በአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ለህብረተሰቡ በእጅጉ ቅርብ የሆኑት ‹‹ሱጋዎች›› የተደራጀ መረጃ እንዲያቀርቡ ቀጠሮ ይሰጣል፡፡

የሁለተኛው ቀጠሮ ቀን ሲደርስ የበዳይ ቤተሰብ ወይም ጎሳ ባህላዊ መጠጦች (ጨቃ) ምግቦች (ኩርኩፋ) እንዲያዘጋጅ ይደረጋል፡፡ ሽማግሌዎችም የተለመደ የሽምግልና ቦታቸውን ከያዙ በኋላ በዳይና ተበዳይ ከችሎቱ ፊት ለፊት እንዲቆሙ ይደረጋል፡፡ ሽማግሌዎችም ‹‹የጠፋው እንዳልጠፋ፣ የሚተው እንዳልሞተ ይቆጠር፣ ክፉ መንፈስ ይራቅ›› የሚሉ የማስማሚያና የማቀራረቢያ ተማጽኖ ካቀረቡ በኋላ ለዚህ ተብሎ የተዘጋጀው ጨቃ በእንስራ ላይ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ ከቀረበው ጨቃ አናት ላይ የሁለቱ ጎሳ ሽማግሌዎች ፉት፣ ፉት በማለት ወደ ግራና ቀኝ ይተፋሉ፡፡ይህ ማለት ቂማችን ይውጣ የሚል እሳቤ እንዳለሁ የመረጃ አቀባዮቹ ይገልፃሉ፡፡ በመቀጠልም በዳይና ተበዳይ በአንድ መጠጫ በጋራ ይጠጣሉ፡፡ በዚህም ሰላም ፍቅርን ያወርዳሉ፡፡

የተፈጠሩ ግጭቶችና ግጭቶቹን የፈጠሩ የጎሳ አባሎቻቸውን በሀገሩ ባህልና ሥርዓት እንደጥፋታቸው የሚሰጣቸውን ቅጣት ይሁን ውሳኔ እንደሚቀበሉ ይገልፃሉ፡፡ የተጎጂ ጎሳ መሪም የሱን ወገን ተጎጂዎችን በማነጋገርና ጉዳዩ በሽምግልና እንዲያዝ ቀነ ቀጠሮ ሰጥቶ ያሰናብታቸዋል፡፡

የጎሳ መሪዎቹ ተጠሪነታቸው ለዳማው በመሆኑና ለጎሳ አባሎቻቸው ኃላፊነት ስላለባቸው በጎሳዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን በጥንቃቄና በትኩረት ይከታተላሉ፡፡ የማህበረሰቡም ሠላም እንዳይናጋ በመካከሉ የሚፈጠሩ ግጭቶችን በሽምግልናና በእርቅ ተስማምቶ እንዲፈታ ያደርጋሉ፡፡ በሽምግልና ለመያዝ ቀጠሮ ሲሰጥ የሽምግልና ስርዓቱ

የሚከናወንበት ቦታ አብሮ ይወሰናል፡፡ በአብዛኛው ከሁለቱ ጎሳዎች መኖሪያ አዋሳኝ በሆነ በሌላ ጎሳ ‹‹ሞራ›› (የችሎት) አደባባይ ይሆናል፡፡

በተመረጠው የሽምግልና ቦታ ላይ በተባለው ቀንና ሰዓት የሁለቱ ጎሳ መሪዎች, ሽማግሌዎች እና የበዳይ እና የተበዳይ ቤተሰብ አባላት እንዲገኙ ይደረጋል፡፡ የሁለቱም ጎሳ መሪዎችም ሆነ ሽማግሌዎች የማህበረሰቡን ሰላም መጠበቅና አንድነቱን ማጥበቅ ስለሆነ የጎጂንም ሆነ የተጎጂ ቤተሰብን በግጭቱ ላይ ያላቸው ሚና በጥንቃቄ ይመረምራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ካቶ ኩሾ መስከረም 6/2008 ዓ/ም)፡፡

በመጀመሪያ የሽምግልና ስርዓት የሁለቱን ቃል መቀበል ይሆንና ሁለቱም የሰጡት ቃል ትክክለኛ ስለመሆኑ ለማጣራት ሁለተኛ ቀጠሮ ይሰጣሉ፡፡ለውሳኔ እንዲሆናቸው በሁለት ጎሳዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች በሁለቱ የጎሳ መሪዎችና ሽማግሌዎች መስማማት ካልተገኘ ጉዳዩ ወደ ዳማው (ንጉስ) ችሎት አራፋይታ እንዲታይ ይደረጋል፡፡ በዚህ ችሎት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻውና የትኛውም የጎሳ መሪ ተቀብሎ ማስፈፀም ግዴታው ይሆናል፡፡

በጎሳዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች እንደ አይነታቸው የዓይነት፣ የጉልበትና የገንዘብ ቅጣቶች የሚጣሉባቸው ጊዜያት እንዳሉ የመረጃ አቀባዮቹ ገልጸውልኛል፡፡ የነፍስ ማጥፋት ከሆነ በጥንቱ ባህል የሞት ቅጣት ሊጣልበት ይችላል፡፡ ንብረት ማውደም ከሆነ ንብረቱን ሙሉ በሙሉ አልያም በከፊል እንዲተካ በሰፊው እየተለመደ መምጣቱን ሽማግሌዎች ይገልጻሉ፡፡

## 4.2.4 ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶች የአፈታት ሥርዓት

የድራሼ ብሔረሰብ ከኮንሶ፣ ከአሌና ከዘይሴ ብሔረሰብ ጋር ካለው የቋንቋና የባህል ግንኙነት የኢኮኖሚና የማህበራዊ ትስስራቸው የላቀ ነው፡፡ በዚህ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ትስስር የሚፈጥሩ አለመግባባቶች ለመፍታት የመንግስት አካላትም ሆኑ ሌሎች ተቋማት የተለያዩ ጥረቶች ያደርጋሉ፡፡ በጥናቱ ሁለተኛ ክፍል ለማሳየት እንደተሞከረው ልዩ ልዩ ተመራማሪዎች በብሔረሰቦቹ መካከል የሚፈጠሩትን ግጭቶች ለማስቀም ምርምር አድርገዋል፡፡ የመፍትሄ ሀሳብ ያሏቸውንም ጠቁመዋል፡፡ ይሁን እንጂ ብሔረሰቦቹ የራሳቸው የሆነ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት አላቸው፡፡ በዚህም ችግሩን ይፈታል፣ ልዩነቱን ያጠባል፡፡

የአሌ ብሔረሰብ በድራሼ ደጋማው አካባቢ የሚኖር ህዝብ ሲሆን በአሁን ሰዓት ህዝቡ ራሱን ችሎ እንደ አንድ ወረዳ መተዳደር ከጀመረ ዓመታት ተቆጠሩ፡፡ እነዚህ ሁለት ህዝቦች በአብሮነት ህይወታቸው የሚጋሯቸውና የሚያስተሳስራቸው በርካታ ጉዳዮች አሏቸው፡፡ ለግጭቶቻቸው መነሻ የሚሆኑ በአብዛኛው በእርሻ መሬት፣ በከብት ግጦሽ ቦታ፣ በድንበር ይገባኛል የመሳሰሉ ምክንያቶች ናቸው፡፡ የፍትህ አስከባሪ አካላትም ግጭቶችን ለማብረድና ለመፍታት ተደጋጋሚ ጥረቶችን አድርገዋል፡፡ ግጭቶቹ አንዱ ሌላውን ቂም እየመዘዘና እያገረሸ ዛሬ ተፈቷል ሲባል ወራትን አልፎ እንደ አዲስ ይከሰታሉ፡፡

ይህ በመሆኑ የብሔረሰቦቹ የጎሳ መሪዎች ጉዳዩ ስላሳሰባቸው በጋራ በመምከር የሁለቱ ብሔረሰቦች ተደጋጋሚ ግጭቶች የሚፈጠሩት ባህላዊ የእርቅ ስርዓት ስላልተፈጸመና የአያት ቅድም አያቶቻችን ስርዓት ስላላከበሩ እንደሆነ ተማመኑ፡፡ በዚህ መሰረት የሁለቱ የጎሳ መሪዎች ተግባብተው ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የእርቅ ስርዓት ለማከናወን ሐምሌ 17/2007ዓ/ም ቀጠሮ በመያዝ ተለያዩ፡፡

ቦታው ደግሞ የሁለቱ አቅራቢያ የሆነው ጋቶ ቀበሌ ገበሬ ማህበር እንዲሆን ተወሰነ፡፡ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት ይህንን የእርቅ ስርዓት በተፈጥራዊ መቼቱ ያየሁትንና ከእርቁ በፊት የተከናወኑ ስርዓቶችን በዝርዝር እንመልከት፡-

**ቅድመ እርቅ**

የብሔረሰቦቹ የጎሳ መሪዎች የአያት ቅድመ አያቶቻችን ስርዓት አልፈፀምንም ካሉ በኋላ በባህላዊ የእርቅ መፍቻ ስርዓቱ ያለፉ ግጭቶችን ለመርሳትና ይቅር ለመባባል ወሰኑ፡፡ በመጀመሪያ የየጎሳ መሪዎቹ ተደጋጋሚ ግንኙነት በማድረግ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተመካከሩ፡፡ በሁለቱም ወገኖች የጠፋ ነፍስ እና ንብረት አለ፡፡ በዚህም አንዱ ሌላውን ሳይጠይቅ ቂም ላለመያያዝና ይህንንም ከውስጥ ለማስቀረት የተለመደውንና ባህሉ የሚፈቅደውን የእርድ ስርዓት ለማከናወን ሶስት የእርድ ከብቶች እንዲገዙ ተስማሙ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ዘላለም አምሳሉ ሐምሌ 19/2007 ዓ/ም)፡፡

በብሔረሰቦቹ ባህል ለእንደዚህ ዓይነት የባህል እርቅ ሥርዓት የሚታረዱ ከብቶችና በጎች የተለዩ ናቸው የሚል እምነት አለ፡፡ በተለይ በጎቹ ኮንሶ አካባቢ ብቻ የሚገኙ ወደ ጭራቸው አከባቢ ድፍን መሆን አለባቸው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህም የሚሆነው የብሔረሰቦቹን የወደፊት ዕድል አንጀት በማንበብ የሚተነበይ በመሆኑ ይህንን ግልጽ

አድርገው የሚያሳዩት እነዚህ የበጎች አይነት ናቸው ተብሎ ስለሚታመን መሆኑን የሀገር ሽማግሌዎች ገልፀውልኛል፡፡



**ምስል አራት፡- ለእርቅ ስርዓቱ ማስፈፀሚያ ተመርጠው የተዘጋጁ ከብቶች**

በዚህም መሰረት ከእርቅ ስርዓቱ ሶስት ቀን በፊት ከሁለቱ ብሔረሰቦች የተወከሉና የእምነት መሪዎች ወደ ኮንሶ በመሄድ የተባሉትን ሁለት በጎችና አንድ ጥርሷን ያልሸረፈች ጊደር እንዲገዙ ተደረገ፡፡ይቺ ጥርሷን ያልሸረፈችና ወንድ ያልደረሰባት ጊደር የምትመረጠው በሁለቱ ህዝቦች መካከል የሚደረገው እርቅ ሙሉና ቂም የማይቋጠርበት ይቅር መባባሉም ያልተሸራረፈ መሆኑን ለማመልከት እንደሆነ የሀገር ሽማግሌዎቹ ገልፀውልኛል፡፡

ለእርድ የሚሆኑ ከብቶች በዚህ መልኩ ከተሟሉ በኋላ በእርቅ ስፍራው የሚገኙ የየብሔረሰቡ የጎሳ መሪዎች፣ ባህላዊ የአምልኮ መሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች የሚመለከታቸው የመንግስት አካላትና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ተለይተው በተጠቀሰው ቀን ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት እንዲገኙ ተደረገ፡፡ ሁሉም የብሔረሰቡ አባላት ከተጠቀሰው ሰዓት አስቀድመው በመገኘት የአያት ቅድመ አያቶቻቸውን ሥርዓት ለመፈፀምና ሰላም ለማውረድ ተሰናዱ፡፡ ከዚህም በኋላ የእርቅ ስርዓት ጀመረ፡፡

### የእርቅ ስርዓቱ አፈፃፀም

በሥፍራው የተገኙ ከሁለቱ ብሔረሰቦች የተውጣጡ የጎሳ መሪዎች፣ የእምነት መሪዎችና የሀገር ሽማግሌዎች በየወገን በየወገናቸው ፊት ለፊት በኮረብታማው ቦታ ቆሙ፡፡ አቋቋማቸው በሁለቱም ወገን የጎሳ መሪዎች ከፊት፣ የሀገር ሽማግሌዎች ከኋላ እና የአመልኮአዊ መሪዎች በሁለቱ ጎን ለጎን በአጀብ ነበር፡፡ ከድራሼ ብሔረሰብ አንድ የሀገር ሽማግሌ ከሰልፉ ወጣ በማለት፡-

ቃያ ሀሰጋዶ

ካራዳይኖ ሂቁሃት ኮዶ

አኩም ኦልን ካላኖ ሂጎዶ

ሃንዶት ሂኮዶ

ሁሳይኖ ህካኖ

ኢንጎት ሃይት ሂኤብፋምቶ

ሴ ታዋድ ሂምታቶ

ትርጉም፡-

ክፉ መንፈስ ይራቅ፣

ሆዳችን ይርጠብ፣

አብሮ ያኑረን፣

ሠላም ይስፈንልን፤

አካባቢው ይለምልም፣

የወላድ ማህፀን ይርጠብ፣

የጠፋ ይተካ

በየመካከሉ (ሂጎዱ!) ይሁን! (ሂጎዱ!) ይሁን! የሚሉ ድምፆች በጋራ ይሰማሉ፡፡ በእዛኛውም ወገን በተመሳሳይ ተደገመ፡፡ ይህን ተከትሎ የእምነት መሪዎቹ በወጣቶቹ ተጎትተው የመጡ በጎችን በቁማቸው ሆድቃቸውን በቢላዋ ተረተሯቸው፡፡ በጎቹም ከፍተኛ ድምፅ ካሰሙ በኋላ ወደ መሬት ተዘረሩ፡፡ በመቀጠል አንገታቸውን በመቁረጥ ቆዳቸው ሳይገፈፍ አንጀታቸውን አወጡ (ምልከታ፣ ሐምሌ 17/2007 ዓ/ም)፡፡

የበጎቹ በቁም በቢላ ሆድቃቸው መተርተር የብሔረሰቦቹን የቀጣይ እጣ ፈንታ ለማንበብ አንጀቱ መድረቅ ስለማይኖርበት የበጉ ነፍስ ሳትወጣ መሆን አለበት የሚል እምነት እንዳለ የሀገር ሽማግሌዎቹ በወቅቱ አስረድተውኛል፡፡



**ምስል አምስት፡- ለአንጀት ንባብ የታረዱ በጎች**

የበጎቹ አንገት ሲታረድ አንድም ደም ወደ መሬት እንዳይፈስ በጥንቃቄ እንዲቀዳ ተደረገ፡፡ ይህም የሆነው ለባህላዊ ሥርዓቱ ማስፈፀሚያ ስለሚያገለግል እንደሆነ በምልከታዬ ማስተዋል ችያለሁ፡፡



**ምስል ስድስት፡-** ለባህላዊ ስርዓቱ ማስፈጸሚያ ለእርድ ከቀረቡ በጎች ደም ሲቀዳ

በቁማቸው የተዘረገፈው የበጎቹ አንጀት ሜዳው ላይ ተዘርግቶ በአምልኮ መሪዎቹ እየተገላበጠ በጥንቃቄ ተነበበ፡፡ የአንጀት ንባቡ የሚያሳየው ክፉም ሆነ ደግ ከጥቂት ሰዎች ውጪ ማንኛውም ሰው እንዲያውቀው አይፈለግም፡፡ በኋላ መረጃ አቀባዮቹ እንደገለፁልኝ ክፉ እድልን የሚያመላክት ከሆነ ሌላ ባህላዊ ሥርዓት አምልኮ ይከናወናል፡፡በወቅቱ ግን ከዚህ ውጪ የተከናወነ ሌላ ስርዓተ አምልኮ አልነበረም፡፡ ከዚህ መገመት የሚቻለው የብሔረሰቦቹ የቀጣይ ዘመን ተስፋና ሰላም መልካም መሆኑን የሚያመላክት እንደሆነ ነው



**ምስል ሰባት፡-** *የአምልኮ መሪዎች የአንጀት ንባብ ሲያደርጉ*

የአንጀት ንባቡ ካበቃ በኋላ እነዚሁ የአምልኮ መሪዎች በጠፍጣፋ ጥቁር ድንጋይ ላይ ‹‹የቀበሪኛ›› ቅርፊት በመፍጨት ቀደም ሲል ከበጎች የተቀዳውን ደምና ለዚሁ ስርዓት ተብሎ ከተዘጋጀው የ‹‹ጨቃ›› መጠጥ ጋር አንድ ላይ እንዲደባለቅ አደረጉ፡፡



**ምስል ስምንት፡-** የአምልኮ መሪዎች ቀበሪቾ ሲፈጩና ከጨቃና ከደም ጋር ሲቀላቅሉ

ይህም ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላ ሁሉም ቦታ ቦታውን በመያዝ የደም፣ የጨቃና የቀበሪቾ ድብልቅ የሆነውን መጠጥ በመቀባበል ሁሉም ተቃመሱት፡፡



**ምስል ዘጠኝ፡-** የደም፣ የጨቃና ቀበሪቾ ቅልቅልን እየተቀባበሉ ሲጠጡ፡፡

የእነዚህ የሶስቱ የደም፣ የጨቃና የቀበሪቾ አንድ ላይ መደባለቅ የሚያመላክተው ቀበርቾ በባህሪው  የመምረር ሁኔታ ያለው ሲሆን በሆድ ውስጥ ያለን ቂም ጠርጎ ያወጣል የሚል እምነት እንዳለና የደምና የጨቃው መቀላቀል ደግሞ ሁለቱ ህዝቦች በደምና በስጋ የተሳሰርን አንድ ቤተሰብ ነን የሚል ትርጓሜ እንዳለው የህግር ሽማግሌዎች ገልፀውልኛል፡፡

በዚህ መሰረት ሁለቱ ብሔረሰቦች ባህላዊ ሥርዓት በመፈፀም በውስጣቸው የነበረውን አለመግባባት አስታርቀው፣ ልዩነታቸውን አጥብበው አንድነታቸውን አጥብቀው እርቅ ሠላም አወረዱ፡፡

# 5. በባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቱ ላይ የተደረገ ትንተና

የድራሼ ብሔረሰብ ግጭት የሚፈታበትን ባህላዊ መዋቅር፣ የግጭት አፈታት ሥርዓቱንና የግጭት ዓይነቶችን ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም ይህ የባህላዊ ግጭት መፍቻ ሥርዓት ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ምን እንደሆነ፣ የባህላዊ ሥርዓቱ ዋነኛ እሴቶች ወይም ባህሉ በምን ላይ እንደተመሰረተ፣ የባህላዊ ግጭት መፍቻና የመደበኛ ፍትህ ስርዓት ተዛምዶ፣ ማህበረሰቡ ለሁለቱ ተቋማት ያለው ምልከታ፣ የባህላዊ ስርዓቱ ጥንካሬና ክፍተቶች እንዲሁም የማህበረሰቡ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል በዚህ ምዕራፍ ይተነትናሉ፡፡

## 5.1 የባህላዊ ሥርዓቱ ፋይዳ

አራርሳ (ሆሮታን) የድራሼ ማህበረሰብ ግጭት የሚፈታበት ሥርዓት ለዘመናት ሲጠቀምበት ኖሯል፡፡ በዚህም ማህበረሰቡ አንድነቱን፣ ሰላሙንና ማንነቱን አስጠብቆ ቆይቷል፡፡ ባህልና ወጉ እንዳይጣስ ትውልዱን እያስተማረ፣ እየዳኘና እያስታረቀ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ የማህበረሰቡን ማህበራዊ ግንኙነት በማጠናከር፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስሩን በማጎልበትና ስነ-ልቦናዊ መንፈሱን በማሳደግ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ ዘርዝር አድርገን እንመልከት፡፡

### ማህበራዊ ፋይዳው

የግጭት መፈጠር በየትኛውም ቦታና ጊዜ በአብዛኛው የሚደገፍ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ይህን የተፈጠረ ግጭት ለማብረድ በሚደረገው ጥረት ውስጥ በሚታለፉ ሂደቶች የማህበረሰቡን የእርስ በእርስ ግንኙነትና አንድነት የማጥበቅ አጋጣሚዎች ሲፈጠሩ እናስተውላለን፡፡ይህ ጥናት ትኩረት ባደረገው የድራሼ ብሔረሰብ ውስጥ በግጭት መፍታት ሂደት ውስጥ ከቤተሰብ መሪ እስከ ላይኛው የብሔረሰብ መሪ ዳማ ድረስ ተሳትፎ እንዳላቸው ተመልክተናል፡፡ በነዚህ የፍትህ መዋቅር የሚያልፍ ግጭት ውሳኔ ሲሰጥበት እያንዳንዱ የጎሳ መሪም ሆነ የመንደሩ አለቃ በውሳኔ አፈጻጸም ሆነ በፍርድ ሂደት በጥብቅ ትስስር ይሰራሉ፡፡ ይህ ማህበራዊ ግንኙነቱን የበለጠ እንዲጠብቅ ያደርገዋል፡፡

በሌላ መልኩ አንድ የጎሳ አባል ግጭት ውስጥ ቢገባ እንደ ጠበቃ ሆኖ የሚከራከርለት የጎሳው መሪ ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የጎሳ አባሉ የሚወስንበትን ውሳኔ መፈፀም የማይችል ከሆነ በካዳይት አማካኝነት ከጎሳው አባል በሙሉ እንዲዋጣ በማድረግ የመክፈልና ከችግሩ

እንዲላቀቅ በማድረግ ባህላዊ ሥርዓቱ ማህበረሰቡ እንዲረዳዳ፣ እንዲተሳሰብ በማድረግ ማህበራዊ ትስስሩ እንዲጠነክር ያደርጋል፡፡

### ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ

በጥናቱ ቀዳሚ ክፍል እንደተገለጸው የድራሼ ብሔረሰብ የሚተዳደረው በእርሻ ነው፡፡ ይህ የእርሻ ሥራ የሚከናወነው ወቅቱን ተከትሎ በሚመጣ ዝናብ ነው ፡፡ በመሆኑም ይህንን ጊዜ በመከተል ማረስ፣ ማጨድና ለቀጣይ መዘጋጀት የብሔረሰቡ የዘወትር ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታና ፍትህ ለማግኘት የባህላዊ ግጭት መፍቻ ሥርዓቱ በዚያው ማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ ረጅም ጉዞ ሳያደርግ፣ ገንዘቡንና ጉልበቱን ሳያባክን ፍትህ እንዲያገኝ በማድረግ ማህበረሰቡ እንዳይጉላሉ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ የሚወሰኑ ውሳኔዎች በተለይ የከብት፣ የገንዘብ ቅጣቶች አንድ ሰው ላይ ብቻውን እንዲወጣ ባህሉ አለመፍቀዱ የግለሰቦች ህይወት በኢኮኖሚያዊ ምክንያት ለማህበራዊ ደህንነታችው ስጋት እንዳይፈጠር የጎላ አስተዋጾኦ አለው፡፡ ይህም ግለሰቡ በቀላሉ ወደ ነበረው ህይወት እንዲቀላቀል ይደረጋል፡፡

### ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ

የድራሼ ማህበረሰብ ለባህላዊ ሥርዓቱ ከፍተኛ ክብር አለው፡፡ በፍትህ ስርዓቱ የሚሰጡ የዳኝነት ውሳኔዎች እንደ እርግማን ፣ የማግለል የመሳሰሉት የቅጣት ዓይነቶች የቤተሰቡን አልፎም የዘር ማንዘሩን ህይወት ያናጋሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የትኛውም የብሔረሰቡ አባል በግጭት ሥርዓት አፈታት ውስጥ ጥፋቱን ሳያምን ቢቀር በአምልኮአዊ መሪዎች የሚደረግበት እርግማን ይደርስብኛል ብሎ ስለሚያስብ ጥፋቱን ከመካድ ይልቅ ማመንን ምርጫው ያደርጋል፡፡ በዚህ ምክንያት በብሔረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶች በአብዛኛው የተደበቁና አውጫጭኝ የሚፈልጉ አይደሉም፡፡ ይህ ደግሞ በባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ የውሳኔ ዓይነቶች በጎ ስነ-ልቦናዊ ተጽዕኖ የመጣ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ በጎ ተጽዕኖ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶች ሳይደበቁ ይቅር በመባባል የአብሮነት ህይወቱ እንዲቀጥል አስችሎታል፡፡

ፖለቲካዊ ፋይዳው

ግጭት በብሔረሰቡ ጎሳዎች ሆነ ከብሔረሰቡ ውጪ ካሉ ማህበረሰቦች ጋር ይፈጠራል፡፡ የእነዚህ ግጭቶች ምክንያት በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው የሀብት፣ የስልጣንና ፍላጎት አለመጣጣም ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ፍላጎቶች ደግሞ አይለው የማህበረሰቡን ህልውና አደጋ ውስጥ ሊከቱ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ይህ እንዳይሆን የባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱ የመጨረሻ ወሳኝ አካል የዳማውን ችሎት ‹‹አርፋይታ›› አስቀምጧል፡፡ ይህ የዳማው ችሎት በየደረጃው የስልጣን ባለቤቶችን በማስቀመጥ የማህበረሰቡ ማህበራዊ ህይወት እንዳይናጋ፣ ሰላሙ እንዲጠበቅ፣ መደማመጥ እንዲሰፍን፣ መከባበር እንዲነግስ አድርጓል፡፡ በዚህም የስልጣን ተዋረድ እንዲመራ በማድረግ ከሌሎች የአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር የኢኮኖሚያዊ ሆነ የማህበራዊ ግንኙነቱ ጤናማ ሆኖ እንዲቀጥል አስችሎታል፡፡ በመሆኑም ሥርዓቱ ‹‹ከኦስማረ›› እስከ ‹‹ዳማ›› በመዋቀሩ የማህበረሰቡን ግንኙነት አጥብቆ አቆይቷል ማለት ይቻላል፡፡

## 5.2 የባህላዊ ሥርዓቱ እሴቶች

ይህ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓት የቆመባቸው በርካታ እሴቶች አሉ፡፡ እነዚህ የስርዓቱ እሴቶች ባይኖሩ ህልውና ይኖረዋል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ማህበረሰቡም ለእነዚህ እሴቶች ተገዥና ህልውናውን ጠብቆ እንዲቀጥል ልዩ ልዩ ብልሀቶችን አስቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ የሥርዓቱ እሴቶች ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ እየሳሱ እንደመጡ ማስተዋል ተችሏል፡፡ በዋነኝነት የባህል ሥርዓቱ መሠረቶች የሚባሉትን ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን፡፡

**የፍትህ ስርዓቱ መዋቅር መኖር፡-**ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቱ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን የሚመለከትና መፍትሄ የሚስጥ መዋቅር መኖሩ የባህላዊ ሥርዓቱ መሠረት ነው፡፡ መዋቅሩ የሚመለከታቸውንና የማይመለከታቸውን ጉዳዮች እያንዳንዱ ለይቶ ማስቀመጡ ማህበረሰቡ የትኛው ግጭት በማን እንደሚፈታና ውሳኔ እንዲያገኝ እንዲያውቅ አስችሎታል፡፡ ከዚህም ባለፈ በዘር ሐረግ የሚተላለፍ የፍትህ ሥርዓቱ ወሳኞች እንደ ‹‹ዳማ›› ‹‹ሼላ›› የመሳሰሉት እንዳሉ ሆነው በተለይም ትልቁ የስልጣን ባለቤት የንጉስ ችሎት ‹‹ አራፋይታ›› ውሳኔ አዛብቶ ከተገኙ ‹‹በጥንስስ ጠሩ›› አማካኝነት ህዝቡ ከስልጣን

አውርዶት በሌላ መተካት መቻሉ የ‹‹አራፋይታው›› ችሎት በሌላ ገጽታው ለህዝቡ የሚሰራ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ይህ የባህል ሥርዓቱ ውስጥ ቁልፍ እሴት ነው ማለት ይቻላል ፡፡

***መተማመን*** ፡- በባህል ህጉ ከሚሰጡ ውሳኔዎች አንዱ እርግማን ነው፡፡ ይህ እርግማን ደግሞ በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ በአጥፊው ላይ ብቻ ሳይሆን በዘር ማንዘሩ ላይ ሁሉ የሚከሰት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የትኛውም የማህበረሰቡ አባል በባህል ሥርዓቱ ሲዳኝ ከመካድ ይልቅ መተማመን ይመርጣል፡፡ ይህ ደግሞ የባህል ህጉን ጠንካራ ከማድረጉ ባለፈ በማህበረሰቡ ውስጥ እምነትና ታማኝነት መፍጠር ይቻላል፡፡

***ይቅር መባባል*** ፡- በድራሼ ብሔረሰብ ነፍስ ማጥፋት፣ ንብረት በእሳት ማውደም፣ የሰው ንብረትን መውሰድ፣ መዋሸት በ‹‹ዳውራ›› ባህላዊ አስተምህሮት ሥርዓት እጅግ የተወገዙና የተጠሉ ነውር ተግባራት ናቸው፡፡ በዚህ የአስተምህሮት ባህል እየተቀረጸ የመጣ የማህበረሰቡ አባል እነዚህን ተግባራት ፈጽሞ ሲገኝ ከፍተኛ ጸጸት ውስጥ ከመግባቱም በላይ ቅጣቱም ከፍ ያለ እንደሆነ ያውቃል፡፡ እነዚህ የጥፋት ዓይነቶች ከባድ ቢሆኑም የማህበረሰቡ ህልውናን የሚያናጉ ከሆኑ በአብዛኛው የሚሰጡ ውሳኔዎች በዳይም ሆነ ተበዳይ ይቅር በመባባል ወደ ሠላማዊ ህይወታቸው እንዲመለሱ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የባህላዊ ሥርዓቱ መሠረት ማህበረሰቡን እያስማማ፣ እያስታረቀ ህልውናውን ማስቀጠል በመሆኑ ይቅር መባባል የባህል ስርዓቱ መሰረት ነው፡፡

***ማስተማር፡-*** የዚህ ባህላዊ ሥርዓት አንዱ እሴት ማስተማር ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ተደጋጋሚ ጥፋቶችን የሚፈጽሙ፣ ለባህላዊ ህጉ ተገዢ ያልሆነ የማህበረሰቡን ሰላም የሚያደፈርስ በየደረጃው ባለ የፍትህ ሥርዓት ተዳኝቶ አስተማሪ ውሳኔዎች ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ ውሳኔዎች እስከ ሞት ቅጣት በንጉስ ችሎት ‹‹በአራፋይታ›› እንዲወሰን ይደረጋል፡፡ ይህ ውሳኔ አጥፊዎችን የሚያርም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮችን የሚመለከትና የሚወስን አካል እንዳለ ያሳያል፡፡ሽማግሌዎችም በሚደረጉ የእርቅ ሥርዓቶች አጥፊዎችን የመምከርና የማስተማር ዳግም የጥፋት ተግባር እንዳይፈጸም የማድረግ ሀላፊነትን ሲወጡ እንመለከታለን፡፡ በመሆኑም የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ጥፋተኛን ማረም፣ ማስተካከል ዓይነተኛ መገለጫ ነው፡፡

***የባህል ሥርዓት ህጉን ማክበር***፡- በእያንዳንዱ በፍትህ ሥርዓት መዋቅር ውስጥ የተለያዩ ህጎች፣ ባህላዊ ደንቦችና ሥርዓቶች አሉ፡፡ እነዚህ ባህላዊ ሥርዓቶችና ደንቦች በብሔረሰቡ

አባላት እንዲጠበቁ ይደርጋል፡፡ አንድ ነፍስ ያጠፋ ግለሰብ በፍጥነት ወደ ጎሳ መሪው ‹‹ፓልዳ›› ቤት ገብቶ እጅ ከሰጠ የሟች ወገኖች በፍጹም ለጥፋትና ለበቀል አለመነሳታቸው የባህል ህጉን ከማክበር የሚመነጭ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ ከዚህ ባለፈ በዳማ ችሎት የሚወሰኑ ውሳኔዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ የችሎቱ አደባባዮች ‹‹ሞራ››ን የመሳሰሉት ቦታዎች ልዩ ክብር ይሰጣቸዋል፡፡ እንደ‹‹ ሼላ›› የመሳሰሉ የባህላዊ ሥርዓቱ አምልኮአዊ መሪዎች ቃላቸው ይከበራል፡፡ በመሆኑም የባህላዊ ሥርዓቱን ማክበር ሌላው ዋነኛ እሴት ነው፡፡

***መቻቻል፡-*** የባህላዊ ሥርዓቱ ሌላው ገጽታ ማህበረሰቡ ተረዳድቶ ተቻችሎ እንዲኖር ማድረግ ማስቻሉ ነው፡፡ በብሔረሰቡ አንዱ የጎሳ አባል ላይ በባህላዊ ችሎት የተወሰነ ውሳኔ መክፈል ካልቻለ በመንደር መሪው ካዳይታ አማካኝነት ተሰብስቦ ቅጣቱን መክፈል የተለመደ ነው፡፡ ይህም የመረዳዳት፣ የመተጋገዝና የመቻቻል ባህል መኖሩን ያሳያል፡፡ በተለይም በይቅር ባይነት እያንዳንዱ የመንደሩ አባል የአብሮነት ህይወቱን ለማስቀጠል በእርቅና በሽምግልና የሚሰጡትን ውሣኔዎች ተቀብሎ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ይህም የባህል ስርዓቱ የፈጠረውና የመኖሩ መሰረት ነው፡፡

## 5.3 የባህላዊ ግጭት መፍቻና የመደበኛ ፍትህ ሥርዓት ተዛምዶ

በባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ የማይዳኙ፣ ውሳኔ የማይሰጥባቸው የግጭት (የወንጀል) ዓይነቶች የሉም፡፡ በባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ ካልተዳኘ አብዛኛው የማህበረሰቡ ክፍል የተረጋጋና ሰላማዊ ህይወትን ለመምራት እንደሚቸገር የሀገር ሽማግሌዎች ይናገራሉ፡፡ ይሁን እንጂ በሀገር ሽማግሌዎች የተያዙ ጉዳዮች ወደ መደበኛው የፍትህ ሥርዓት በመሄድ ውሳኔ ተሰጥቶባቸው ከዓመታት በኃላ ተመልሰው ወደ ባህላዊ እርቅ እንደሚመጡ ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ረገድ የባህል ህጉ በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ያለው ትስስር ምን እንደሚመስል አቶ ደረሰ ማሌ የወረዳው ፍርድ ቤት ዳኛ እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡

በተለይ ማስረጃ የማይገኝላቸው ወንጀሎች የህብረተሰቡን ሠላምና ደህንነት አደጋ ውስጥ ስለሚከቱ በባህላዊ የእርቅ ሥርዓቱ እንዲዳኝ ይደረጋል፡፡ ይህም የሚሆነው በህገ- መንግስቱ አንቀጽ 8 ንዑስ ቁጥር 5 መሰረት የግልና የቤተሰብ ጉዳዮች በሐይማኖት ወይም በባህል የዳኝነት ሥርዓት መዳኘትን የሚፈቅድ በመሆኑ በባህላዊ የእርቅ ስርዓት ስምምነት አግኝተው የሚቋጩ ጉዳዮች በርካታ ናቸው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ደረሰ ማሌ፣ መስከረም 9/2008 ዓ/ም)፡

አብዛኛዎቹ ጉዳዮች የቤተሰብ ህጉን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ በባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ እርቀ ሰላም ወርዶ እንኳ ቢሆን አንዳንድ ጉዳዮች በመደበኛ ፍትህ ሥርዓቱ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውና የሚዳኙ የወንጀል ዓይነቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም ወስጥ የነፍስ ግድያ፣ የጠለፋ የመሳሰሉት በባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ፣ ቢዳኙም በመደበኛው ፍትህ ስርአቱ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ ይሁን እንጂ ቀላል የማይባሉ ግጭቶች በባህላዊ ዳኝነት የሚያልቁ ናቸው ሲሉ አቶ ደረሰ ያስረዳሉ፡፡ ይህም የሚያመላክተው የባህላዊ ፍትህ ስርአቱ የመደበኛ ፍትህ ስርአቱን በማገዝ እየሰራ መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱን ለማጎልበት የሚደረግ ጥረት ውስን መሆኑን ያነሳሉ፡፡

በሌላ መልኩ በመደበኛ የፍትህ ሥርዓት የግለሰቦች ወይም የቡድኖች ግጭት እልባት ሊያገኝ ይችላል፡፡ ነገር ግን እንደ ማህበረሰብ የጋራ ሰላምን ለማውረድ ባህላዊ የእርቅና የሽምግልና ሥርዓት ግጭቶችን በማቅለል በኩል ከፍተኛ ሚናን በመጫወት የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን ሥራ የቀነሰ ተግባር እንደሚያከናውንና ለዚህም የድራሼና የአሌ ብሔረሰብ ችግሮቻቸውን በባህላዊ የእርቅ ሥርዓት በመፍታት በኩል የሄዱበት መንገድ የፍትህ ስርዓቱን በማገዝ፣ የአካባቢውን ሰላም በመፍጠር ያደረጉት አስተዋጽኦ ላቅ ያለ መሆኑን ያሳያል (ቃለ መጠይቅ፣ ዘላለም አምሳሉ፣ ሐምሌ 19/2008 ዓ/ም) ፡፡

## 5.4 የተቋማቱ ውሳኔ ተቀባይነት

የመደበኛውም ይሁን ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ በሚፈጠሩ ግጭቶችና አለመግባባቶች የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች አሉ፡፡ በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ከማስተማር ይልቅ ቅጣት ላይ የሚያተኩር ሲሆን በባህላዊ ዳኝነቱ በአብዛኛው ማስታረቅ፣ ማስማማትና ማቀራረብ ላይ ትኩረቱን ያደርጋል፡፡ ከእነዚህ በሁለቱ የውሳኔና የዳኝነት አሰጣጥ ላይ ተቋማቱ ልዩነት ውስጥ በመግባት አንዱ የአንዱን ውሳኔ በግልጽ ይሽራል፡፡ ለዚህ ምሳሌ አብነት የሚሆን ክስተትን በቡድን ውይይት ወቅት የሀገር ሽማግሌዎች እንዲህ ሲሱ ገልፀውልኛል፡-

> ጋቶ አካባቢ ከገበያ ሲመለሱ ሁለት የአንድ መንደርና የኮላይታ ጎሳ አባል የሆኑ ወጣቶች ይጋጫሉ፡፡ በዚህ መካከል የአንደኛው ወንድም በስፍራው ይደርስና ለወንድሙ ተደርቦ ፀብ ውስጥ ይገባል፡፡ የባላጋራውንም እግር በዱላ ይመታና ይጎዳዋል፡፡ሰዎችም ይገላግሏቸውና ጉዳዩ ወደ ሽምግልና

ይመጣል፡፡ በሽምግልናውም የገንዘብና አንድ በግ ቅጣት ይጣልበታል፡፡ በዳይም ይቅርታ ጠይቆ የተባለውን ይከፍላል፡፡ ይሁን እንጂ በወቅቱ ጉዳዩ በፖሊስ ተይዞ ነበርና አንድ ዓመት ከስምንት ወር ተፈርዶበት ፍርዱን ተቀብሎ ጨርሶ ወጥቷል፡፡ (የቡድን ውይይት፣ መስከረም 5/2008 ዓ/ም)

እንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎች አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ሲሆን የባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱም በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት የተወሰኑ ውሳኔዎች በባህላዊ ስርአቱ በድጋሚ እንዲታይ ያደርጋል፡፡ በተለይም የነፍስ ማጥፋትና የንብረት ማውደም የመሳሰሉ ግጭቶች ከሆኑ ውሳኔ ተሰቶባቸውም ቢሆን በባህላዊ ስርአት በጎሳ መሪው ፍፃሜ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ይህ በአብዛኛው በበዳይና ተበዳይ መካከል ሰላማዊ ግንኙነትና የበቀል መንፈስ እንዳይኖር በማሰብ የሚደረግ ነው፡፡

በሌላ መልኩ በመደበኛው የፍትህ ስርአት የሚወሰኑ ውሳኔዎች የገንዘብም ይሁን የዐይነት ግለሰቡ ራሱ የሚወጣቸው የሚሆንበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ ነገር ግን በባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ በፓልዳውም ይሁን በዳማው የሚወሰኑ ውሳኔዎች የግለሰቡን ወይም የቤተሰቡን አቅም ያገናዘበ የሚሆንና ከግለሰቡ አቅም በላይ ቢሆን እንኳ የጎሳ አባላቱ በጋራ ተባብረው ይወጡታል፡፡ ይህ ደግሞ የማህበረሰቡን አንድነት የበለጠ ያጠናክረዋል፡፡

## 5.5 ለሁለቱ ተቋማት ማህበረሰቡ ያለው አመለካከት

ምንም እንኳ የነፍስ ማጥፋት፣ አስገድዶ መድፈር የመሳሰሉት ወንጀሎች አሁን ድረስ በመደበኛ ሥርዓቱ መዳኘት እንዳለባቸው የወንጀል ህጉ ያስገድዳል፡፡ ከእነዚህ ከባድ ወንጀሎች እስከ ቀላል የሚባሉ የስርቆትና የስድብ ወንጀሎች በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ቢዳኙም የመጨረሻ እልባት የሚያገኙትና ማህበረሰቡም ትክክለኛ ውሳኔ እንደተሰጠው የሚያምነው በባህላዊ የእርቅ ሥርዓቱ ሲያልፍ ነው፡፡

በተለይም የነፍስ ማጥፋት፣ የንብረት ማውደም የመሳሰሉት ወንጀሎች በፍርድ ቤት ውሳኔ ቢያገኙም ድርጊት ፈፃሚው ፍርዱን ጨርሶ እንኳ በቀላሉ ወደ ማህበረሰቡ አይቀላቀልም፡፡ የመገለል፣ የበቀልና የጥቃት ሰለባ እንደሚሆን ያምናል፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው ሚስቱን በጥርጣሬ የገደለ አባዎራ በመደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሰቶት ፍርዱን ጨርሶ ይመጣል፡፡ የሚኖርበትን ማህበረሰብ እና የሚች ሚስቱን ቤተሰብ እንዲሁም ልጆቹን ማሩኝ በማለት

በባህላዊ የእርቅ ሥርዓቱ ይቅርታ ጠይቆ ወደ ቤቱ ተመልሷል (የቡድን ውይይት፣ መስከረም 5/2008 ዓ/ም)፡፡

በመሆኑም በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች እንኳ ቢሆኑ በባህላዊ ስርዓቱ ማለፍ እንደ ግዴታ ማህበረሰቡ ይወስደዋል፡፡ ይህ አስተሳሰብ በተለይም ከብሔረሰቡ የአስተምሮት እሴቶች የሚመነጭና የባህላዊ ፍትህ ስርዓቶች አምልኮአዊ ገጽታ ስላላቸው የሚሰጡ እርግማኖች መገለሎች በወንጀል ፈፃሚው ባይሆን እንኳ በዘር ማንዘሩ ይደርሳል የሚል ፅኑ እምነት ስላለ ነው፡፡

## 5.6 የባህላዊ ሥርዓቱ ጥንካሬና ክፍተት

በየትኛው ዘመን የነበሩና ያሉ አስተሳሰቦች፣ ድርጊቶች እምነቶችና ሥርዓቶች የራሳቸው የሆኑ ጉድለትና ጥንካሬ አሏቸው፡፡ እነዚህ ጉድለቶችና  ጥንካሬዎች ለየደረሱበት ዘመን እና የአስተሳሰብ ደረጃ እየተለወጡ፣ እየተሻሻሉ አልያም ፍጹም በሌላ አስተሳሰብና ተግባር እየተቀየሩ ይመጣሉ፡፡ የድራሼ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓትም ከዚህ አስተሳሰብ የወጣ አይደለም፡፡በመሆኑም በባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱ የሚስተዋሉ ክፍተቶች እንዲሁም ጥንካሬዎች እንዳሉ ማስተዋል ተችሏል፡፡ ክፍተቶች እንዳሉ ሁሉ በቀዳሚነት ጥንካሬውን እንመልከት፡፡

### 5.6.1 የባህላዊ ሥርዓቱ ጥንካሬዎች

በባህል ሥርዓቱ ከሚስተዋሉት ጠንካራ ጎኖች አንዱ በየደረጃው ግጭቶች የሚፈቱበት ስርዓት መዋቅር መኖሩ ነው፡፡ ይህ የፍትህ ሥርዓት እንደ ችግሮቹ ዓይነትና ስፋት ውሳኔ እየሰጠ መሄዱ ደግሞ ለማህበረሰቡ ህይወት መቃናት ትልቅ አስተዋፆኦ አለው ማለት ይቻላል፡፡ በየደረጃው ውሳኔ መሰጠቱ ብቻ ሳይሆን በህብረተሰቡ ተመራጭ መሆኑ ደግሞ ከመደበኛው የፍትህ ሥርዓት እንደ አማራጭ ሆኖ መቀጠል መቻሉ ነው፡፡ በዚህም ማህበረሰቡ ጠንካራ የአንድነት፣ የመቻቻል፣ የመረዳዳት ባህል እንዲኖረው አደርጓል፡፡

በሌላ መልኩ በባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱ የሚከናወኑ አምልኮአዊና ባህላዊ ሥርዓቶች ማህበረሰቡን የመቆጣጠር፣ የመግታት የማረም ሚናን ሲጫወቱ እንመለከታለን፡፡ በተለይ የብሔረሰቡ አምልኮአዊም ሆነ አስተዳደራዊ መሪዎች እርስ በእርስ በተሳሰረው መዋቅር በመጠባበቅ የማህበረሰቡን ህልውና ያስቀጥላሉ፡፡ በአንድ መዋቅር ውሳኔ ያላገኘ ጉዳይ ወደ

ሌላኛው መዋቅር በመውሰድ ፍትህ ለማግኘት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ በመንደር መሪ ‹‹ሻና›› ያልተፈታ ጉዳይ ወደ ጎሳው መሪ ‹‹ፓልዳ›› በመውሰድ ውሳኔ እንዲያገኝ ይሆናል፡፡ በጎሳ መሪዎች የሚፈቱ ችግሮች በ‹‹ዳማው›› መፍተሄ ያገኛሉ፡፡ እነዚህ መዋቅራዊ ትስስሮች የባህላዊ ሥርዓቱ የህልውና መሠረቶችና ጥንካሬዎች ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የውሳኔ አፈጻጸም ሂደትን የሚከታተል ‹‹ሆርቤ›› የተሰኘ አካል መሰየሙ፤ ይህንን የሚያስፈጽሙ እንደ ‹‹ዋሎት››የመሳሰሉ አደረጃጀቶች መኖራቸው የባህል ሥርዓቱ የተቀመጡ እንደ ‹‹ሞት›› ዓይነት ቅጣት በንጉሱ ችሎት ‹‹በአረፋይታ›› ብቻ እንዲወሰን መደረጉ ማዕከላዊነቱት እንዲጠበቅና ከፍተኛ ጥፋት የሚባሉት መዳኘት ያለባችው በጥንቃቄ ታይተው እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡ እንዲህ ለማሳያ የቀረበ እንጂ በባህል ሥርዓቱ እጅግ በርካታ የሚታዩ ጠንካራ ጎኖችን ማንሳት ይቻላል፡፡

## 5.6.2 የባህላዊ ሥርዓቱ ክፍተቶች

በዚህ የባህል ሥርዓት ውስጥ ከሚታዩ ክፍተት አንዱ በፍትህ ስርዓት ውስጥ ውሳኔ የሚሰጡ አካላት በዘር ሐረግ የሚወርሱት በመሆኑ የተዛባ ፍትህ (ውሳኔ) ቢሰጡ እንኳ በዚህ ስልጣናቸው ለመቀጠል ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ በተለይም ‹‹ዳማው››፣ ‹‹ሼላው›› እንዲሁም ‹‹ሻናው›› በዘር ሐረግ የሚወረሱ እንጂ በህዝቡ ምርጫ የሚቀመጡ አይደሉም፡፡ ይህ ደግሞ ለህዝቡ እድል የሚሰጥ አይሆንም፡፡ በሌላ መልኩ የዳማው ውሳኔ ፍጹማዊ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህ ደግሞ ለይግባኝ ዕድል የሚሰጥ አለመሆኑ የባህል ስርዓቱ ክፍተት ነው፡፡ በተጨማሪ በባህላዊ ሥርዓቱ ሴቶችና ህፃናት ተሳታፊ አይደሉም፡፡ እንዲሁም ከችሎት አደባባይ ‹‹ሞራ›› እንዲርቁ ይደረጋል፡፡ የመወገንም ሆነ ሀሳብ የመስጠት ዕድል የላቸውም፡፡ ይህንን በተመለከተ መረጃ አቀባዮቹ አንድ ታሪክ ነግረውኛል፡፡ በአንድ ወቅት የድራሼ ዳማ በድንገት ይሞታል፡፡ ይህ ‹‹ዳማ›› ወንድ ልጅ ሳይወልድ ስለሞተ ሴቷ ልጅ መውረስ አለባት በሚል ከፍተኛ ክርክር ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም ሴቷ የዳማነት ማዕረግ ሳታገኝ ቀርታለች፡፡ ይህም የሚያሳየው የባህላዊ ሥርዓቱ ለሴቶች ቦታ የማይሰጥና ተሳትፏቸው መገደቡ ሌላው የስርዓቱ ክፍተት ነው፡፡

## 5.7 በባህላዊ ሥርዓቱ የሴቶችና የህፃናት ተሳትፎ

በድራሼ ብሔረሰብ የባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ ሴቶችም ሆኑ ህፃናት ተሳታፊ አይደሉም፡፡ እንዲሁም በችሎት አደባባይ ‹‹ሞራ›› ላይ እንዲቀመጡ አይፈቀድም እንደ ነውር ተግባር ይታያል፡፡ በፍትህ ሥርዓቱ ወቅት የሴቶች ሚና ለእርቅ የተዘጋጀውን ጨቃና ምግብ ማቅረብ ብቻ ነው፡፡ ሴቷ ተበድላ እንኳ ቢሆን ችሎት የሚቆምላት የቅርብ ቤተሰብ የሆነ ወንድ ነው፡፡ በችሎት አደባባይ ተገኝተው የፍርድም ሆነ የድርድር ሂደቶችን ቢከታተሉ ስራ ፈት ተደርገው እንደሚታዩ መረጃ አቀባዮቹ ገልጸውልኛል፡፡

ይህ ከጥንት ጀምሮ የመጣ ባህል ስለሆነ ዛሬም ድረስ ዘልቋል፡፡ ይህንኑ በድራሼና በአሌ ብሔረሰብ በባህላዊ የእርቅ ስርዓት አፈፃፀም ወቅት ማስተዋል ችያለሁ፡፡ በየትኛውም የባህላዊ እርቅ ስርዓቱ አይሳተፉም፡፡ ይልቅስ በስተመጨረሻ የታረዱ ከብቶችን ስጋ በመጥበስ ሲያዘገጃጁ ተመልክቻለሁ፡፡

በተመሳሳይ ህፃናትም በባህል ሥርዓቱ ተሳትፎ የላቸውም፡፡ ለአቅመ አዳም ከደረሱ ብቻ በ‹‹ሞራ›› የችሎት አደባባይ ተገኝተው የችሎት ሥርዓቱን እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡

# 6 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የድራሼ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓትን የተመለከተ ነው፡፡ ዓላማው አድርጎ የተነሳው የብሔረሰቡ የግጭት አፈታት ሥርዓት ምን እንደሚመስልና ግጭቶቹን ለመፍታት የሚከተሏቸው ሥርዓቶች፣ ደንቦችና መዋቅሮችን መመርመር ነው፡፡

በጥናቱ እንደተጠቀሰው የድራሼ ብሔረሰብ አራርሳ (ሆሮታ) ተብሎ የሚጠራ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓት አለው፡፡ ብሔረሰቡ የራሱ የሆነ የአስተዳደርና የፍትህ ተቋማት መዋቅር አለው፡፡ በእነዚህ መዋቅሮች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ይዳኛል፣ ውሳኔ ይሰጣል፣ ቅጣት ይጥላል፡፡ ግጭቶች ሲፈጠሩ ከቤተሰብ መሪ ኦስማረ፣ ሼላ/ሻና፣ ፓልዳ፣ ዳማ ባሉ መዋቅሮች መፍትሄ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

በድራሼ ብሔረሰብ ተዘውትረው የሚከሰቱ ዋነኛ የግጭት ዓይነቶች የጎሳ ግጭት፣ ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚፈጠር ግጭት የነፍስ ግድያ ግጭትና የጠለፋ ግጭት ናቸው፡፡ የእነዚህ ግጭቶች ምክንያቶች ድንበር መግፋት በሰው ንብረት ላይ ሰደድ እሳት መልቀቅ መካካድና ጊዜያዊ ግጭቶች መሆናቸው ታይቷል፡፡ እነዚህን ግጭቶች ከላይ በተጠቀሱ ባህላዊ የፍትህ ተቋማቱ እንደ ክብደትና ዓይነታቸው ታይተው ባህላዊና አምልኮአዊ ሥርዓቶችን አልፈው መፍትሄ ይሰጥባቸዋል፡፡

የነፍስ ግድያ፣ የንብረት ማውደም ግጭቶች ዳኝነት የሚሰጥባችው በዳማው የአራፋይታ ችሎትና እንደ ጥፋቱ ዓይነት በፓልዳው የሞራ ችሎት ብቻ ነው፡፡ በሻሌ፣ ሻና እና ኦስማራ መዋቅር እንዲህ ዓይነት ግጭቶች ለውሳኔ ወይም ለዳኝነት አይቀርቡም፡፡ በተመሳሳይ የሁለት ጎሳ ግጭቶች የመጨረሻ ውሳኔ የሚያገኙት በዳማ (ንጉስ) ችሎት ብቻ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

በፍትህ ሥርዓቱ መዋቅር ውስጥ የሚገኙት ዳማው፣ ፓልዳውና ሼላው መለኮታዊ ባህሪ አላችው ተብሎ ስለሚታመን ውሳኔያቸው ተቀባይነቱ ከፍ ያለ ነው፡፡ በሥርዓቱም ከሚወሰኑ ውሳኔዎች አንዱ ‹‹እርግማን›› ነው፡፡ ይህ እርግማን የሚከወነው በእነዚህ የፍትህ ሥርዓቱ መሪዎች ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ እነዚህ አካላት መለኮታዊ ባህሪ አላቸው ብሎ ስለሚያምን ለባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱ አክብሮትና ታማኝነት አለው፡፡ በዚህም ዛሬም

ድረስ ከመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ይልቅ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ በማህበረሰቡ ተቀባይነቱ ከፍ ያለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ይሁን እንጂ የባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱ ሴቶችን ህፃናትን እና ‹‹ሀውዳ›› ተብለው የሚጠሩ የእጅ ጥበብ ሰራተኛ የሆኑ የማህበረሰቡ ክፍሎችን ያገለለ ነው፡፡ በየትኛውም የፍትህ ሥርዓት እነዚህ የህብረተሰቡ ክፍሎች ተሳታፊ እንዳልሆኑ በጥናቱ ወቅት ማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ ረገድ መደበኛው የፍትህ ሥርዓት የተሻለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሁለቱ ተቋማት መደበኛውና ባህላዊው በመደጋገፍ እንደሚሰሩ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በአንፃራዊነት የባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ፋይዳ ከፍ ያለ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

# ይሁንታ

የድራሼ ብሔረሰብ ከመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ይልቅ ለባህላዊ ፍትህ ሥርዓት ተገዥና ቅርብ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ማህበረሰቡ ይህን ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት ምርጫው ካደረገ ይህንኑ በማጠናከር በአብሮነት ህይወቱ የሚገጥሙ ችግሮችን እየፈታ፣ ባህልና ወግን ጠብቆ ማንነቱን ይዞ እንዲቀጥል መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ይህ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓት የበለጠ ጎልብቶ ፋይዳው ከፍ ያለ እንዲሆን የሚታዩ ክፍተቶች እንዲሻሻሉ፤ ጥንካሬዎቹ ደግሞ የበለጠ እንዲጎለብቱ የሚከተሉትን አሳቦች አቀርባለሁ፡፡

1. በባህላዊ የግጭት ፍትህ ሥርዓት ውስጥ በዳኝነት ሆነ ሀሳብ አቅርቦ የመከራከር ዕድል ለሴቶች የተዘጋ ነው፡፡ በመሆኑም ሴቶች የማህበረሰቡ አንድ አካል ናቸውና በባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ዕድል ቢሰጣቸው፣
2. በባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ የዳማው ችሎት /አራፋይታ/ በአደረጃጀቱም ሆነ በአባላቱ የተሳትፎ መረጣ የተሻለ በመሆኑ አሁን በተግባር ላይ ባለመሆኑ ወደ ነበረበት እንዲመለስ የባህላዊ ተቋማቱ መሪዎችም ሆነ የሚመለከታቸው አባላት ቢያደርጉ የባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱ የበለጠ ይጠናከራል፣
3. የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ መደበኛውን የፍትህ ሥርዓት የሚደግፍ መሆኑ የሚታመን ቢሆንም ይህ ጎልብቶ ሁለቱ ተቋማት የበለጠ መደጋገፍ በውስጣቸው እንዲኖር የባህላዊ መዋቅሩን መሪዎች ከዘመናዊ አሰራር፣ ዕውቀትና አቅጣጫን እንዲከተሉ ማድረግ ይገባል፡፡ ይህም የሚሆነው የባህላዊ ሥርዓቱን ደንቦች በማጥናት፣ ልዩ ልዩ አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት በውይይት በማበልጸግ ነው፡፡
4. በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ የሚታዩ፣ እሴቶችና ሥርዓቶች በሚገባ ተቀርጸው በዘመናዊ የዳኝነት ሥርዓቱ ቢካተቱና በትምህርት መዋቅርም ውስጥ ገብተው ለአዲሱ ትውልድ እንዲደርሱ የሚደረግበት ዘዴ ቢፈለግ፣
5. በአካባቢው የሚስተዋሉ ግጭቶች ከመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ይልቅ በባህላዊ የእርቅና የሽምግልና ሥርዓት ሲዳኙ ውጤታማ መሆናቸው በጥናቱ ወቅት ለመንገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህን ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻልበት መንገድ ቢፈለግ መልካም ነው፡፡
6. በባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ‹‹ሀውዳ›› ተብለው የሚጠሩ እና ዝቅ ተደርገው የሚታዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች ዛሬም ድረስ አሉና በባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱ ተሳታፊ

የሚሆኑበትን እንዲሁም በማንኛውም ማህበራዊ ግንኙነቶች የሚገለሉበትን ሁኔታን ለመፍጠር ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ቢሰራ፣

ከላይ የተዘረዘሩ የይሁንታ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲሁም በባህላዊ ግጭት አፈታት ላይ የሚሰሩ ግለሰቦች ተሳትፎ ቢያደርጉ ለባህላዊ ስርዓቱ መጎልበት አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ የድራሼ ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህ ስርአትን የበለጠ በማጎልበት በውስጡና ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር ያለውን ግንኙነት የተሻለ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ በአካባቢው ተደጋግሞ የሚፈጠረውን የብሔረሰቦች ግጭት በዘላቂነት ለመፍታት ይህን ባህላዊ ሥርዓትና እምነት መጠበቅና ማሳደግ ይገባል፡፡ በባህላዊ ሥርዓቱም እጅግ ጠቃሚ እሴቶችና ሥርዓቶች በመኖራቸው እነዚህን ለይቶና አደራጅቶ ጥቅም ላይ ማዋል የዚህ ትውልድ ኃላፊነት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

## የተጠቀሱ ምንጮች


ሐንሳሞ ሐመላ፤ በደቡብ ኢትዮጵያ ወግና ልማድ የድራሼ ሕዝብ ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፤ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች፤ 1993፡፡

ማህተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ የኢትዮጵያ ባህል ጥናት፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፤ 1960፡፡

ባህሩ ዘውዴ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847-1983፡፡ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኑቨርስቲ ፕሬስ፤ 2007፡፡

ተመስገን ምንዋጋው፤ ሀገረሰባዊ የግጭት መፍትሔ ሥርዓት በዶኮ-ጋሞ፤ የኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤ 1998፡፡

አብዱልፈታህ አብደላህ፤ ሜራ አታ ኮንሶ የኮንሶ ብሔረሰብ የባህል ሕግ ሥርዓት፡፡ አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ የፍትህ ሥርዓቶች ማዕከልና የኮንሶ ወረዳ አስተዳደር፤ 2006፡፡

አብርሃም ታደሰ፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ፤ የኤም. ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥና-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤ 1999፡፡

አንዷለም አባተ፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በመኤኒት ብሔረሰብ፤ የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤ 2004፡፡

ደስታ ተክለወልድ፤ ዐዲስ ያማርኛመዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1962፡፡

የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ፕሮፋይል፣ 2001 ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት፡፡ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፤ 1987፡፡

ገብሬ ይንቲሶና ሌሎችም፣ <u>ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች በኢትዮጵያ፡ቅጽ 1</u> በኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት የማስማማትና ዕርቅ ማዕከል አዲስ አበባ፤ (2004)፡፡

……………. <u>ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች በኢትዮጵያ ቅጽ 2</u> በኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት የመስማማትና ዕርቅ ማዕከል አዲስ አበባ፤ 2005፡፡

ይልማ ተፈሪ፤ የሽምግልና እርቅ ሥርዓት በወላይታ፤ የኤም. ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤ 1998፡፡

ፈቃደ አዘዘ፤ <u>የሥነ-ቃል መመሪያ</u>፤ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ የኒቨርስቲ መጻሕፍት ማዕከል ሁለተኛ ዕትም፤ 1993፡፡

Bender M.L and etal (e d s), <u>Languages in Ethiopia.</u> London: Oxford University Press. 1976.

Black, Paul. `Lingushtic Evidence of the Origin of Konsoid Peoples`. Proceedings of the first United States Confrence on Ethiopian Studies. East Lansing Michigaan State University.1973.

Bohaman, Paul, (ed.) "Introduction" <u>Law and War Fare; Studies in the Anthropology of Conflict</u>. Austin University of Texas press፡ 1967.

Coser, Lewis. <u>Conflict, Social Aspect</u>, International Encyclopedia of Social Sciences vol.3. The Macmillan Company and Free Press, 1968.

………………...<u>The Function of Social Conflict</u>. New York: and Basic Books inc, Publishers, 1956.

Deutsch, M. <u>The Resolution of Conflict</u>.New Haven: Yale University, Press, 1973.

Firew Tesfaye. The Quest for Empowering Indigenous System in Local Self-Governance among the Dirashe Of South Western Ethiopia. M.A. Thesis, A.A.U. 2012.

Fisher, Ronald. Social Psychology. An Applied Approach.New York: St. Martin's Press, 1982.

Goldstein, Kenneth. A Guide for Field Workers in Folklore. Penny/vain Gale Research Company American folklore association inc,1974.

Gulliver, P.H. Disputes and Negotiations: A Cross Cultural Perspective. London: Academic Press, Inc, 1997.

Hallpike C.R. 'The konso of Ethiopian A study of the values of acushitic people.' Oxford at the clarendon press, 1972.

Hansamo, Hamela, Internal History of Dirasha /Gidole/. B.A, Fourth Year Essay, A.A.U, 1983.

Hayward, D. 'Some observations on diraytat (Gidole) Pronouns'. In Gideo Golden Berg (ed). The Proceedings of the six International Conference of Ethiopian studies Tel-Aviv. 1980.

Heinz J. Conflict — A Literary Review". University OF Duisburg - Essen, 2006.

Jeong. Ho-Wan. Peace and Conflict Studies an Introduction. England：Ashgate Publishing Ltd. 2000.

Kuper, Adam and Jussica Kuper (eds). The Social Science Encyclopedia, (2nd ed.) London: Rutledge.1996.

Leslau, WolF. English- Amharic Context Dictionary. Baden Otto Harrissowitz Wies：1973.

_______________. Continuities in the study of Social Conflict. The Free Press, New York, 1973.

Levinson, David and Melvin Ember. Encyclopedia of Cultural Antropology- New York: Henry Holt and Company Inc- Vol. 1, 1996.

Loomis, Charles P. and Zonalk. Loomis. Modern Social Theories. Princeton D. Vans No Stand Company. Inc. 1965.

Medhane Tadesse. The Quest For Conflict Settlement in Ethiopia's Territory, Addis Ababa, 2004.

Mike and Cook. Doing Ethnography. Londo: SAGE Publishing: 2007.

Schellenberg, James A. Conflict Resolution. Theory. Research and Practice. Albany: State University OF New York Press, 1996.

Tizazu Desalegn. Inter Ethnic Conflict in South Western Ethiopia a Case Study of Resource Based Inter Ethnic Conflict Between Zaysa and Dirashe Communities and Attempts For Transformation. M.A. thesis, A.A.U. 2007.

Wondwoson Tesfaye, Aspects of Diryayatat morphology and syntax. Doctoral Thesis of NINU, Norwegian University of Science and Technology Faculty of Arts. 2006.

Yednekachew Ayel. Management and Transformation of Conflict Between Dirashe and Konso. M.A. thesis A.A.U. 2011.

Zartman, William I. and Francis M. Deng (ed). Conflict Resolution in Africa. Washington. D.C; the Bro oking Institution, 1991.

_______________.Traditional Cures of Modern Confilicts: Affrican Confilict `` Medicine Colorado: Rienner Publishers. Inc. 2000.

**አባሪ አንድ፡- ለቃለ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች**

1. በብሔረሰቡ የግጭት መፍቻ ሥርዓት ምን ተብሎ ይጠራል?
2. በብሔረሰቡ ተዘውትረው የሚፈጠሩ የግጭት ዓይነቶች ምንድ ናቸው?
3. በሽምግልና ሥርዓት ውስጥ ነገር ለማየት የሚቀመጡት እን ማን ናቸው?
4. ግጭት የሚፈታበት ባህላዊ መዋቅር አለወይ?
5. በመዋቅሩ ውስጥ የሥራ ዘመን ገደብ አለ ወይ?
6. ለዳኝነትና ለሽምግልና አይበቁም ተብለው የማይመረጡ የማህበረሰብ ክፍሎች አሉ? ካሉ እነማን ናቸው? ለምን አይመረጡም?
7. ግጭት ሊፈጠር መጀመሪያ ለማን ነው የሚነገረው?
8. ነጋሪው ማን ነው?
9. እንዴት ነው የሚነገረው?
10. ሽማግሌዎች ምስክሮች ጠርተው ቃል ይቀበላሉ?
11. የሀገር ሽማግሌዎች ወደ ውሳኔ የሚያመሩበት መንገድ ምን ይመስላል?
12. ውሳኔ የሚገለጽበት የተለየ ስፍራ አለ?
13. ውሳኔ አሰጣን በበላይነት የሚመራ ማን ነው?
14. በመደበኛውና በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋም መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት አለ?
15. የባህላዊ ፍትህ ተቋሙ አሁን ያለበት ሁኔታ ምን ይመስላል?
16. የባህላዊ ፍትህ ተቋሙ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎችን ያሳትፋል?
17. ከመደበኛውና ከባህላዊው የፍትህ ተቋም በማህበረሰቡ የትኛው የበለጠ ተቀባይነት አለው?
18. በባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱ የተወሰኑ ውሳኔዎች ውስጥ ለአብነት የሚነሳ ታሪክ አለ?

**አባሪ ሁለት፡-** ለቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. በብሔረሰቡ ተዘውትረው የሚፈጠሩ የግጭት ዓይነቶች ምንድን ናቸው?
2. በሽምግልና ሥርዓት ውስጥ ነገር ለማየት የሚቀመጡት እን ማን ናቸው?
3. በመዋቅሩ ውስጥ የሥራ ዘመን ገደብ አለ ወይ?
4. ለዳኝነትና ለሽምግልና አይበቁም ተብለው የማይመረጡ የማህበረሰብ ክፍሎች አሉ? ካሉ እነማን ናቸው? ለምን አይመረጡም?
5. ሽማግሌዎች ምስክሮች ጠርተው ቃል ይቀበላሉ?
6. የሀገር ሽማግሌዎች ወደ ውሳኔ የሚያመሩበት መንገድ ምን ይመስላል? ውሳኔ አሰጣን በበላይነት የሚመራ ማን ነው?
7. በባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱ የተወሰኑ ውሳኔዎች ውስጥ ለአብነት የሚነሳ ታሪክ አለ?
8. የባህላዊ ፍትህ ተቋሙ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎችን ያሳትፋል?
9. በመደበኛውና በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋም መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት አለ?

## አባሪ ሶስት፡- ልዩ ልዩ ፎቶዎች



**ፎቶ አንድ፡-** ከግራ ወደ ቀኝ የጎሳ መሪ አቶ ካቶ ኩሾ መሀል አጥኚው እና የመጀመሪያ ወንድ ልጃቸው



**ፎቶ ሁለት፡-** በባህላዊ ሥርዓቱ መዋቅር ከግራ ወደ ቀኝ  ሼላ፣ ሻና እና ሱጋ መሪዎች



**ፎቶ ሶስት፡-** በቡድን ውይይት ወቅት




**ፎቶ አራት፡-** የተቀዳው ደም ከጨቃ ከቀበርኛ ጋር ሲቀላቀል፡፡



**ፎቶ አምስት፡-** የበጎቹ አንገት ሳይታረድ ለንባብ አንጀት ሲወጣ፡፡



**ፎቶ ስድስት፡-** ሞራ የባህላዊ የዳኝነት ስፍራ



**ፎቶ ሰባት ፡- የባህላዊ መሪዎች በሞራ የዳኝነት ስርዓት ላይ**

## አባሪ ሶስት፡- የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ/ቁ | የመረጃ ሰጪዎች ስም | ጾታ | የሚወለዱበት ጎሳ | የሚኖሩበት አካባቢ | ማህበራዊ ኃላፊነት | ሃይማኖት | ዕድሜ | ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ካቶ ኩሾ | ወ | ካላይት | ላይኛው አርጎባ | የጎሳ መሪ | | 58 | ግብርና |
| 2 | አቶ ታደሰ ተሸባሌ | ወ | ዋሌሳ | ጊዶሌ | የሀገር ሽማግሌ | ፕሮቴስታንት | 51 | ግብርና |
| 3 | አቶ ብሩ ሰማሎ | ወ | አርጋማይታ | ጊዶሌ | የሀገር ሽማግሌ | ኦርቶዶክስ | 61 | ጡረተኛ |
| 4 | አቶ መለሰ ማሞ | ወ | ካርጭት | አፊያ | የአካባቢ ነዋሪ | ፕሮቴስታንት | 42 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 5 | አቶ ዳትኮ ኪታንቦ | ወ | ኤላይታ | ያያቤ | የሀገር ሽማግሌ | | 89 | ግብርና |
| 6 | ወ/ሮ ፍሬህይወት ግርማ | ሴ | ካላይት | ዋላይቴ | የአካባቢ ነዋሪ | ፕሮቴስታንት | 38 | መምህርት |
| 7 | አቶ ጉደታ ኩቤ | ወ | አርጋማይት | ጊዶሌ | የአካባቢ ነዋሪ | ኦርቶዶክስ | 45 | የፖሊስ ኮማንደር |
| 8 | አቶ ታምሩ ጌታሎ | ወ | ካላይት | ጊዶሌ | የአካባቢ ነዋሪ | ፕሮቴስታንት | 46 | ግብርና |
| 9 | ወ/ሮ ማሚቴ ማሞ | ሴ | ኤላይታ | ያያቤ | የአካባቢ ነዋሪ | ፕሮቴስታንት | 62 | ግብርና |
| 10 | አቶ ተስፋዬ ኦዳይቴ | ወ | ኤላይታ | ጊዶሌ | የጎሳ መሪ | ፕሮቴስታንት | 56 | ግብርና |
| 11 | አቶ ይልማ ከተማ | ወ | ካላይት | ጊዶሌ | የአካባቢ ነዋሪ | ኦርቶዶክስ | 40 | ሰራተኛ |
| 12 | አቶ ወዳጅ ታዬ | ወ | አርጋማይጥ | ሽሌሌ | የቀበሌ ሊ/መንበር | ኦርቶዶክስ | 42 | ግብርና |
| 13 | ወ/ሮ ዳንደኔ ደባ | ሴ | ኮላይት | ያያቤ | የቤት እመቤት | ፕሮቴስታንት | 63 | ግብርና |
| 14 | አቶ ዘላለም አምሳሉ | ወ | አርጋማይት | ጊዶሌ | የአካባቢ ነዋሪ | ኦርቶዶክስ | 43 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 15 | አቶ ዘነበ ማሌ | ወ | ሞስዬ | ጊዶሌ | የፍርድ ቤት ዳኛ | ፕሮቴስታንት | 43 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 16 | ወ/ሮ ካሰች ኢካ | ሴ | አርጋማይት | ቀያማ | የቤት እመቤት | | 48 | ግብርና |
| 17 | አቶ ደበላ ቶላ | ወ | ካንሰት | ጋርዳ | የሀገር ሽማግሌ | | 80 | ግብርና |
| 18 | አቶ አየለ ኦዳይተ | ወ | ካንሰት | ያያቤ | የሀገር ሽማግሌ | | 60 | ግብርና |
| 19 | አቶ አይሩ ይታሞ | ወ | ማሊት | ዋላይቴ | የመንደር መሪ | | 56 | ግብርና |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | አቶ አማኑኤል ማሞ | ወ | | ጊዶሌ | የሀገር ሽማግሌ | | 57 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 21 | አቶ ጊዶላ ኪቴ | ወ | ኤላይት | ጊዶሌ | | | 54 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 22 | አቶ ከበደ ኮሻ | ወ | ካላይት | አርጎባ | የመንደር መሪ | | 55 | ግብርና |
| 23 | አቶ ደበርሻ ዳያማ | ወ | ካርጭት | ቀሌሳ | የሀገር ሽማግሌ | | 75 | ግብርና |

## ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች

| ተ/ቁ | የመረጃ ሰጪዎች ስም | ጾታ | የሚወለዱበት ጎሳ | የሚኖሩበት አካባቢ | ማህበራዊ ኃላፊነት | ሃይማኖት | ዕድሜ | ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ካቶ ኩሾ | ወ | ካላይት | ላይኛው አርጎባ | የጎሳ መሪ | | 58 | ግብርና |
| 2 | አቶ ታደሰ ተሸባሌ | ወ | ዋሌሳ | ጊዶሌ | የሀገር ሽማግሌ | ፕሮቴስታንት | 51 | ግብርና |
| 3 | አቶ ብሩ ሰማሎ | ወ | አርጋማይታ | ጊዶሌ | የሀገር ሽማግሌ | ኦርቶዶክስ | 61 | ጡረተኛ |
| 4 | አቶ መለሰ ማሞ | ወ | ካርጭት | አፊያ | የአካባቢ ነዋሪ | ፕሮቴስታንት | 42 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 5 | አቶ ዳትኮ ኪታንቦ | ወ | ኤላይታ | ያያቤ | የሀገር ሽማግሌ | | 89 | ግብርና |
| 6 | ወ/ሮ ፍሬህይወት ግርማ | ሴ | ካላይት | ዋላይቴ | የአካባቢ ነዋሪ | ፕሮቴስታንት | 38 | መምህርት |
| 7 | አቶ ይልማ ከተማ | ወ | ካላይት | ጊዶሌ | የአካባቢ ነዋሪ | ኦርቶዶክስ | 40 | ሰራተኛ |
| 8 | አቶ ዘላለም አምሳሉ | ወ | አርጋማይት | ጊዶሌ | የአካባቢ ነዋሪ | ኦርቶዶክስ | 43 | የመንግስት ሰራተኛ |
| 9 | ወ/ሮ ዳንደኔ ደባ | ሴ | ኮላይት | ያያቤ | የቤት እመቤት | ፕሮቴስታንት | 63 | ግብርና |